ምዕራፍ አንድ

1. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ትምህርታችሁ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸውን ተምራችኋል። በመቀጠል በዚህ ምዕራፍ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና በተጨማሪ የቁጥር ቤት ዋጋቸውን ትለያላችሁ።

የትምህርቱ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች

- የቁጥሮች ቤት ዋጋን ትረዳላችሁ።
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በማወዳደር በቅደም ተከተላቸው ታስቀምጣላችሁ።

1.1 በመቶዎች እና በሺህዎች መቁጠር

መግቢያ

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ በመጀመሪያ ቁጥሮችን በመቶዎች መቁጠር ጽንሰ-ሀሳብ፤ በመቀጠል ቁጥሮችን በሺህዎች መቁጠር ለማስታወስ የሚረዱ ተግባራት እና መልመጃዎች ቀርቦላችኋል።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- **በመቶዎች እና በሺህዎች ትቆጥራላችሁ።**

1.1.1 በመቶዎች መቁጠር

ተግባር 1.1

ከዚህ በታች ያሉት እያንዳንዳቸው 100 ሎሚዎች የሚይዙት የቅርጫት ምስሎች ተመልክታችሁ ቀጥሎ የተሰጡትን ጥያቄዎች በ"ሀ" መሠረት መልሱ።

ሀ.  2 x 100 = 200

ለ.  3 x 100 = _____

ሐ.  4 x 100 = _____

መ.  5 x 100 = _____

ማስታወሻ፦

- **ቁጥሮችን በመቶዎች ስንቆጥር ቀጣዩን ቁጥር ለማግኘት መቶን እየጨመርን እንሄዳለን።**

ምሳሌ 1.1፦

ከዚህ በታች ያሉት ብሎኬቶች ውስጥ የሚገኙ የካሬዎች ብዛት በመቁጠር ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

ሀ.  $1 \times 100 =$ _____

ለ.  $4 \times 100 =$ _____

መፍትሔ፦

ሀ. $1 \times 100 = 100$ ለ. $4 \times 100 = 400$

መልመጃ 1.1

1. ከዚህ በታች በመቶዎች ቆጠራ ውስጥ የጎደሉትን ቁጥሮች በቁጥር መስመር ላይ ሙሉ።



2. ከዚህ በታች ያሉ ምስሎች እያንዳንዱ እስር 100 እንጨቶችን ይይዛሉ እንበል። የእስሮችን ብዛት በመቁጠር በጠቅላላው ስንት እንጨቶች እንዳሉ ትክክለኛ መልሳችሁን በባዶ ቦታ ሙሉ።

ሀ.  $3 \times 100 =$ _____

ለ.  $5 \times 100 =$ ___

1.1.2 በሺህዎች መቁጠር

ተግባር 1.2

ከዚህ በታች ያሉ የካሬ ምስሎች እያንዳንዳቸው 1,000 የተደራደሩ የስምንቶ ብሎኬቶች የሚያሳይ ሰንጠረዦችን በመጠቀም ትክክለኛውን የስምንቶ ብሌኬቶች ብዛታቸውን በመቁጠር ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

ሀ.  $1 \times 1{,}000 =$ _____

ለ.  ስንት የስምንቶ ብሌኬቶች አሉ?

ማስታወሻ፦

ቁጥሮችን በሺህዎች ስንቆጥር ቀጣዩን ቁጥር ለማግኘት በተሰጠው ቁጥር ላይ 1,000 እንደምራለን።

ለምሳሌ 1.2፦

1) ቆጠራን ከዜሮ ብንጀምር 1,000፣ 2,000፣ 3,000፣ እያለ ይቀጥላል። ምክንያቱም

$0 + 1{,}000 = 1{,}000$ $0 + 2{,}000 = 2{,}000$ $0 + 3{,}000 = 3{,}000$ ይሆናል።

2. ቆጠራን ከሁለት ብንጀምር 1,002፣ 2,002፣ 3,002 እያለ ይቀጥላል። ምክንያቱም

$2 + 1{,}000 = 1{,}002$ $2 + 2{,}000 = 2{,}002$ $2 + 3{,}000 = 3{,}002$ ይሆናል።

መልመጃ 1.2

1. የጎደሉትን ባዶ ቦታዎች በቁጥር መስመር ላይ ሙሉ።



2. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ።

ሀ	1,005	2,005			5,005	6,005			9,005
ለ	1,006		3,006	4,006			7,006	8,006	
ሐ	1,004						7,004		
መ	1,009	2,009		4,009		6,009		8,009	

3. የጎደለው ቦታ ሙሉ።

ሀ. 1,010፣ 2,010፣ _____ ፣ 4,010፣_____፣ _____፣ 7,010

ለ. 1,200፣ _____፣ _____፣ 4,200፣ 5,200፣ _____፣ ___ እና ___

ሐ. 3,000፣ 4,000፣ _____፣ _____፣ 7,000 እና _____

1.2 የእስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ

መግቢያ

በዚህ ንዑስ ርዕስ የእስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ እንዴት እንደምቀመጥ እና እንደሚጠራ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በመጠቀም በምሳሌዎች የተሠሩ ስለሆኑ ይህንን በመረዳት መልመጃዎችን በቀላል መሥራት ይችላሉ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የእስከ 10.000 ያሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋን ትለያላችሁ።

ተግባር 1.3

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ።
   ሀ. የምታውቁት የቁጥር ቤቶች እነማን ናቸው?
   ለ. የቁጥር ቤት ዋጋ እያደገ ወይም እየጨመረ የሚሄደው ከግራ ወደ ቀኝ ነው ወይስ ከቀኝ ወደ ግራ ነው?
   ሐ. ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር የቁጥር ቤት ስንት ነው?
   መ. ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር የቁጥር ቤቶች _____ እና _____ ናቸው።

ማስታወሻ፦

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች የአንድ ቤት ብቻ አሏቸው
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች በስተቀኝ ያለው ሆሄ የአንድ ቤት ስሆን በስተግራ ያለው ሆሄ የአስር ቤት ነው።
- ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮች በስተግራ ያለው ሆሄ የአንድ ቤት ነው፤ መሃል ያለው ሆሄ የአስር ቤት ነው፤ በስተመጨረሻው ግራ በኩል ያለው ሆሄ የመቶ ቤት ነው።
- ባለ አራት ሆሄ ቁጥሮች በስተቀኝ ያለው የአንድ ቤት ከሱ ቁጥር በስተግራ ያለው የአስር ቤት ከሱ ቀጥሎ በስተግራ ያለው የመቶ ቤት ስሆን ከሁሉም በስተግራ ያለው ሆሄ ደግሞ የሺህ ቤት ነው።
- ባለ አምስት ሆሄ ቁጥሮች ውስጥ በስተቀኝ ያለው ሆሄ የአንድ ቤት ከሱ ቀጥሎ በስተግራ ያለው የአስር ቤት፣ ከሱ ቀጥሎ

ምሳሌ 1.3፦

ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ በሺህ ቤት 2 ሺህዎች፣ በመቶ ቤት 3 መቶዎች በአስር ቤት 7 አስሮች እና በአንድ ቤት 8 አንዶች ይገኛሉ። ይህም ሲጻፍ 2,378 ተብሎ ይጻፋል።

			
የሺህ ቤት 2	የመቶ ቤት 3	የአስር ቤት 7	የአንድ ቤት 8

ምሳሌ 1.4 ፦

ቁጥሮች በቁጥር ቤት በአባካስ ስቀመጡ፤



የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት

ከዚህ በላይ ባለው አባካስ ውስጥ 2 አንዶች፣ 1 አስሮች፣ 2 መቶዎች እና 1 ሺህዎች አሉ።

ይህም 1,212 ተብሎ ይጻፋል። ሲነበብ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሃምሳ አራት ተብሎ ይነበባል

ምሳሌ 1.5፦

4,562 በቁጥር ቤት ስናስቀምጥ

የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት
4	5	6	2

በፊደል ሲጻፍ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ነው

መልመጃ 1.3

1. የሚከተለውን አባካስ በማየት ብዛታቸውን በቁጥር ቤት ሙሉ:



የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በየቤታቸው እና በፊደል ጻፉ።

ሙሉ ቁጥሮች	የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት	በፊዳል ሲጻፍ
9,463					
6,078					
2,560					
1,304					

3. የሚከተለውን ሠንጠረዠ ውስጥ ያሉ የቤቶችን ብዛት በመቁጠር ከታች ባለው በሆሄው ቤት ዋጋ ሙሉ።

1000 1000	100 100 100	10 10 10 10	1 1 1 1 1
የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት

4. የሚከተለውን አሳካሶችን በመጠቀም የተሰጡትን ቁጥሮች ብዛት በየቤታቸው በምስል አሳዩ።

ሀ. 9,876 ለ. 5,082 ሐ. 9,608

5. የእያንዳንዱን ቁጥር ሆሄያትን በየቤታቸው ጻፉ።

ሀ. 487 ____ የመቶ ቤት ___ የአስር ቤት ___ የአንድ ቤት

ለ. 6,453 ___ የሺህ ቤት ____ የመቶ ቤት ___ የአስር ቤት __ የአንድ ቤት

ሐ. 2,679 ___ የሺህ ቤት ___ የመቶ ቤት ___ የአስር ቤት ___ የአንድ ቤት

1.3 እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

መግቢያ

በዚህ ንዑስ ርዕስ እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን ያንሳል፣ ይበልጣል እና እኩል ይሆናል ምልክቶችን በመጠቀም እንዴት ማወዳደር እንደሚቻል በምሳሌዎች ተገልጸላቸዋል።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ታወዳድራላችሁ።

ተግባር 1.4

1. በክፍላችሁ ያሉ የሴት እና የወንድ ተማሪዎች ብዛት እኩል ነውን? እኩል ካልሆኑ የሚያንሰው እና የሚበልጠው ለመለየት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሳችሁን ስጡ።

ማስታወሻ፡

- ባለአራት ሆሄ ቁጥሮችን ስናወዳድር በመጀመሪያ የሺህ ቤቶችን እናወዳድራለን። የሺህ ቤት ትልቅ የሆነው ከሺህ ቤት ትንሽ ከሆነው ይበልጣል። የሺህ ቤቶች እኩል ከሆኑ የመቶ ቤቶችን እናወዳድራለን። የመቶ ቤት ትልቅ የሆነዉ ከመቶ ቤት ትንሽ ከሆነዉ ይበልጣል። የመቶ ቤቶችም እኩል ከሆኑ የአስር ቤቶችን እናወዳድራለን። የአስር ቤት ትልቅ የሆነዉ ከአስር ቤት ትንሽ ከሆነዉ ይበልጣል። የመቶ እና የአስር ቤቶች እኩል ከሆኑ የአንድ ቤቶች እናወዳድራለን። የአንድ ቤት ትልቅ የሆነዉ ከአንድ ቤት ትንሽ ከሆነዉ ይበልጣል። ባለ አምስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ስናወዳደራቸው የቁጥሮችን ሆሄያት በቤት በቤታቸው ከግራ ጀምሮ በማወዳደር ይሆናል።፡

ምሳሌ 1.6

1. 8435 > 926 ምክንያቱም የ8435 የሆሄያት ብዛት 4 ስለሆኑ እና የ926 ሆሄያት ብዛት 3 ስለሆኑ ነው።

2. የ<፣ > ወይም = ማወዳደሪያ ምልክቶችን በመጠቀም የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ።

2.1 ሀ. 44 -------- 44 ሐ. 86 -------- 37

ለ. 33 -------- 55 መ. 84 -------- 87

2.2 ሀ. 333 -------- 444 ሐ. 887 -------- 884

ለ. 286 -------- 286

2.3 ሀ. 6,570 ------ 5,570 ለ. 1,829 ------- 1,809 ሐ. 7,246 -------- 7,499

መፍትሔ፦

2.1 ሀ. 44 = 44 ምክንያቱም የአስር ቤትና የአንድ ቤት ሆሄያቸው አንድ ዓይነት ስለሆኑ።

ለ. 33 < 55 ምክንያቱም የአስር ቤት ሆሄያት 3 < 5 ስለሆነ።

ሐ. 86 > 37 ምክንያቱም የአስር ቤት ሆሄያት 8 > 3 ስለሆነ።

መ. 84 < 87 ምክንያቱም የአስር ቤት ሆሄያት አንድ ዓይነት ቢሆንም የአንድ ቤት ሆሄያት 4 < 7 ስለሆነ።

2.2 ሀ. 333 < 444 ምክንያቱም የመቶ ቤት ሆሄያት 3 < 5 ስለሆኑ።

ለ. 286 = 286 ምክንያቱም ሁሉም ተዛማጅ የቤት ዋጋዎች እኩል ስለሆኑ።

ሐ. 887 > 884 ምክንያቱም የመቶ ቤትና የአስር ቤት ሆሄያቸው አንድ ዓይነት ቢሆንም የአንድ ቤት ሆሄያት 7 > 4 ስለሆነ

2.3 ሀ. 6,570 > 5,570 ምክንያቱም የሺህ ቤት ሆሄያት 6 > 5 ስለሆነ።

ለ. 1,829 > 1,809 ምክንያቱም የሺህ ቤትና የመቶ ቤት ሆሄያቸው አንድ ዓይነት ቢሆንም የአስር ቤት ሆሄያት 2 > 0 ስለሆነ።

ሐ. 7,246 < 7,499 ምክንያቱም የሺህ ቤት ሆሄያት አንድ ዓይነት ቢሆንም የመቶ ቤት ሆሄያቸው 2< 4 ስለሆነ።

መልመጃ 1.4

1. የ<፣ > ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ ቁጥሮችን

አወዳድሩ::

ሀ. 989 ------- 984 ሐ. 1,394 ------- 1,082 ሠ. 7,315 ----- 7,315

ለ. 429 --------- 469 መ. 6,748 --------- 6,724

2. አቶ ዲቻ ገበያ ሄዶ አንድ ፍየል በ6,420 ብር ገዛ:: በተመሳሳይ ቀን ወይዘሮ ዳቦቴ ከገበያ አንድ አቻ ፍየል በ6,520 ገዛች:: ከሁለቱ ገበያተኞች ውስጥ በውድ ዋጋ የገዛው ማን ነው?
3. የጉጌ ተራራ ከፍታ 4,200 ሜትር ሲሆን ፣ የራስ ዳሽን ተራራ 4,620 ሜትር ነው:: የትኛው ተራራ በከፍታ ይበልጣል? በስንት ይበልጣል?

1.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው ማስቀመጥ

መግቢያ

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ቅደም ተከተላቸውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ አዘጋጅታችሁ በሰንጠረዥ አማካኝነት ቀዳማይና ተከታይ ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚገኙ ትማራላችሁ::

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ::

ተግባር 1.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

ሀ. የ100 ተከታይ ቁጥር ስንት ነው? ሐ. የ9999 ተከታይ ቁጥር ስንት ነው?

ለ. የ100 ቀዳማይ ቁጥር ስንት ነው? መ. የ9991 ቀዳማይ ቁጥር ስንት ነው?

ሠ. ከ300 በአንድ የሚበልጥ ቁጥር ማን ነው? ከ2000 በአንድ የሚያንስ ቁጥር ማነው?

ማስታወሻ፦

- በቁጥር መስመር ላይ በስተቀኝ ያለውን ቁጥር ለማግኘት አንድ እንደምራለን። በስተግራ ያለውን ቁጥር ለማግኘት ደግሞ አንድ እንቀንሳለን።
- በአንድ ቁጥር አንድ በመደመር የሚገኘው ድምር የቁጥሩ ተከታይ ቁጥር ይባላል። እንዲሁም ከተሰጠን ቁጥር ላይ አንድ በመቀነስ የሚገኘው ቁጥር

ምሳሌ 1.7

ሀ. የ365 ተከታይ 366 ነው። ምክንያቱም 365 + 1 = 366 ስለሆነ።

ለ. የ365 ቀዳማይ 364 ነው። ምክንያቱም 365 — 1 = 364 ስለሆነ።

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ::

   48፣ 22፣ 97፣ 33፣ 85

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ።

   1,937፣ 4,744፣ 1,604፣ 8,904፣ 3,972

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ።

   134፣ 44፣ 555፣ 51፣ 329

መፍትሔ፦

2. የእያንዳንዱን ሙሉ ቁጥር የ10 ቤት በመመልከትና በማወዳደር ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ሲጻፉ፦

   22፣ 33፣ 48፣ 85፣ 97

3. የእያንዳንዱን ሙሉ ቁጥር ከመቶ ቤት ጀምሮ በመመልከትና በማወዳደር ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ሲፃፉ፦

   1,604፣ 1,937፣ 3,972፣ 4,744፣ 8,904

4. የእያንዳንዱን ሙሉ ቁጥር ከመቶ ቤት ጀምሮ በመመልከትና በማወዳደር ከትልቅ

ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸው ሲፃፉ፦

555፣ 329፣ 134፣ 51፣ 44

መልመጃ 1.5

1. ከዚህ በታች በተገለጸው ሠንጠረዥ ውስጥ የጎደሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ::

ቀዳማይ	ሙሉ ቁጥር	ተከታይ
	7,144	
		100
	0	
999		

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ::

ሀ. 78፣ 28፣ 49፣ 95፣ 66፣ 33 ለ. 904፣ 555፣ 55፣ 801፣ 99

ሐ. 3,551፣ 8,472፣ 1,290፣ 6,287፣ 7,504፣ 2,925

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ::

ሀ. 34፣ 19፣ 86፣ 55፣ 94 ለ. 324፣ 99፣ 128፣ 33፣ 804፣ 72

ሐ. 3,000፣ 9,253፣ 1,746፣ 2,800

4. አርሶ አደር አቶ ጉጃ በዚህ ዓመት ያመረታቸውን የተለያዩ ምርቶችን የሸጡበት ዋጋ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተገልጿል::

የምርቱ ዓይነት በኩንታል	በቆሎ	ገብስ	አተር	ጤፍ	ድንች
ዋጋ (ብር)	3,000	4,785	5,500	4,800	1,300

ሀ. አቶ ጉጃ እያንዳንዱን የምርት ዓይነት ሸጠው ያገኙት የብር መጠን ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ::

ለ. አቶ ጉጃ እያንዳንዱን የምርት ዓይነት ሸጠው ያገኙት የብር መጠን ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ::

1.5 ቁጥሮችን ወደ አቅራብ አስሮች፣ መቶዎች እና ሺህዎች ማጠጋጋት

መግቢያ

የቁጥሮችን ትክክለኛ ዋጋ መጠቀም በማይቻልበት እና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት ቁጥሮችን አጠጋግቶ መጠቀም የተለመደ ተግባር ነው። በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ የቁጥሮችን አቅራብ ዋጋዎች በማጠጋጋት እንዴት መገመት እንዳለባችሁ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

ቁጥሮችን ወደ አቅራብ አስሮች፣ መቶዎች እና ሺህዎች በማጠጋጋት ታስቀምጣላችሁ።

ተግባር 1.6

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግል መልሱ።

1. የሚከተሉትን ከቅንፍ ውጭ ያሉ ቁጥሮች በቅንፍ ውስጥ ካሉት የ10 ብዜቶች ውስጥ ወደ የትኛው እንደቀርቡ ከሥር በማስመር አመልክቱ።

   ሀ. 24 (20፣ 30)　　ሐ. 162 (160፣ 170)

   ለ. 89 (80፣ 90)　　መ. 5,687 (5,680፣ 5,690)

2. የሚከተሉትን ከቅንፍ ውጭ ያሉ ቁጥሮች በቅንፍ ውስጥ ካሉት የ100 ብዜቶች ውስጥ ወደ የትኛው እንደቀርቡ ከሥር በማስመር አመልክቱ።

   ሀ. 685 (600፣ 700)　　ሐ. 986 (900፣ 1,000)

   ለ. 8,543 (8,500፣ 8,400)　　መ. 3,647 (3,600፣ 3,700)

ማስታወሻ፦

1. የአንድን ቁጥር አቅራብ ዋጋ መሆኑን ለመግለፅ የ" ≈" ምልክት እንጠቀማለን፡፡ ሲነበብም ይቀርባል ተብሎ ነው፡፡
2. የተሰጠ ቁጥርን ወደ 10 ቤት ለማጠጋጋት
   - ✓ የተሰጠው ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ ከ5 ያነሰ ከሆነ የአንድ ቤት ሆሄን ዜሮ በማድረግ ይጠጋጋል፡፡
   - ✓ የተሰጠው ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ 5 እና ከዚያ በላይ ከሆነ የ1 ቤት ሆሄ ዜሮ ማድረግ የ10 ቤት ሆሄ ላይ 1ን በመደመር ይጠጋጋል፡፡
3. የተሰጠ ቁጥርን ወደ 100 ቤት ለማጠጋጋት፡
   - ✓ የቁጥሩ የ10 ቤት ሆሄ ከ5 የሚያንስ ከሆነ የ10 እና የ1 ቤት ሆሄያት ዜሮ በማድረግ ይጠጋጋል፡፡
   - ✓ የቁጥሩ የ10 ቤት ሆሄ 5 እና ከ5 የሚበልጥ ከሆነ የ100 ቤት ሆሄ ላይ 1ን በመደመር እና የ1ና የ10 ቤት ሆሄያትን ዜሮ በማድረግ ይጠጋጋል፡፡

ምሳሌ 1.8፦

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ 10 ቤት አጠጋጉ፡፡

   ሀ. 73 ለ. 768 ሐ. 154 መ. 157

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ 100 ቤት አጠጋጉ፡፡

   ሀ. 748 ለ. 976 ሐ. 926

መፍትሔ፦

1 ሀ. 73 ≈ 70 ምክንያቱም የ73 የአንድ ቤት ሆሄ 3 ስለሆነ፡፡

ለ. 768 ≈ 770 ምክንያቱም የ768 የአንድ ቤት ሆሄ 8 ስለሆነ።

ሐ. 154 ≈ 150 ምክንያቱም የ154 የአንድ ቤት ሆሄ 4 ስለሆነ።

መ. 157 ≈ 160 ምክንያቱም የ157 የአንድ ቤት ሆሄ 7 ስለሆነ።

2 ሀ. 748 ≈ 700 ምክንያቱም የ748 የአስር ቤት ሆሄ 4 ስለሆነ።

ለ. 976 ≈ 1,000 ምክንያቱም የ976 የአስር ቤት ሆሄ 7 ስለሆነ።

ሐ. 926 ≈ 900 ምክንያቱም የ926 የአስር ቤት ሆሄ 2 ስለሆነ።

መልመጃ 1.6

1. የአቅራብ ምልክት በመጠቀም የሚከተሉትን ወደ 10 ቤት አጠጋጉ።

ሀ. 68 ለ. 299 ሐ. 364 መ. 3,486

2. የአቅራብ ምልክት በመጠቀም የሚከተሉትን ወደ 100 ቤት አጠጋጉ።

ሀ. 649 ለ. 803 ሐ. 370 መ. 9,413

3. የአቅራብ ምልክት በመጠቀም የሚከተሉትን ወደ 1,000 ቤት አጠጋጉ።

ሀ. 3,645 ሐ. 3,076 ሠ. 8,900

ለ. 3,298 መ. 9,408 ረ. 9,999

4. አቶ ፍቅሬ አንድ ፍየል በ5,234 ብር ገዝቶ ከሳምንት በኋላ በ6,174 ብር ሸጠ። አቶ ፍቅሬ ከሳምንት በኋላ የሸጡበትን የገንዘብ መጠን ወደ 1,000 ቤት አጠጋጉ።

የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

- ቁጥሮችን ለማንበብ የቁጥር ቤት ዋጋ ማወቅ ያስፈልጋል።
- ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የሚባሉት ከ0 እስከ 9 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው።
- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የሚባሉት ከ10 እስከ 99 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው። ለምሳሌ፦ 10፣ 11፣ 12፣ እያለ እስከ 99 ይቀጥላል።
- ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የሚባሉት ከ100 እስከ 999 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው። ለምሳሌ፦ 100፣ 101፣ 102፣ እያለ እስከ 999 ይቀጥላል።

- ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የሚባሉት ከ1,000 እስከ 9,999 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው። ለምሳሌ፦ 1,000፣ 1,001፣ 1,002፣ እያለ እስከ 9,999 ይቀጥላል።
- "ሀ" ከዜሮ የሚበልጥ ሙሉ ቁጥር ቢሆን $ሀ-1$ የ"ሀ" ቀዳማይ ነው።
- 0 (ዜሮ) ቀዳማይ የሌለው ሙሉ ቁጥር ነው።
- "ለ" ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ቢሆን $ለ+1$ የ"ለ" ተከታይ ነው።
- ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ለማወዳደር $<$ ፣ $>$ ወይም $=$ ምልክቶችን እንጠቀማለን።
- የሁለት እና በላይ ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት የተለየ ከሆነ ብዙ ሆሄያት ያለው ይበልጣል።
- የሁለት ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት እኩል ከሆነ የቁጥሮቹን ሆሄያት ከግራ በመጀመር በቤት በቤታቸው ማወዳደር።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ
   - ሀ. የ94 ቀዳማይ 95 ነው።
   - ለ. የ607 ተከታይ 608 ነው።
   - ሐ. $608 < 609 < 622 < 596 < 595$
   - መ. $435 > 433 > 398 > 394$
   - ሠ. 5,674 ወደ 1,000 ቤት ሲጠጋጋ 6,000 ይሆናል።
   - ረ. 749 ወደ መቶ ቤት ሲጠጋጋ 800 ይሆናል።
   - ሰ. $10,000 < 9,999$
   - ሸ. $9,452 > 9,387$
2. የ99 ተከታይ ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?
3. የትልቁ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ተከታይ ስንት ነው?
4. የትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ተከታይ ስንት ነው?
5. የትንሹ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ቀዳማይ ስንት ነው?
6. ቀዳማይ የሌለው ሙሉ ቁጥር ማን ነው?
7. በክፍት ቦታዎች ላይ $<$ ፣ $>$ ወይም $=$ ምልክቶችን በመጠቀም ቁጥሮቹን አወዳድሩ።
   ሀ. $687 - 680$ ለ. $1,000 - 9,999$ ሐ. $4,900 - 7,800$ መ. $5,014 - 5,014$
8. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቁጥሮች
   - ሀ. ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ።
   - ለ. ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተላቸው ፃፉ።

1. 49፣ 84፣ 23፣ 94፣ 56
2. 624፣ 189፣ 844፣ 409፣ 981
3. 7,402፣ 3,924፣ 8,045፣ 2,740

9. ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ውስጥ የተሰጡ ቁጥሮችን በቤት ቤታቸው ለይታችሁ ጻፉ።

ሙሉ ቁጥር	የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት
9,260				
835				
7,026				
130				
8,001				

10. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ውስጥ ያሉ የቤቶችን ብዛት በመቁጠር ከበታች ባለው በሆሄ ቤት ዋጋ ሙሉ።

1000 1000	100 100 100 100 100	10 10 10 10	1 1 1
የሺህ ቤት	የመቶ ቤት	የአስር ቤት	የአንድ ቤት

11. ከዚህ በታች በቁጥር መስመር ላይ ያሉ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።

ሀ. 0 100 200 500 900

ለ. 0 1,000 2,000 6,000 7,000 10,000

12. ከ0 እስከ 2,000 ያሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቁጥሮችን በደብተራችሁ ላይ በቅደም ተከተል ጻፉ።



2. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ

መግቢያ

የዚህ ምዕራፍ ዓቢይ ትኩረት እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ ሲሆን ይህንኑ ከግብ ለማድረስ ሶስት ንዑስ ምዕራፎችን በዋናነት የሚሸፈኑ ይሆናሉ። እነርሱም፦ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፣ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ እና እስከ 10,000 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ የሚያካትቱ ነባራዊ የኑሮ ሁኔታ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ።
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትቀንሳላችሁ።
- የሙሉ ቁጥሮችን መደመር ጽንሰ-ሀሳብን ለነባራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ትተገብራላችሁ።

2.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ በመጀመሪያ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቃል መደመር፣ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ጋር መደመር፣ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ

ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር እና እስከ 10,000 ያሉ ባለ አራት ሆሄ ሙሉ

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመርና በመቀነስ ታሰላላችሁ።

2.1.1 እስከ 10,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን በቃል መደመር

ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርን በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የ1,000 ብዜቶችን በቃል መደመርን ትማራላችሁ።

ተግባር 2.1

1. ትንሹ የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ስንት ነው?
2. እስከ 10,000 የሚደረሱ የ1,000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

ማስታወሻ፦

- ሁለት ከ10,000 የሚያንሱ የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በቃል ሲትደምሩ በሺህ ቤት የሚገኙትን ሆሄዎች ደምራችሁ በቀኝ በኩል ሶስት ዜሮዎችን መፃፍ ነው።

ምሳሌ 2.1፦

ሀ. 2,000ን እና 5,000ን በቃል ደምሩ።

መፍትሔ፦

ሀ. በ2,000 ውስጥ በሺህ ቤት የሚገኘው ሆሄ 2 ነው። በ5,000 ውስጥ በሺህ ቤት የሚገኘው ሆሄ 5 ነው። በሺህ ቤት የሚገኙ ሆሄያት ድምር 7 በመሆኑ የ2,000 እና 5,000 ድምር 7,000 ነው።

ለ. ከዚህ በታች ያሉት የመደመር ግድግዳዎች ከመሠረቱ ጀምሮ የ1,000 ብዜቶችን

በቃል እየደመሩ ወደ ላይ መውጣትን ያሳያሉ።

1)



2)



መልመጃ 2.1

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቃል ደምሩ።

   ሀ. 2,000 እና 4,000 ለ. 3,000 እና 5,000

   ሐ. 7,000 እና 2,000 መ. 4,000 እና 5,000

2. የሚከተሉትን የመደመር ግድግዳዎች በቃል በመደመር ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።



2.1.2 ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር

ተግባር 2.2

1. ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በደብተራችሁ ላይ በመፃፍ የ100 ቤት፣ የ10 ቤት እና የ1 ቤትን በማሳየት ከጓደኞቻችሁ ተወያዩ።
2. የባለ ሶስት ሆሄ ትልቁ ሙሉ ቁጥር እና የባለ ሁለት ሆሄ ትልቁ ሙሉ ቁጥር ድምር ስንት ነው?

ማስታወሻ

- ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ወደ ጎን ወይም ቁልቁል መደመር ይቻላል። አደማመሩም ከአንድ ቤት በመጀመር ሆሄዎችን መደመር። ከዚያም በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ አለኝ የሚባለውን ቁጥር ከሚቀጥለው ትልቁ ቁጥር ቤት ጋር መደመር።

ምሳሌ 2.2፦

1. የሚከተሉትን ወደ ጎን ደምሩ።

ሀ. 624 + 62 ለ. 407 + 69

2. የሚከተሉትን ወደ ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 724 \\ +\ 40 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 394 \\ +\ 58 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 290 \\ +\ 19 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

1 ሀ. 624 + 62 = 600 + 20 + 4 + 60 + 2

= 600 + 20 + 60 + 4 + 2

= 600 + 80 + 6

= 686

1 ለ. 407 + 69 = 400 + 0 + 7 + 60 + 9

= 400 + 60 + 7 + 9

= 400 + 60 + 16

= 400 + 60 + 10 + 6

= 400 + 70 + 6

= 476

2 ሀ. $\begin{array}{r} 724 \\ +\ 40 \\ \hline 764 \end{array}$ (ያለ አለኝታ ተደምሯል) 2 ለ. $\begin{array}{r} 394 \\ +\ 58 \\ \hline 452 \end{array}$ (በአለኝታ ተደምሯል)

ሐ. $\begin{array}{r} 290 \\ +\ 19 \\ \hline 309 \end{array}$ (በአለኝታ ተደምሯል)

መልመጃ 2.2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ደምሩ።

ሀ. 643 + 15 ለ. 389 + 34 ሐ. 783 + 46

2. የሚከተሉትን ወደ ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 495 \\ +\ 24 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 459 \\ +\ 67 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 505 \\ +\ 46 \\ \hline \end{array}$

1. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ።

ሀ	ለ	ሀ + ለ
999	99	
763	24	
777	48	

2. አንድ ትምህርት ቤት በግቢው ውስጥ የሚገኘውን ሣር በመሸጥ 5,240 ብር አገኘ። እንዲሁም የትምህርት ቤቱ የተፈጥሮ ሳይንስ ክበብ ካፈላው ከጓሮ አትክልት በመሸጥ ያገኘው 4,194 ብር ነው። ትምህርት ቤቱ ከሣርና ከጓሮ አትክልት ችግኝ ሽያጭ ያገኘው ብር በጠቅላላ ስንት ነው?

2.1.3 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር

ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመርን ከዚህ በፊት በነበረው ርዕስ ተምራችኋል። ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር በተመሳሳይ መንገድ ይሰራል።

ተግባር 2.3

1. ትልቁ ባለ ሶስት ሆሄና ትንሹ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ሲደመሩ ስንት ይሆናል? ከጓደኞቻችሁ ጋር በክፍል ውስጥ ተወያዩ።

ምሳሌ 2.3፦

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ደምሩ።

ሀ. 4,567 + 124 ለ. 6,734 + 583

2. የሚከተሉትን ወደ ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 6{,}132 \\ +\ 235 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 9{,}437 \\ +\ 113 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

1 ሀ. 4,567 + 124 = 4,500 + 60 + 7 + 100 + 20 + 4

= 4,500 + 100 + 60 + 20 + 7 + 4

= 4,600 + 80 + 10 + 1

= 4,600 + 90 + 1

= 4,691

1 ለ. 6,734 + 583 = 6,700 + 30 + 4 + 500 + 80 + 3

= 6,700 + 500 + 30 + 80 + 4 + 3

= 7,200 + 110 + 7

= 7,200 + 100 + 10 + 7

= 7,300 + 10 + 7 = 7,317

2ሀ. $\begin{array}{r} 6,132 \\ +\ 235 \\ \hline 6,367 \end{array}$ (ያለ አለኽታ ተደምሯል)

2ለ. $\begin{array}{r} 9,437 \\ +\ 113 \\ \hline 9,550 \end{array}$ (በአለኽታ ተደምሯል)

መልመጃ 2.3

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ደምሩ።

ሀ. 5,184 + 306 ለ. 4,612 + 320 ሐ. 7,567 + 524 መ.7,499 +783

2. የሚከተሉትን ወደ ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 3,863 \\ +\ 138 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 7,880 \\ +\ 512 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 7,089 \\ +\ 657 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 4,583 \\ +\ 702 \\ \hline \end{array}$

3. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ።

ሀ	ለ	ሀ + ለ
2,654	942	
1,019	403	
7,999	392	

2.1.4 እስከ 10,000 ያሉ ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር መደመር

ተግባር 2.4

1. የትልቁ ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ቀዳማይና ተከታይ ሙሉ ቁጥሮችን በደብተራችሁ ላይ በመፃፍ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

ማስታወሻ፦

- ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታ ስትደምሩ ቁጥሮችን በቤት ቤታቸው መደመር ተገቢ ነው። በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን ሆሄዎች መደመር፣ ቀጥሎ በ10 ቤት፣በ100 ቤት እና በ1,000 ቤት ያሉ ሆሄዎች ይደመራሉ። በየደረጃው አለኝ የሚንለውን በሚቀጥለው ትልቁ ቁጥር ቤት ካሉት ሆሄዎች ጋር መደመር።

ምሳሌ 2.4፦

1. የሚከተሉትን ደምሩ።

ሀ. 4,563 + 3,405 ለ. 3,654 + 1,963

መፍትሔ፦

ሀ. $\begin{array}{r} 4,563 \\ +\ 3,405 \\ \hline 7,968 \end{array}$ (ያለ አለኝታ ተደምሯል)

ለ. $\begin{array}{r} 3,654 \\ +\ 1,963 \\ \hline 5,617 \end{array}$ (በአለኝታ ተደምሯል)

መልመጃ 2.4

1. የሚከተሉትን ደምሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 3,534 \\ +\ 2,343 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 7,111 \\ +\ 2,663 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 3,025 \\ +\ 2,340 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 3,267 \\ +\ 6,102 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 6,064 \\ +\ 3,852 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 1,526 \\ +\ 7,878 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 3,213 \\ +\ 4,648 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 6,590 \\ +\ 2,296 \\ \hline \end{array}$

2. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ።

ሀ	ለ	ሀ + ለ
5,024	2,929	
2,892	4,844	
3,566	2,653	
2,534	3,637	

2.2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

መግቢያ

ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ማቀናነስ፣ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች እንዴት መቀነስ እንደሚትችሉ መረዳት እና በተመሳሳይ መልኩ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት እና ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ እንዴት መቀነስ እንደሚሰራ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመርና በመቀነስ ታሰላላችሁ።

2.2.1 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ መበደር መቀነስ

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ስለመቀነስ በተማራችሁት መሠረት በማድረግ ከባለ ሶስት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር መቀነስን ከዚህ ቀጥሎ ትማራላችሁ።

ተግባር 2.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን መፍትሔ ፈልጉ።

1. ወይዘሮ ማዳረ ለልጇ ሠርግ መስተንግዶ የሚሆን 570 ብርጭቆዎችን ከቀበሌው እድር ቤት ተውሳለች። ከዚህ ውስጥ 40 ብርጭቆዎች ቢሰበሩ ስንት ብርጭቆዎች ይቀራሉ?

ማስታወሻ፦

- ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ መበደር መቀነስ በሁለት መንገድ ሊሰራ ይችላል።

1. አንደኛው አሰራር ቁጥሮችን ተንትኖ መቀነስ ስሆን
2. ሁለተኛው አሰራር ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ጽፎ ሆሄያትን በየቤታቸው መቀነስ ነው።

ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ሆነው፤ ሀ > ለ ቢሆን ሀ - ለ = መ በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ "ሀ" ዋና፣ "ለ" ተቀናሽ እና "መ" ልዩነት ይባላል።

ምሳሌ 2.5፦

1. ሀ. 367 — 21 = 346 በዚህ ስሌት ውስጥ 367 ዋና፣21 ተቀናሽ እና 346 ልዩነት ነው።

ለ. 699 — 47 = 652 በዚህ ስሌት ውስጥ 699 ዋና፣47 ተቀናሽ እና 652 ልዩነት

2. የተሰጡትን ቁጥሮች በመተንተንና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ የሚከተሉትን ቀንሱ

ሀ. 486 — 53 ለ. 846 — 23

መፍትሔ፦

1. ቁጥሮችን በመተንተን መቀነስ

ሀ. 486 — 53 = 400 + 80 + 6 — (50 + 3)

= 400 + (80 — 50) + (6 — 3)

= 400 + 30 + 3

= 433

ለ. 846 — 23 = 800 + 40 + 6 — (20 +3)

= 800 + (40 — 20) + (6- 3)

= 800 + 20 + 3

= 823

2. ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው በመፃፍ ሲሰላ በሚከተለው መንገድ ይሆናል።

ሀ. $\begin{array}{r} 486 \\ -\ 53 \\ \hline 433 \end{array}$ መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 6 -3 = 3 እና ውጤቱን “3” በአንድ ቤት ስር መፃፍ፤ ቀጥሎ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 8 — 5 = 3፤ ከዚያም ውጤቱን “3” በአስር ቤት ስር መፃፍ፤ በመቶ ቤት ያለውን ሆሄ “4” እንዳለ በመቶ ቤት ስር መፃፍ፤

ስለዚህ $\begin{array}{r} 486 \\ -\ 53 \\ \hline 433 \end{array}$ ይሆናል።

ለ. $\begin{array}{r} 846 \\ -\ 23 \\ \hline 823 \end{array}$ መጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 6 -3 = 3 እና ውጤቱን “3” በአንድ ቤት ስር መፃፍ፤ ቀጥሎ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 4 — 2 = 2፤ ከዚያም ውጤቱን “2” በአስር ቤት ስር መፃፍ፤ በመጨረሻ በመቶ ቤት ያለውን ሆሄ “8” እንዳለ በመቶ ቤት ስር መፃፍ፤

ስለዚህ $\begin{array}{r} 846 \\ -\ 23 \\ \hline 823 \end{array}$

መልመጃ 2.5

1. የሚከተሉትን ቀንሱ።

ሀ. 484—61 ለ. 698—54 ሐ. 578—78

መ. 483—62 ሠ. 852—40 ረ. 667—47

ሰ. $\begin{array}{r} 965 \\ -\ 44 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 768 \\ -\ 54 \\ \hline \end{array}$ ቀ. $\begin{array}{r} 688 \\ -\ 35 \\ \hline \end{array}$

3. ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ከ"ሀ" "ለ"ን በመቀነስ ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሀ	ለ	ሀ - ለ
184	63	
649	30	
896	74	
280	70	

2.2.2 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በመበደር መቀነስ

ተግባር 2.6

1. በኩሉፎ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በፀረ ኤች እይ ቪ ኤድስ ክበብ ውስጥ በአባልነት የተመዘገቡ ተማሪዎች 256 ቢሆኑና ከተመዘገቡት ውስጥ 18ቱ ወደ ሌላ ክበብ ለቀው ቢሄዱ ስንት ተማሪዎች በክበቡ ውስጥ ይቀራሉ? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

ማስታወሻ፦

- የመቀነስ ስሌትን ቁልቁል ስናሰላ ከአንድ ቤት ጀምረን እንቀንሳለን። የሚቀነሰው ሆሄ ከዋናው ሆሄ ያነሰ ከሆነ ከቀጣዩ ቤት አስር ወስዶ በዋናው ሆሄ ላይ በመደመር እና ከዚያም በመቀጠል ተቀናሽ ሆሄውን በመቀነስ ይፃፋል።

ምሳሌ 2.6፦

የሚከተሉትን ቀንሱ።

ሀ. 963 — 47 ለ. $\begin{array}{r} 614 \\ -96 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦ ሀ. $\begin{array}{r} 963 \\ -\ 47 \\ \hline 916 \end{array}$

በመጀመሪያ ቁልቁል መፃፍ፤

3 < 7 ስለሆነ ከ10 ቤት አስርን ወስዶ ከ3 ጋር መደመር፤

ይህም 10 + 3 = 13 ነው። በመቀጠል ከ13 ላይ 7ን መቀነስ፤

ይህም 13 — 7 = 6 ነው።ውጤቱን "6"ን አንድ ቤት ስር መፃፍ።

ከዋናው በ10 ቤት የቀረን 5 ነው።

ስለዚህ 5 > 4 ስለሆነ ቀጥታ 5 — 4 = 1 ነው።

ውጤቱን "1"ን በ10 ቤት ስር መፃፍ ፤

ዋናው በመቶ ቤት ያለው ሆሄ 9 ስለሆነ "9"ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ።

ለ. $\begin{array}{r} 614 \\ -96 \\ \hline 518 \end{array}$ 4 < 6 ስለሆነ ከ10 ቤት አስርን ወስዶ ከ4 ጋር መደመር፣

ይህም 10 + 4 = 14 ነው። በመቀጠል ከ14 ላይ 6ን መቀነስ፤

ይህም 14 — 6 = 8 ነው። ውጤቱን “8”ን አንድ ቤት ስር መፃፍ።

ከዋናው በ10 ቤት የቀረን 0 ነው።

ስለዚህ 0 < 9 ስለሆነ ከ100 ቤት አስርን ወስዶ ከ0 ጋር መደመር፣

ይህም 10 + 0 = 10 ነው። በመቀጠል ከ10 ላይ 9ን መቀነስ፣

ይህም 10 — 9 = 1 ነው። ውጤቱን “1”ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤

ዋናው በመቶ ቤት የቀረን 5 ነው። ስለሆነም “5”ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ።

መልመጃ 2.6

1. የሚከተሉትን ቀንሱ::

ሀ. 450 — 41 ለ. 320 — 50 ሐ. 855 — 76

መ. 633 — 52 ሠ. 976 — 81 ረ. 705 — 76

ሰ. $\begin{array}{r} 750 \\ -53 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 765 \\ -58 \\ \hline \end{array}$ ቀ. $\begin{array}{r} 534 \\ -67 \\ \hline \end{array}$

2. ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ከዋናው ተቀናሹን በመቀነስ ባዶ ቦታውን ሙሉ::

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
725	65	
670	80	
618	29	
282	79	

2.2.3 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

ከላይ ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ተማራችኋል። አሁን ደግሞ ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስን ትማራላችሁ።



የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ።

1. ከ764 ላይ 347 ብቀነስ መልሱ ስንት ይሆናል?
2. በደቡብ ክልል ውስጥ ከ674 በኤች አይ ቪ ኢድስ ከተያዙ ሰዎች 252 ቢሞቱ በዚህ ክልል በኤች አይ ቪ ኢድስ ተይዘው በሕይወት ያሉ የሰዎች ቁጥር ስንት ነው?

ማስታወሻ፦

- ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥርን ላይ ስትቀንሱ ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ጽፎ በቤት ቤታቸው በመቀነስ ነው።
- ባለ ሶስት ሆሄን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ የሚቀነሰው ዋናው ከተቀናሹ ሲበልጥ ነው። ውጤቱም ሁልጊዜ ሙሉ ቁጥር ነው።
- አንድ ሙሉ ቁጥር ከሌላው ሙሉ ቁጥር በስንት እንደሚበልጥ ወይም

ምሳሌ 2.7፦

1. የ354 እና 217 ልዩነት ስንት ነው?

2. 638 ከ346 በስንት ይበልጣል?

3. ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ከዋናው ተቀናሹን በመቀነስ ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
762	526	
300	104	
854	396	

መፍትሔ፦

1. $\begin{array}{r} 354 \\ -\ 217 \\ \hline 137 \end{array}$ ስለዚህ የ354 እና 217 ልዩነቱ 137 ነው።

2. $\begin{array}{r} 638 \\ -\ 346 \\ \hline 292 \end{array}$ ስለዚህ 638 ከ346 በ292 ይበልጣል።

3. በሠንጠረዡ ላይ የጎደለውን ክፍት ቦታ ለመሙላት ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ቤታቸው ቁልቁል በመፃፍ ቀጥሎም በመቀነስ ነው።

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
762	526	236
300	104	196
854	396	458

መልመጃ 2.7

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 527—227 ለ. 646—312 ሐ. 887—489

መ. 753—368 ሠ. 604—377 ረ. 800—724

2. ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ከዋናው ተቀናሹን በመቀነስ ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
634	476	
573	569	
924	857	

2.2.4 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

መግቢያ

ባለ ሶስት ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ ከዚህ በፊት ተምራችኋል። አሁን ግን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ በተመሳሳይ መንገድ ትማራላችሁ።

ተግባር 2.8

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 3,654 — 654 ለ. 8,574 — 986

2. ዋናው 1,657 እና ተቀናሹ 269 ቢሆን ልዩነቱ ስንት ይሆናል?

ማስታወሻ፦

- ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ስንቀንስ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመጻፍ በመጀመሪያ በ1 ቤት ያሉትን፣ ቀጥሎ በ10 ቤት ያሉትን ከዚያም በ100 ቤት ያሉትን በመቀነስ ነው። በየቤቱ ያሉ የላይኛው ቁጥር ሆሄያት በታችኛው ካሉት የሚያንሱ ከሆነ ከዚህ በፊት የተጠቀምናቸውን በመበደር የመቀነስ

ምሳሌ 2.8፦

የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 7,864 — 864 ለ. $\begin{array}{r} 6,342 \\ -\ 396 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

ሀ.
$$\begin{array}{r} 7{,}864 \\ -\ 864 \\ \hline 7{,}000 \end{array}$$

ለ.
$$\begin{array}{r} 6{,}342 \\ -\ 396 \\ \hline 5{,}946 \end{array}$$

መልመጃ 2.8

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 2,645—342 ለ. 4,785—607

ሐ. 7,104 — 846 መ. 7,184 — 885

2. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሠንጠረዥ ከዋና ተቀናሹን በመቀነስ ሙሉ።

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
9,674	712	
8,400	125	
1,763	548	

2.2.5 ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ

መግቢያ

ባለ ሶስት ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ መቀነስ ከዚህ በፊት ተምራችኋል። ይህንን እውቀታችሁን ተጠቅማችሁ ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ላይ መቀነስን ትማራላችሁ።

ተግባር 2.9

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር ስሩ።

ሀ. የ4,000 እና የ3,000 ልዩነት ስንት ነው?

ለ. 4,520 ከ3,800 በስንት ይበለጣል?

ማስተወሻ፦

- ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ የመቀነስ አሰራር ዘዴ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመጻፍ በቤት በቤታቸው ከዚህ በፊት በተጠቀምናቸው የአሰራር ዘዴ በመቀነስ ይሆናል። ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥርን ከባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ላይ ለመቀነስ ዋናው ከተቀናሹ መብለጥ ይኖርበታል። ልዩነቱንም ሁልጊዜ ሙሉ ቁጥር ይሆናል።

ምሳሌ 2.9፦

የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 6,534 — 4,213 ለ. $\begin{array}{r} 8,243 \\ -\ 6,478 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

ሀ. $\begin{array}{r} 6,534 \\ -\ 4,213 \\ \hline 2,321 \end{array}$

በመጀመሪያ ቁልቁል መፃፍ

4 > 3 ስለሆነ 4 — 3 = 1 ነው። ውጤቱን “1”ን አንድ ቤት ስር መፃፍ።

3 > 1 ስለሆነ 3 — 1 = 2 ነው። ውጤቱን “2”ን አስር ቤት ስር መፃፍ።

5 > 2 ስለሆነ 5 — 2 = 3 ነው። ውጤቱን “3”ን መቶ ቤት ስር መፃፍ።

6 > 4 ስለሆነ 6—4 = 2 ነው። ውጤቱን “2”ን ሺህ ቤት ስር መፃፍ።

ለ.
$$\begin{array}{r} 8,243 \\ -\ 6,478 \\ \hline 1,765 \end{array}$$

3 < 8 ስለሆነ ከ10 ቤት አስርን ወስዶ ከ3 ጋር መደመር፣

ይህም 10 + 3 = 13 ነው። ይህም 13 — 8 = 5 ነው።

ውጤቱን “5”ን አንድ ቤት ስር መፃፍ።

ከዋናው በ10 ቤት የቀረን 3 ነው።

ስለዚህ 3 < 7 ስለሆነ ከ100 ቤት አስርን ወስዶ ከ3 ጋር መደመር፣

ይህም 10 + 3 = 13 ነው።

በመቀጠል ከ13 ላይ 7ን መቀነስ፣

ይህም 13 — 7 = 6 ነው። ውጤቱን “6”ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤

ከዋናው በመቶ ቤት የቀረን 1 ነው።

1 < 4 ስለሆነ ከሺህ ቤት 10ን ወስዶ ከ1 ጋር መደመር።

ይህም 10+1 = 11 ነው።

በመቀጠል 11 ላይ 4ን መቀነስ። ይህም 11 — 4 = 7 ነው።

ውጤቱን “7”ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ።

7 > 6 ስለሆነ 7 — 6 = 1 ነው።

ውጤቱን “1”ን ሺህ ቤት ስር መፃፍ።

መልመጃ 2.9

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 2,564 — 1,764	ለ. 9,073 — 8,173	ሐ. 3,500 — 2,645
መ. 8,006 — 3,217	ሠ. 6,453 — 4,368	ረ. 4,500 — 3,900

2. ዋናው 7,534፣ ተቀናሹ 3,687 ቢሆን ልዩነቱ ስንት ይሆናል?

3. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሠንጠረዥ ከዋና ተቀናሹን ሙሉ።

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
6,400	2,400	
5,371	1,646	
7,568	4,599	

2.3 መደመርና መቀነስን የያዙ ነባራዊ የኑሮ ሁኔታዎች ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞች

መግቢያ

ባለፉት ንዑስ ምዕራፎች ላይ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር ተምራችኋል። ይህን እውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በመደመር ሊሰሩ የሚችሉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሙሉ ቁጥሮችን በመጠቀም ነባራዊ ኑሮ ሁኔታዎችን ትፈታላችሁ።

2.3.1 መደመርን የያዙ ነባራዊ የኑሮ ሁኔታዎችን ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞች

ተግባር 2.10

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር ስሩ።

1. አርባ ምንጭ ሙሉ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአካል ጉዳተኞች ክበብ 7,650 ብር እና ለሴት ተማሪዎች መማክርት 2,300 ብር መድቦ ሰጠ። ትምህርት ቤቱ በአጠቃላይ የሰጠው ብር ስንት ነው?
2. ተማሪ አይናቱ ከትምህርት ቤቷ ካሉ አጠቃላይ ተማሪዎች 1ኛ በመውጣቷ ትምህርት ቤቱ 1,500 ብር፤ ወላጆቿ ደግሞ 300 ብር ሸልሟታል። ተማሪ አይናቱ የተሸለመችው ጠቅላላ ብር ስንት ነው?

ማስተወሻ፦

- የቃላት ፕሮብሌሞች ለመፍታት ወይም መፍትሔ ለማግኘት የሚከተሉትን የአሰራር ደረጃዎች መከተል ያስፈልጋል።

ምሳሌ 2.10፦

ወይዘሮ ባሎቴ ባሳ ሁለት ልጆች አሏት። ሁለቱም ከጫዋታ መልስ እጃቸውን ሳይታጠቡ ምግብ ይመገባሉ። በመሆኑም አንዳኛው ልጅ ትውከትና ተቅማጥ ታሞ በ347 ብር ታከመ። ሁለተኛዋ ልጅ የሆድ ቁርጠት ታማ በ480 ብር ታክማለች። ወይዘሮ ባሎቴ ባሳ በጠቅላላ ለህክምና ያወጣችው ስንት ብር ነው?

መፍትሔ፦

ለትውከትና ተቅማጥ ህክምና የወጣ ብር 347 ነው። ለሆድ ቁርጠት ህክምና የወጣ 480 ነው። ጠቅላላ ለሕክምና የወጣው ብር የሁለቱ ድምር ይሆናል።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 347 \\ +\ 480 \\ \hline 827 \end{array}$

መልመጃ 2.10

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞችን አንብባችሁ መፍትሔ ስጡ።

1. አቶ ግሮጫ ማጋና ሕፃናትን በሕገወጥ መንገድ ሲያዛውር በፖሊስ ተይዞ 5,000 ብር ተቀጣ። በተጨማሪም ግለሰቡ በተያዘበት ወቅት በኪሱ አደገኛ እፆች በመገኘታቸው 4,500 ብር ተቀጣ። በጠቅላላ አቶ ግሮጫ ስንት ብር በሕግ ተቀጣ?
2. በመስከረም ወር የማዜ ብሔራዊ ፓርክ ለመጎበኘት የመጡ የውጪ አገር ጎበኝዎች ያስገቡት ገቢ 6,741 ብር ነው። በተመሳሳይ ወር አርባ ምንጭ ነጭ ሣር ብሔራዊ

ፓርክ ለመጎብኘት የመጡ የአገር ውስጥ ጎበኝዎች ያስገቡት ገቢ 2,052 ብር ነው። በጠቅላላ ሁለቱ የደቡብ ክልል ብሔራዊ ፓርኮች በመስከረም ወር ያስገቡት ገቢ ስንት ነው?

3. ወይዘሮ ካርሞቴ እና ባለቤቱ አቶ ገዛኸኝ ከኮንሶ ማህበረሰብ የታወቁ ለወጣቶች ሥራ ፈጣሪዎች ናቸው። በመሆኑም ይህ ቤተሰብ በወር ለእህል ሻጪዎች 3,250 እና ለጥበቃ ሠራተኞች ክፍያ 4,850 ብር ቢከፍሉ በአጠቃላይ በወር ለእነዚህ ለሁለት ሥራ መስኮች ስንት ብር ያወጣሉ?
4. የኢትዮጵያ የፓራ ኦሎምፕክ ተወዳዳሪው አትሌት ታምሩ ደምሴ በብራዚል በተካሄደው የፓራ ኦሎምፕክ ውድድር በ1,500 ሜትር ሩጫ የብር መዳሊያ በማግኘቱ የተደሰተው የጂንካ ዞን አስተዳደር 8,250 ብር ቢሰጥና በሽልማቱ ስነ-ሥርዓት ላይ የተሳተፉት በዞኑ ታዋቂ የአገር ሽማግሌ አቶ በቀለ 1,500 ብር ቢጨምሩበት አትሌቱ በጠቅላላው ስንት ብር ተሸለመ?
5. አንድ አርሶ አደር የሚታለቡ ሰባት ምርጥ የወተት ላሞች ነበሩት። በመጀመሪያው ወር 3,360 ሊትር ወተት ለገበያ አቀረበ። በሁለተኛው ወርም ተመሳሳይ ሊትር ለገበያ አቀረበ። በሁለቱ ተከታታይ ወራት ስንር ሊትር ወተት ለገበያ አቅርቧል።
6. ጠንካራ አርሶ አደር ወይዘሮ ሎላሼ ሎጎ ሁለት ኩንታል በርበሬ አምርታ በመሸጥ 2,850 ብር አገኘች። በቀጣዩ ዓመት ደግሞ አምስት ኩንታል በርበሬ አምርታ በመሸጥ 6,225 ብር አገኘች። ወይዘሮ ሎላሼ ሎጎ በሁለቱ ዓመት ስንት ብር ከበርበሬ አገኘች?

2.3.2 መቀነስን የያዙ ነባራዊ የኑሮ ሁኔታዎችን ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞች መግቢያ

ባለፉት ሁለት ምዕራፎች እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ ተምራችኋል። ይህን እውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በመቀነስ ሊሰሩ የሚችሉ የቃላት ፕሮብለሞችን ትፈታላችሁ።



የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ስሩ።

1. በአንድ ትምህርት ቤት ወገን ለወገን ደራሽ ክበብ ውስጥ የነበሩ የክብቡ አባላት የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማስተባበር 6,450 ብር ሰበሰቡ። ክበቡ ካገኘው ብር ለተቸገሩ ሃያ ተማሪዎች 6,440 ብር አውጥቶ ለደብተር መግዣ አከፋፈሉ። በክበቡ እጅ የሚቀረው ብር ስንት ነው?
2. አንድ አንጆ ኑስ የሚባል የዶሮ አርቢዎች ማህበር ካሏቸው 8,396 ዶሮዎች ውስጥ 85 አውራ ዶሮዎችን ለእንቁጣጣሽ ገበያ አውጥተው ቢሸጡ ምን ያህል ዶሮዎች ለማህበሩ ይቀራሉ?

ምሳሌ 2.11፦

1. የአንድ ወረዳ ታዋቂ አርቲስት ለአገር መከላከያ ሠራዊት ድጋፍ የሚሆን 9,550 ብር ለመስጠት ቃል ገባ። በቃሉ መሠረት በግንቦት ወር 6,200 ብር ሰጠ። አርቲስቱ ቃል ከገባው ብር ውስጥ ቀሪው ብር ስንት ነው?
2. አንድ የሱቅ ባለበት ከአንድ እንቁላል ነጋዴ 6,240 እንቁላሎችን ገዛ። ከተገዙት እንቁላሎች 294 የተበላሹ ሆነው ተገኙ። ያልተበላሹ እንቁላሎች ብዛት ስንት ነው?

መፍትሔ፦

1. አርቲስቱ ቃል የገባው 9,550 ብር ለመስጠት ነው። አርቲስቱ በመጀመሪያ ዙር የሰጠው 6,200 ብር ነው። የሚፈለገው በአርቲስቱ ላይ የቀረው ብር ነው። ቀሪው

ብር እርሱ ቃል ከገባው ብር አሁን የሰጠውን ብር ስቀነስ ይሆናል።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 9,550 \\ -\ 6,200 \\ \hline 3,350 \end{array}$

2. ነጋዴው መጀመሪያ የገዛው እንቁላል 6,240 ነው። ከተገዙት ውስጥ የተበላሹት እንቁላሎች 294 ነው። የሚፈለገው ያልተበላሹ እንቁላሎች ብዛት ነው። ቀሪ ያልተበላሹ እንቁላሎች አጠቃላይ ነጋዴው የገዛው እንቁላል እና አሁን የተበላሹ እንቁላሎች ልዩነት ይሆናል።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 6,240 \\ -\ 294 \\ \hline 5,946 \end{array}$

መልመጃ 2.11

ለሚከተሉት ለቃላት ፕሮ ብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ።

1. አንድ የቀበሌ ልማት እድር በቀበሌው ላሉ አረጋዊያን መጦሪያ ቤት ለመስራት አባላቱን በማስተባበር 9,587 አዋጡ። ከዚህ ገንዘብ ሰላሳ አንድ ቆርቆሮዎችን 9,300 ብር ወጪ አድርገው ቢገዙ ቀሪው ብር ስንት ይሆናል?
2. አቶ ክፍሉ 7,695 ብር እና ወይዘሮ ባታሌ ደግሞ 5,389 ብር አላቸው። የአቶ ክፍሉ ብር ከወይዘሮ ባታሌ ብር በስንት ይበልጣል?
3. በአንድ ወረዳ ውስጥ በመንግስት ትምህርት ቤት 8,950 ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች አሉ። ደግሞ በግል ትምህርት ቤት 5,320 ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ቢኖሩ፤ በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት ስንት ነው?

4. የትዕግስት አባት 4,335 ብር ይዘው ወደ ገበያ ሄዱ። በ2,560 ብር ለልጆቻቸው ጫማ፣ ሱሪ እና ሸሚዝ ገዝተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። የትዕግስት አባት ወደ ቤት ስንት ብር ይዘው ተመለሱ?
5. በአንድ ወረዳ ካሉ ቀበሌያት ውስጥ አንድ ቀበሌ የሚኖሩ ወጣቶች ብዛት 8,986 ነው። ከእነዚህ ውስጥ ደፋሪና ጀግና የነበሩ 786 ወጣቶች የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር ቢሄዱ በቀበሌው ውስጥ ስንት ወጣቶች ይቀራሉ?
6. ዋናው 3,654 ቢሆን ተቀናሹ ደግሞ 2,654 ቢሆን ልዩነቱ ስንት ይሆናል?

የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- ሁለት የ1,000 ብዜቶችን በቃል ለመደመር በሺህ ቤት የሚገኙ ሆሄዎችን ደምሮ ከውጤቱ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መፃፍ።
- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታና በአለኝታ መደመር ይቻላል። የአደማመር ስልት ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ሆሄያትን በየቤታቸው መደመር ነው። በመጀመሪያ በ1 ቤት ያሉትን፣ ቀጥሎ በ10 ቤት ያሉትን እየደመሩ በየቤቱ ስር መፃፍ። ድምሩ ያለ አለኝታ ድምር በሚሆንበት ጊዜ በ100 ቤት የሚገኘውን ሆሄ እንዳለ በቤቱ ስር መፃፍ። በአለኝታ በሚደመርበት ጊዜ ከአንድ ቤት በመጀመር በየቤቱ የሚገኙትን ደምሮ “አለኝታ” የሚባለውን ከሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄዎች ጋር መደመር።
- ከባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ለመቀነስ ልክ እንደ መደመሩ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል መፃፍ። ከዚያም በቤት በቤታቸው መቀነስና ውጤቱን በየቤቱ ስር መፃፍ፤ ያም በመበደር ወይም ያለ መበደር ሊሆን ይችላል።
- ባለ ሶስት ሆሄን ከባለ ሶስት ሆሄ ስትቀንሱ ሁልጊዜ ዋናው ከተቀናሹ መብለጥ ይኖርበታል። ባለ አራት ሆሄ ከባለ አራት ሆሄ በተመሳሳይ መልኩ ይቀነሳል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ደምሩ::

ሀ. 689 + 69

ለ. 6,345 + 25

ሐ. 5,187 + 438

መ. $\begin{array}{r} 7{,}964 \\ +\ 452 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 4{,}716 \\ +\ 3{,}549 \\ \hline \end{array}$

ረ. $\begin{array}{r} 2{,}356 \\ +\ 6{,}104 \\ \hline \end{array}$

2. የሚከተሉትን ቀንሱ::

ሀ. 574 - 62

ለ. 318 - 49

ሐ. 836 - 75

መ. 382 — 261

ሠ. $\begin{array}{r} 458 \\ -\ 368 \\ \hline \end{array}$

ረ. $\begin{array}{r} 588 \\ -\ 398 \\ \hline \end{array}$

ሰ. $\begin{array}{r} 7{,}845 \\ -\ 2.613 \\ \hline \end{array}$

ሸ. $\begin{array}{r} 8{,}645 \\ -\ 3{,}776 \\ \hline \end{array}$

3. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሙሉ::

ሀ.

መ	ሠ	መ + ሠ
8,001	1,023	
3,188	5,449	
4,991	2,489	

ለ.

ዋና	ተቀናሽ	ልዩነት
3,627	3,566	
7,643	3,752	
9,741	3,895	

4. አንድ የሸማቾች ማህበር 8,500 ብር ይዞ ወደ ገበያ ወጣ። በ4,000 ብር አንድ ኩንታል ዱቀት እና በ2,400 ብር አስር ደርዘን ሳሙና ገዝተው ተመለሱ።

ሀ. ማህበሩ በጠቅላላ ስንት ብር አወጣ?

ለ. ማህበሩ ስንት ብር ቀረው?

5. አንድ የዘይት መጭመቂያ ፋብሪካ በሁለት ተከታታይ ቀናት 5,820 ሊትር እና 3,980 ሊትር ዘይት አመረተ። በሁለት ቀናት የተመረተው ዘይት ውስጥ 7,500 ሊትር ለተለያዩ ድርጅቶች ተሰጠ። ያልተሸጠው ዘይት ስንት ሊትር ነው።

6. በደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ በሐምሌ 25 2012 ዓ/ም ጀምሮ የተከሰተው የኦሞ ወንዝ ሙላት ባስከተለው ጎርፍ ምክንያት ከተፈናቀሉ ሰዎች ውስጥ 9,385 ያህሉ አረጋዊያንና ሕፃናት ቢሆኑ እና ከተፈናቃዮቹ ውስጥ በመስከረም ወር 5,800 አረጋዊያንና ሕፃናት ቢመለሱ ወደ ቀያቸው ያልተመለሱ አረጋዊያንና ሕፃናት ስንት ናቸው?

ምዕራፍ ሶስት

3. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ እስክ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ይህንኑ በማጠናከር እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን (ብዜታቸውም ከ1,000 ያልበለጠ)፣ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች

ማባዛትን እና እስከ 1,000 ድረስ ማባዛትን የሚያካተቱ ነባራዊ የኑሮ ሁኔታ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታትን ትማራላችኋሁ።

3.1 የ10 እና የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማብዛት

መግቢያ

ከዚህ በፊት የ100 እና 1,000 ብዜቶች እስከ 10,000 ድረስ በምዕራፍ አንድ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የ100 ብዜቶችን በአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ታባዛላችሁ።

ተግባር 3.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱ።

ሀ. ከመቶ ያነሱ የ10 ብዜቶች ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ። ከ100 የሚያንሱት የ10 ብዜቶች ትልቁንና ትንሹን ለይታችሁ አሳዩ።

ለ. ከ1,000 ያነሱ የ100 ብዜቶች ሙሉ ቁጥሮችን በመዘርዘር ትንሹንና ትልቁን ለዩ።

ማስታወሻ፦

- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ዜሮ $(መ \times 0 = 0 = 0 \times መ)$ ነው። በመሆኑም ዜሮ የማንኛውም ሙሉ ቁጥር ብዜት ነው። ነገር ግን ትንሹ ብዜት ሲጠየቅ የሚንወስደው አወንታዊ የሆነውን ትንሹ ብዜት ብቻ ነው።
- የ10 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስታባዙ የሚከተለውን አሰራር ተከተሉ። ከተሰጠው የ10 ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄ ጋር አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ አንድ ዜሮን መፃፍ።
- የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስታባዙ የሚከተለውን አሰራር ተከተሉ። ከተሰጠው የ100 ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄ ጋር አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መፃፍ።

ምሳሌ 3.1፦

የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. 10×5 ለ. 10×4 ሐ. 100×5 መ. 200×4

መፍትሔ፦

ሀ. 10×5 ይህን ማባዛት ለመስራት 1ን በ5 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ አንድ ዜሮ

መግፍ ነው። ስለዚህ $1 \times 5 = 5$ ላይ ዜሮን በስተቀኝ በኩል መግፍ ነው። ፣

ይኸውም 50 ይሆናል።

ለ. 10×4 ይህን ማባዛት ለመስራት 1ን በ4 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ አንድ ዜሮ መግፍ፤ ይኸውም $1 \times 4 = 4$ ላይ በስተቀኝ በኩል ዜሮን መጻፍ ይኸውም 40 ይሆናል።

ሐ. 100×5 ይህን ለማባዛት 1ን በ5 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መግፍ ነው። ስለዚህ $1 \times 5 = 5$ ላይ ሁለት ዜሮዎችን በስተቀኝ በኩል መግፍ ነው። ይኸውም 500 ይሆናል።

መ. 200×4 ይህን ማባዛት ለመስራት 2ን በ4 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መግፍ ነው። ይኸውም $200 \times 4 = (2 \times 4) \times 100$ በመጀመሪያ ቅንፍ ውስጥ ያለውን ማባዛት ነው። ስለዚህ $8 \times 100 = 800$

በመሆኑም $200 \times 4 = 800$ ይሆናል።

ምሳሌ 3.2፦

ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ ውስጥ ያሉ ባዶ ቦታዎችን አሟሉ።

×	10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
1			30			60		80	90	
2		40	60				140			200
3	30			120	150				270	
4	40			160		240				

5			150					400		500

መፍትሔ፦

በሠንጠረዥ ላይ ያሉ ባዶ ቦታዎችን ለመሙላት ከላይ ያሉ የ10 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን ከጎን ባሉ በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር በማባዛት መልሱን ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ተገልጿል።

×	10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
1	10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
2	20	40	60	80	100	120	140	160	180	200
3	30	60	90	120	150	180	210	240	270	300
4	40	80	120	160	200	240	280	320	360	400
5	50	100	150	200	250	300	350	400	450	500

መልመጃ 3.1

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $60 \times 8 =$ — ሠ. $900 \times 5 =$ — ቀ. $8 \times 30 =$ —

ለ. $700 \times 2 =$ — ረ. $100 \times 6 =$ — በ. $9 \times 60 =$ —

ሐ. $500 \times 3 =$ — ሰ. $7 \times 600 =$ — ተ. $9 \times 400 =$ —

መ. $300 \times 4 =$ — ሸ. $8 \times 200 =$ —

2. የሚከተለውን የአብዥር ሠንጠረዥ አሟሉ።

ሀ.

×	100	200	300	400	500	600	700	800	900	1,000
1	100	200				600	700		900	
2			600	800				1,600		2000

3	300				1,500	1,800			2,700	
4		800	1,200	1,600			2,800	3,200		
5	500				2,500	3,000				5000

ለ.

×	100	200	300	400	500	600	700	800	900	1,000
6	600			2400	3,000			4,800		6,000
7		1,400	2,100			4,200	4,900		6,300	
8	800			3,200	4,000			6,400	7,200	
9		1,800	2,700			5,400	6,300			9,000

3. አንድ ልስትሮ ሠራተኛ በየቀኑ ከሚያገኘው ገቢ 30 ብር በእያንዳንዱ ቀን በቁጠባ ሳጥኑ ውስጥ ቢያስቀምጥ በሳምንት የቆጠበው ብር ስንት ይሆናል?
4. አቶ ሀሰን የጫማ መሸጫ ሱቅ አላቸው። አቶ ሀሰን አንዱን ጥንድ ጫማ በ700 ብር ይሸጣሉ። ከሰኞ እስከ ዓርብ የሸጧቸው ጥንድ ጫማዎች ብዛት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ተገልጿል።

ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዓርብ
2 ጥንድ ጫማዎች	6 ጥንድ ጫማዎች	1 ጥንድ ጫማ	42 ጥንድ ጫማዎች	1 ጥንድ ጫማ

ሀ. አቶ ሀሰን ሰኞ እለት ከጫማ ሽያጭ ስንት ብር አገኙ?

ለ. አቶ ሀሰን ማክሰኞ እለት ከጫማ ሽያጭ ስንት ብር አገኙ?

ሐ. አቶ ሀሰን ረቡዕ እለት ከጫማ ሽያጭ ስንት ብር አገኙ?

መ. አቶ ሀሰን ከሰኞ እስከ ዓርብ እለት ከጫማ ሽያጭ በጠቅላላው ስንት ብር ገቢ

አገኙ?

3.2 ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት (ብዜታቸውም ከ1,000 ያልበለጡ)

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሙሉ ቁጥሮች ብዜትን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ታሰላላችሁ (ብዜቶችም ከ1,000 ያልበለጡ)

3.2.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቆጠራ ዝለላ መቁጠር

ተግባር 3.2

1. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ከ“1” በመነሳት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

1	2		4		6				
11				15			18	19	
21		23				27			30
31			34				38		
	42				46				50
		53		55				59	
61			64			67	68		

2. የሚከተለውን ሠንጠረዥ ከ“2” በመነሳት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

2		6	8		12		16		20
22	24			30		34	36		
42		46	48		52			58	
	64			70			76		80
			88			94		98	

ማስታወሻ፦

- የቆጠራ ዝለላ ማለት በሒሳብ ትምህርት አንዱ ቁጥሮችን የማባዛት ዓይነት ነው። በመሆኑም አንድን ሙሉ ቁጥር መነሻ በማድረግ እና ተማሳሳይ ቁጥር በመዝለል (በማለፍ) የመቁጠር ዘዴ ነው።

ምሳሌ 3.3፦

1. ከዚህ በታች በቁጥር ዘለላ የተቀመጡ ቁጥሮችን ተመልክታችሁ ቀጥለው የሚመጡ ሶስት አባለትን በባዶ ቦታው ላይ ፃፉ።

   ሀ. 1፣ 2፣ 3፣ 4 –፣– እና – ለ. 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ –፣– እና –

   ሐ. 3፣ 6፣ 9፣ 12፣ –፣– እና – መ. 5፣ 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ –፣– እና –

2. ከዚህ በታች በ10 በተሰብ የቆጠራ ዘለላ በሠንጠረዥ ውስጥ ያለውን ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
110		130	140			170	180		200
210	220			250	260			290	
310		330	340			370	380		400
410	420			450	460			490	500
510		530	540			570	580	590	
610	620				660			690	700
710				750			780		
810		830			860	870			900
910	920			950			980		1,000

መፍትሔ፦

1. ሀ. 1፣ 2፣ 3፣ 4 ቁጥሮችን ከአንድ ጀምሮ በ1 መዝለል ስለሆነ ቀጥለው የሚመጡ ሶስት ተከታታይ ቁጥሮች 5፣ 6 እና 7 ይሆናሉ።

1. ለ. 2፣ 4፣ 6፣ 8 ቁጥሮችን ከሁለት ጀምሮ በ2 መዝለል ስለሆነ ቀጥለው የሚመጡ ሶስት ተከታታይ ቁጥሮች 10፣ 12 እና 14 ይሆናሉ።

1. ሐ. 3፣ 6፣ 9 እና 12 ቁጥሮችን ከሶስት ጀምሮ በ3 መዝለል ስለሆነ ቀጥለው የሚመጡ ሶስት ተከታታይ ቁጥሮች 15፣ 18 እና 21 ይሆናሉ።

መ. 5፣ 10፣ 15፣ 20 እና 25 ቁጥሮችን ከአምስት ጀምሮ በ5 መዝለል ስለሆነ ቀጥለው የሚመጡ ሶስት ተከታታይ ቁጥሮች 30፣ 35 እና 40 ይሆናሉ።

2. በሠንጠረዡ ላይ የተሰጡ ቁጥሮች ከ10 ጀምሮው በ10 ዘለላ የተገለፁ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው።

10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
110	120	130	140	150	160	170	180	190	200
210	220	230	240	250	260	270	280	290	300
310	320	330	340	350	360	370	380	390	400
410	420	430	440	450	460	470	480	490	500
510	520	530	540	550	560	570	580	590	600
610	620	630	640	650	660	670	680	690	700
710	720	730	740	750	760	770	780	790	800
810	820	830	840	850	860	870	880	890	900

910	920	930	940	950	960	970	980	990	1,000

መልመጃ 3.2

1. ከዚህ በታች ባለው የቁጥር ዘለላ መሠረት ቀጥለው የሚመጡ ሶስት አባላትን ፃፉ።

   ሀ. 6፣ 12፣ 18፣ _____፣ _____ እና _____

   ለ. 8፣ 16፣ 24፣ 32፣ _____፣ _____እና _____

2. በ4 ቁጥር ዘለላ እስከ 28 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ።
3. በ10 ቁጥር ዘለላ እስከ 100 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ።
4. በ100 ቁጥር ዘለላ እስከ 1,000 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ፃፉ።
5. አንድ የገቢዎች መስሪያ ቤት ሠራተኛ በመስከረም ወር 30 ብር፣ በጥቅምት ወር 60 ብር እና በሕዳር ወር 90 ብር ቢያስገባ በዚህ ዓይነት የገቢ አስባሰብ ሁኔታ በቀጣይ ሶስት ወራት የሚያስገባው ገቢ በተከታታይ _____ብር፣ ____ ብር እና— ብር ነው።
6. አቶ ሉምባሶ 6 የአቮካዶ ችግኝ መደቦች አሉት። በእያንዳንዱ መደብ 70 ችግኞች አሉ። ለአቶ ሉምባሶ በጠቅላላው ስንት የአቮካዶ ችግኞች አሉት?

3.2.1 ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያለ አለኝታ እና በአለኝታ ማባዛት

እስከ 100 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማባዛት በ2ኛ ክፍል ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያለ አለኝታ እና በአለኝታ ማባዛትን ትማራላችሁ።

ተግባር 3.3

ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ።

1. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በሶስት ሲባዛ ውጤቱ ስንት ነው?
2. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ስንት ነው?
3. 486ን በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜት እና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ።

ማስታወሻ፦

1. ባለ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ያለ አለኻታ ሲባዛ፤ 1ኛ. የ1 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በ1 ቤት መፃፍ። 2ኛ. የ10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን በ10 ቤት ወይም በ10 እና በ100 ቤቶች መፃፍ።

2. ባለ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በአለኻታ ሲባዛ፤

1ኛ. የ1 ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘውን ውጤት የ1 ቤት ሆሄውም በ1 ቤት ጽፎ የ10 ቤት ሆሄውን አለኻታ ብሎ ማቆየት

2ኛ. የ10 ቤት ሆሄንው አባዝቶ ውጤቱን አለኻታ ከተባለው ጋር መደመር እና መልሱን በ10 ቤት ስር ወይም በ10 እና በ100 ቤት ስር መፃፍ።

ምሳሌ 3.4፦

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮችን በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜት እና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ።

   ሀ. 867 ለ. 389 ሐ. 456

2. የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. 14×2 ለ. 82×3 ሐ. $\begin{array}{r} 34 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

1ሀ. $867 = 8 \times 100 + 6 \times 10 + 7 \times 1 = 800 + 60 + 7$

ለ. $389 = 3 \times 100 + 8 \times 10 + 9 \times 1 = 300 + 80 + 9$

ሐ. $456 = 4 \times 100 + 5 \times 10 + 6 \times 1 = 400 + 50 + 6$

2. ሀ. 14×2 አሰራሩ ቁጥሮችን በመጀመሪያ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ጽፎ የአንድ ቤት ሆሄውን 4ን በ2 ማባዛትና ውጤቱን በ1 ቤት ስር መጻፍ።

$4 \times 2 = 8$ ከዚያም የ10 ቤት ሆሄውን በ2 ማባዛትና ውጤቱን በ10 ቤት ስር መጻፍ $1 \times 2 = 2$

ስለዚህ $\begin{array}{r} 14 \\ \times 2 \\ \hline 28 \end{array}$

2. ለ. 82×3 በመጀመሪያ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ጽፎ የአንድ ቤት ሆሄውን 2ን በ3 ማባዛትና ውጤቱን በ1 ቤት ስር መጻፍ። $2 \times 3 = 6$ ከዚያም የ10 ቤት ሆሄውን በ3 ማባዛትና ውጤቱን በ10 ቤት ስር መጻፍ $8 \times 3 = 24$

ስለዚህ $\begin{array}{r} 82 \\ \times 3 \\ \hline 246 \end{array}$ (ብዜቱም ያለ አለኝታ ተባዝቷል)

2. ሐ. 34×2 በመጀመሪያ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ጽፎ የአንድ ቤት ሆሄውን 4ን በ2 ማባዛትና ውጤቱን በ1 ቤት ስር መጻፍ። $4 \times 2 = 8$ ከዚያም የ10 ቤት ሆሄውን በ2 ማባዛትና ውጤቱን በ10 ቤት ስር መጻፍ $3 \times 2 = 6$

ስለዚህ
$$\begin{array}{r} 34 \\ \times\ 2 \\ \hline 68 \end{array}$$

መልመጃ 3.3

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮችን በ100 ብዜት፣ በ10 ብዜት እና በባለ አንድ ሆሄ ድምር ፃፉ።

   ሀ.386 ለ. 209 ሐ. 820 መ. 985

2. የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. $\begin{array}{r} 84 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 35 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 62 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 85 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 95 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 32 \\ \times 5 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 66 \\ \times 8 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 44 \\ \times 7 \\ \hline \end{array}$

3.2.2 ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያለ አለኽታ እና በአለኽታ ማብዛት

መግቢያ

ከዚህ በፊት ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚባዛን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛትን ትማራላችሁ።

ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ።

1. ትንሹ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ8 ሲባዛ ውጤቱ ስንት ነው?
2. የአንድ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለሰባት ጎበዝ ሴት ተማሪዎች ደብተር ለመሸለም ፈልጎ ለእያንዳንዳቸው 13 ደብተሮዎችን ለመስጠት ርዕስ መምህሩ ስንት ደብተሮዎች ያስፈልጉታል?
3. የሚከተለውን የማባዛት ሂደት ተመልከቱና በመጨረሻም መልስ ፃፉ።

$5 \times 3 = 15$ = _____

$50 \times 3 = 150$ = _____

500×3 = _____

ማስታወሻ፦

ሶስት ሆሄ ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች አንድ ሆሄ ካላቸው ሙሉ ቁጥሮች ጋር

ሀ. በአለኝታ ሲባዛ በቤት ቤታቸው ማባዛትና ውጤቱንም በቤት ቤታቸው ስር መፃፍ

ለ. በአለኝታ ሲባዛ የ1 ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘውን ውጤት የ1 ቤት ሆሄውም በ1 ቤት ጽፎ የ10 ቤት ሆሄውን አለኝታ ብሎ ማቆየት፤ ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄንው አባዝቶ ውጤቱን አለኝታ ከተባለው ጋር መደመር እና መልሱን በ10 ቤት ስር መፃፍ። በመጨረሻም የ100 ቤት ሆሄውን ማባዛት በአለኝታ የቆየ ካለ ከውጤቱ ጋር ደምሮ በ100 ቤት ወይም በ100 እና በ1,000 ቤት ስር መፃፍ።

ምሳሌ 3.5፦

1. የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. $\begin{array}{r} 312 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 152 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$

2. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ፈልጉ።

ሀ. የአንድ ከተማ ሰፈር የእናቶች እድር በጋራ በመወያየት በሰፈራቸው በዝቅተኛ ኑሮ ላሉ 8 ሰዎችን ለመረዳት አቅደው ለእያንዳንዳቸው 120 ብር በማወጣት ለዘመን መለወጫ በዓል መዋያ ብር ሰጡ። አጠቃላይ በጋራ ያወጡት የብር መጠን ስንት ይሆናል?

ለ. አንድ የተማሪ ወላጅ ለልጁ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን የያዙ 4 ማጣቀሻ መጽሐፍትን እያንዳንዳቸውን በ250 ብር ቢገዛ የአራቱ መጽሐፍት ጠቅላላ ዋጋ ስንት ይሆናል?

መፍትሔ፦

ሀ. $\begin{array}{r} 312 \\ \times\ 3 \\ \hline \end{array}$

በቤት ቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታቸው ስር መፃፍ፤

- 3 × 2 = 6 6ን በ1 ቤት ስር መፃፍ፤
- 3 × 1 = 3 3ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤
- 3 × 3 = 9 9ን በ100 ቤት ስር መፃፍ

ስለዚህ $\begin{array}{r} 312 \\ \times\ 3 \\ \hline 936 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም ያለ አለኝታ የተባዛ ነው)።

ለ. $\begin{array}{r} 152 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$

- በቤት ቤታችው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታችው ስር መፃፍ፤
- 4 × 3 = 12 2ን በ1 ቤት ስር ፅፎ “1”ን በአለኝታ ወይም በተሻጋሪነት ማቆየት፤
- 4 × 5 = 20 “20”ን አለኝ ካለነው ከ1 ጋር መደመር 20 +1 = 21 “1”ን በ10 ቤት ስር መፃፍ እና “2”ን በአለኝ ማቆየት፤
- 4 × 1 = 4 “4”ን በአለኝታ ካቆየነው ከ“2” ጋር በመደመር 4 + 2 = 6
- ስለዚህ “6” በ100 ቤት ስር መፃፍ፤
- ስለዚህ $\begin{array}{r} 153 \\ \times\ 4 \\ \hline 612 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም በአለኝታ የተባዛ ነው)::

መፍትሔ፦

2ሀ. በመጀመሪያ ጥያቄውን ደጋግሞ ማንበብ።

በሰፈሩ በዝቅተኛ ኑሮ ያሉ ሰዎች 8 ናቸው። እያንዳንዳቸው የተረዱት ብር 120

ስለዚህ $\begin{array}{r} 120 \\ \times\ 8 \\ \hline 960 \end{array}$ አዋጥተው የሰፈሩ ሴቶች ረድተዋል::

2ለ. በመጀመሪያ ጥያቄውን ደጋግሞ ማንበብ።

የተማሪው ወላጅ መግዛት የፈለገው መጽሐፍት ብዛት 4 ነው።

የእያንዳንዱ ማጣቃሻ መጽሐፍ ዋጋ 250 ብር ነው።

ስለዚህ $\begin{array}{r} 250 \\ \times 4 \\ \hline 1{,}000 \end{array}$ ይሆናል (የተማሪው ወላጅ ወጪ አውጥቷል)::

መልመጃ 3.4

1. የሚከተሉትን አባዙ::

ሀ. $\begin{array}{r} 343 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 123 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 244 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 112 \\ \times 8 \\ \hline \end{array}$

ሠ. $\begin{array}{r} 400 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ረ. $\begin{array}{r} 143 \\ \times 7 \\ \hline \end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r} 500 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r} 112 \\ \times 6 \\ \hline \end{array}$

2. ትልቁ ባለ ሶስት ሙሉ ቁጥር በ4 ሲባዛ ውጤቱ ስንት ነው?
3. ወይዘሮ ባሎቴ ባምኤ ለዓመት በዓል 4 ኪሎ ቀይ ሽንኩሪት ገዛች:: የአንድ ኪሎ ዋጋ 35 ብር ነው:: ወይዘሮ ባሎቴ ጠቅላላ ስንት ብር አውጥታለች?
4. በአንድ ገበያ ለሽያጭ የሚቀርቡ የእያንዳንዱ ከብት ቀረጥ 9 ብር ቢሆን፥ በዕለቱ ወደ ገበያ የገቡ ከብቶች ብዛት 55 ቢሆኑ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ከዕለቱ ቀረጥ ምን ያህል ገቢ ያገኛል?
5. ከአንድ አውቶቢስ ተራ የሚወጣ ማንኛውም መኪና የመውጫ 8 ብር ታሪፍ ቢከፈል፥ በቀን 66 መኪናዎች ከዚሁ አውቶቢስ ተራ ቢወጡ አጠቃላይ ከታሪፍ የሚያስገባው የዕለት ገቢ ስንት ነው?

የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ"0" ሲባዛ ውጤቱ "0" ነው:: ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ"1" ሲባዛ ውጤቱ ራሱ ቁጥሩ ይሆናል::

- ባለ ሁለት ወይም ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር ያለ አለኝታና በአለኝታ ሲባዙ፦
  - ✓ ከአንድ ቤት ሆሄው በመጀመር በቤት በቤታቸው ማብዛት፤
  - ✓ የተገኘውን ውጤት በቤት በቤት አድርጎ መጻፍ፤ አለኝታ ያለው ከሆነ "አለኝ" የሚባለውን ቁጥር የሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄ ብዜት ጋር መደመር፤

ለቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሔ ስትፈልጉ

- ✓ በመጀመሪያ ጥያቄዎችን ደጋግሞ በማንበብ መረዳት፤
- ✓ ቀጥሎ በጥያቄው ውስጥ የተሰጡትን መረጃዎች ተጠቅሞ የተጠየቀውን መፈለግ፤
- ✓ በመጨረሻ የተገኘውን መልስ ማስቀመጥ

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ከሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ።

ሀ. ትንሹን ባለ ሶስት ሆሄ የ100 ብዜት በ9 በማባዛት የሚገኘው ውጤት ባለ አራት ሆሄ ነው።

ለ. የ100 ብዜቶች ሁሉ የ10 ብዜቶች ናቸው።

ሐ. ትንሹ ባለ ሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ4 ሲባዛ ውጤቱ 400 ነው።

መ. ትልቁ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር በ3 ሲባዛ ውጤቱ 290 ነው።

2. የሚከተሉትን አባዙ።

ሀ. 32×4 ለ. 43×5 ሐ. 85×6

መ. 300×3 ሠ. 900×6 ረ. 600×8 ሰ. 3×500

ሸ. $\begin{array}{r} 314 \\ \times 2 \\ \hline \end{array}$ ቀ. $\begin{array}{r} 123 \\ \times 3 \\ \hline \end{array}$ በ. $\begin{array}{r} 234 \\ \times 4 \\ \hline \end{array}$

3. ከዚህ በታች ባለው ቁጥር ዘለላ መሠረት ቀጥለው የሚመጡ ሶስት አባላትን ፃፉ።

ሀ. 7፣ 14፣ 21፣ __፣ ___ እና __ ሐ. 80፣ 100፣ 120፣ __፣ __እና ___

ለ. 110፣ 120፣ 130፣__፣ __ እና __ መ. 100፣ 200፣ 300፣___፣ __ እና__

4. በአንድ ማሸጊያ ካርቶን ውስጥ 8 መጽሐፍት ብታሸግ፥ በ40 ማሸጊያ ካርቶን ውስጥ ስንት መጽሐፍት ይገኛሉ?
5. በአንድ ምግብ ቤት የሚሰራ አንድ አስተናጋጅ በቀን 9 ብር ጉርሻ ቢያገኝ በ90 ቀናት ቆይታ ስንት ብር ያገኛል?
6. አንድ የሰፈራችሁ ለጋሽ ሰው በቀበሌያችሁ ላሉ 7 ወላጅ አልባ ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው በ108 ብር አውጥቶ 6 ደብተሮችን ገዝቶ ቢሰጥ ለጋሹ ሰውዬ ጠቅላላ ስንት ብር ያወጣል?
7. አንድ የቀን ሰራተኛ በህዳር ወር 5 ብር፣ በታህሳስ ወር 10 ብር፣ በጥር ወር 15 ብር ቢቆጥብና በዚሁ ዓይነት ቀጣዩን ሶስት ወራት የሚቆጥበው ብር በተከታታይ ____፣ ___ እና __ ብር ነው።



4. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል

መግቢያ

በምዕራፍ ሶስት እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የዚህ ምዕራፍ ዓቢይ ትኩረት እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መከለስ እና እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል ሲሆን፣ ይህንኑ ከግብ ለማድረስ አምስት ንዑስ ምዕራፎችን በዋናነት የሚሸፈኑ ይሆናሉ። እነርሱም እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ ቀሪ በ2 ማካፈል፣ እስክ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአንድ ማካፈል፣ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል እና እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ያለ ቀሪ ማካፈልን ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማካፈልን ትረዳላችሁ።
- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10 በቀሪና ያለ ቀሪ ማካፈልን ትረዳላችሁ።

4.1 ማካፈልን እንደ እኩል መጋራት እና ደጋግሞ መቀነስ

መግቢያ

እስከ አሁን ስለ ማካፈል እና በምዕራፍ አንድ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ስለ መቀነስ የተማራችሁትን ጽንሰ-ሀሳብ መሠረት በማድረግ አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ ማካፈልን እንደእኩል መጋራት እና ደጋግሞ መቀነስ ትማራላችሁ

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ ቀሪ በ2 ማካፈልን ታሰላላችሁ።

ተግባር 4.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ስሩ።

1. 18 ኪሶችን ሁለት ልጆች እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት ኪሶች ይደርሳሉ?
2. 16 ጠጠሮችን ሁለት እኩል ቦታ መድቡ። በአንድ ምድብ የሚገኙት ጠጠሮች ስንት ናቸው?

ማስታወሻ፦

- ማካፈል አንድ ቁጥር በሌላ ቁጥር ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደሚገኝ የሚገልጽ መሠረታዊ ስሌት ነው።

ምሳሌ 4.1፦

12 ÷ 6 = 2 ማለት 6 በ12 ውስጥ 2 ጊዜ ይገኛል ማለት ነው። በመሆኑም 12ን ለ6 ለማካፈል በመጀመሪያ ለ6ቱ እኩል ተጋሪዎች ለእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ከተካፋዩ ቀንሶ መስጠት፤ ቀጥሎም ለእያንዳንዱ ተጋሪ የቀረውን ተካፋይ አንድ አንድ ቀንሴን ስንሰጥ የሚቀር ተካፋይ የለም።

መልመጃ 4.1

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ለሁለት እኩል ተጋሪዎቻቸው አካፍሉ።

   ሀ. 14 ለ. 20 ሐ. 10

2. ወ/ሮ ሞኒቼ 8 ማንጎዎችን ለሁለት ልጆቹ ገዘታ እሁል አካፈለቻቸው። የአንዱ ልጅ ድርሻ ስንት ነው?

4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ማካፈል

መግቢያ

ከዚህ በፊት በሒሳብ ትምህርታችሁ ላይ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መከለስን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ለሁለት ያለ ቀሪ የሚካፈሉ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ማካፈልን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 ማካፈልን ታሰላላችሁ።

ተግባር 4.2

1. የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ በመሆን በመወያየት መልሱ።

   ሀ. አስራ ስድስት ብርቱካኖች ለሁለት ልጆች ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

   ለ. 10 ደብተሮች ለሁለት ተማሪዎች ስንት ስንት ይደችሳቸዋል?

ማስታወሻ፦

"ሀ" እና "ለ" ከዜሮ የተለዩ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ እና $ሀ \times ለ = ሐ$ ከሆነ $ሐ \div ለ = ሀ$ ሁልጊዜ እውነት ነው። $ሐ \div ለ = ሀ$ በሚለው ስሌት ውስጥ "ሐ" ተካፋይ፣ "ለ" አካፋይ እና "ሀ" ድርሻ ይባላሉ። "÷" ደግሞ የማካፈል ምልክት ነው።

ምሳሌ 4.2፦

የሚከተለትን አስሉ።

ሀ. $2 \div 2 = -$ ለ. $6 \div 2 = -$ ሐ. $12 \div 2 = -$

መ. $18 \div 2 = -$ ሠ. $20 \div 2 = -$

መፍትሔ፦

ሀ. $2 \div 2 = 1$ ነው፤ ምክንያቱም $2 = 2 \times 1$ እውነት ስለሆነ።

ለ. $6 \div 2 = 3$ ነው፤ ምክንያቱም $6 = 2 \times 3$ እውነት ስለሆነ።

ሐ. $12 \div 2 = 6$ ነው፤ ምክንያቱም $12 = 2 \times 6$ እውነት ስለሆነ።

መ. $18 \div 2 = 9$ ነው፤ ምክንያቱም $18 = 2 \times 9$ እውነት ስለሆነ።

ሠ. $20 \div 2 = 10$ ነው፤ ምክንያቱም $20 = 2 \times 10$ እውነት ስለሆነ።

መልመጃ 4.2

1. የሚከተሉትን ስሌቶች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ።

   ሀ. $12 \div 4 = 3$ ለ. $8 \div 2 = 4$ ሐ. $20 \div 2 = 10$ መ. $16 \div 8 = 2$

2. 18 ደብተሮች ለ2 ልጆች እኩል ቢከፋፈል የእያንዳንዱ ልጅ ድርሻ ስንት ደብተሮች ይሆናሉ?

4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል

መግቢያ

ከዚህ በፊት ባለው ክፍለ ጊዜያችሁ ያለ ቀሪ ለሁለት የሚካፈሉ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ማካፈልን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2፣ በ10 እና ቀጥሎ በ1 በማካፈልን ታሰላላችሁ።

ተግባር 4.3

1. የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱ

ሀ. አንድ ወላጅ ከትምህርት ቤት ተማሪዎች በልጦ አንደኛ የወጣው ልጃቸውን 90 ብር ሸለመ። ጎበዙ ተማሪ የተሸለመው ስንት ብር ነው?

ለ. 35 የቡና ችግኞችን አንድ ተማሪ እንድተክል ቢሰጠው ተማሪው መትከል ያለበት ድርሻው ስንት ነው?

ማስታወሻ፦

- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ1 ስካፈል ድርሻው ያንኑ ሙሉ ቁጥር ይሆናል።
- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ0 አይካፈልም። ነገር ግን "0" ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ስካፈል ድርሻው ዜሮ (0) ነው።

ምሳሌ 4.3፦

የሚከተሉትን ምሳሌዎች አሰራር ተመልክታችሁ በተመሳሳይ መንገድ የመልመጃ ጥያቄዎችን ስሩ።

ሀ. $52 \div 1$ ለ. $64 \div 1$

መፍትሔ፦

ሀ. $52 \div 1 = 52$ ነው፤ ምክንያቱም $52 = 52 \times 1$ እውነት ስለሆነ።

ለ. $64 \div 1 = 64$ ነው፤ ምክንያቱም $64 = 64 \times 1$ እውነት ስለሆነ።

መልመጃ 4.3

ከዚህ በላይ ባለው ምሳሌ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ።

ሀ. 12 ÷ 1 = _____ ነው፤ ምክንያቱም _____

ለ. 98 ÷ 1 = _____ ነው፤ ምክንያቱም _____

ሐ. 83 ÷ 1 = _____ ነው፤ ምክንያቱም _____

4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ያለ ቀሪ ለ2 የሚካፈሉ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ማካፈልና እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2፣ በ10 እና ቀጥሎ በ1 በማካፈልን ታሰላላችሁ።

ተግባር 4.4

1. የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱ።

ሀ. 50 ሎሚዎችን ለሁለት ሴቶች እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት ሎሚዎች ይደርሳቸዋል?

ለ. 15 ማንጎዎች ለ10 ልጆች እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት ማንጎዎች ይደርሳቸዋል? ለእያንዳንዳቸው ባለመድረስ ምክንያት የቀሩ ማንጎዎች ስንት ናቸው?

ማስታወሻ፦

- የ10 ብዜት የሆነውን ቁጥር ለ10 በማካፈል የሚገኙው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤት ሆሄ "0" በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው።
- ቀሪ የሚያስከትሉ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲካፈሉ ድርሻው በቀላሉ ለማወቅ፥ ተካፈዩን በአካፋዩ ብዜት እና ከአካፋዩ በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለጽ፤ ከዚያም የማካፈሉን ስራ በመቀጠል ድርሻና ቀሪውን ማግኘት።
- አንድ ቁጥር ለ10 በቀሪ ይካፈላል ማለት ቀሪው 1 እስከ 9 ያሉ ቁጥር ስሆን ነው። በቀሪ ለ 2 የሚካፈል ማንኛው ሙሉ ቁጥር ለሁለት ስካፈል ቀሪው 1 ነው።

ምሳሌ 4.4፦

የሚከተለትን አስሉ::

ሀ. $26 \div 2$ ለ. $27 \div 2$ ሐ. $30 \div 10$

መፍትሔ፦

ሀ.$12 \div 2 = 6$ ነው፤ ምክንያቱም $12 = 2 \times 6$ እውነት ስለሆነ።

ለ. $27 \div 2 =$ (26+1)÷2 → "27"ን በ2 ብዜትና ከ2 በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለጽ፤

$= (26 \div 2) + (1 \div 2)$

$= 13 + (1 \div 2)$ → "1"ን ለ2 ማካፈል ስለማይቻል "1"ን ቀሪ እንለዋለን።

ስለዚህ $27 \div 2 = 13$ ቀሪ 1 ይሆናል።

ሐ. $30 \div 10 = 3$ ነው፤ ምክንያቱም $30 = 3 \times 10$ እውነት ስለሆነ።

መልመጃ 4.4

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ. $84 \div 2$ ለ. $65 \div 2$ ሐ. $60 \div 10$ መ. $84 \div 10$

2. ሁለት የቀን ሰራተኞች በጋራ የሆነ ስራ ሰርተው ያገኙትን 94 ብር እኩል ቢካፈሉ፥ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

4.5 ያለ ቀሪ ለ3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 የሚካፈሉ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በእነዚህ ቁጥሮች ማካፈል

መግቢያ

ስለ ማካፈል እስካ አሁን የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ያለ ቀሪ ለ3፣ 4፣5፣ 6፣ 7፣8 እና 9 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈልን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና በ9 በማካፈል ያሰላላችሁ።

ተግባር 4.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ስሩ።

1. 21 ጠጠሮችን 3 እኩል ቦታ መድቡ። በእያንዳንዱ ምድብ የሚገኙ ጠጠሮች ስንት ናቸው



2. 32 ብርቱካኖችን 4 ልጆች እኩል ቢካፈሉ የአንዱ ልጅ ድርሻ ስንት ብርቱካኖች ይሆናሉ?



ማስታወሻ፡

ሀ፣ ለ እና መ መሉ ቁጥሮች ቢሆኑና ለ ከዜሮ ሌላ ቁጥር ከሆን እና ሀ ÷ ለ = መ ቢሆን ሀ = ለ × መ ይሆናል (የማካፈል ውጤት በማብዛት ይረጋገጣል)። ስለዚህ ማካፈልና ማብዛት አንዱ ለሌላኛው ተገላብጦሽ ስሌት ናቸው።

ምሳሌ 4.5፦

1. የሚከተሉትን አስልታችሁ መልሶቻችሁን በማብዛት ስለት አረጋግጡ።

   ሀ. $12 \div 3$ ለ. $16 \div 4$ ሐ. $20 \div 5$ መ. $42 \div 6$

   ሠ. $49 \div 7$ ረ. $48 \div 8$ ሰ. $63 \div 9$

2. የአንድ ትምህርት ቤት በጎ አድራጎት ክበብ በህዳር ወር ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ 84 ብር አውጥቶ ሶስት የትምህርት ቤቱ ጎበዝ ተማሪዎችን ቁርስ ቢጋብዝ፥ ክበቡ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስንት ብር አውጥቷል?

መፍትሔ፦

1 ሀ. $12 \div 3 = 4$ ነው፤ ምክንያቱም $12 = 4 \times 3$ በመሆኑ ነው።

ለ. $16 \div 4 = 4$ ነው፤ ምክንያቱም $16 = 4 \times 4$ በመሆኑ ነው።

ሐ. $20 \div 5 = 4$ ነው፤ ምክንያቱም $20 = 5 \times 4$ በመሆኑ ነው።

መ. $42 \div 6 = 7$ ነው፤ ምክንያቱም $42 = 6 \times 7$ በመሆኑ ነው።

ሠ. $49 \div 7 = 7$ ነው፤ ምክንያቱም $49 = 7 \times 7$ በመሆኑ ነው።

ረ. $48 \div 8 = 6$ ነው፤ ምክንያቱም $48 = 6 \times 8$ በመሆኑ ነው።

ሰ. $63 \div 9 = 7$ ነው፤ ምክንያቱም $63 = 9 \times 7$ በመሆኑ ነው።

2 አጠቃላይ ለ3 ተማሪዎች ቁርስ የወጣው 84 ብር ነው። $84 \div 3 = 28$ ብር ለእያንዳንዱ ተማሪ ወጪ ሆኗል። ስለዚህ ለእያንዳንዳቸው 28 ብር ክበቡ ወጪ አድርጓል።

መልመጃ 4.5

1. የሚከተሉትን አስሉ።

   ሀ. $55 \div 5$ ለ. $63 \div 3$ ሐ. $36 \div 4$ መ. $35 \div 7$

2. የሚከተሉትን ካሰላችሁ በኋላ ለእያንዳንዳቸው ተካፋዮችን፣ አካፋዩን እና ድርሻውን ለይታችሁ ፃፉ።

   ሀ. 48 ÷ 6 ለ. 81÷3 ሐ. 56 ÷ 4 መ. 99÷9

3. አንድ የችግኝ መደብ ላይ 9 የእንሰት ችግኞችን ብቻ መትከል ቢቻል፤ 90 የእንሰት ችግኞችን ለመትከል ስንት የችግኝ መደቦች ያስፈልጋል?
4. አንድ ሲኒ የፈላ ቡና ዋጋ 5 ብር ነው። በ85 ብር ስንት ሲኒ ቡና መግዛት ይቻላል?
5. አንድ ፓኬት ውስጥ 6 ሻማዎችን ብቻ ማሸግ ይቻላል። 48 ሻማዎችን በስንት የሻማ ፓኬቶች ውስጥ ማሸግ ይቻላል?
6. አንድ አራት አባላት ያሉት አርሶ አደሮች ጎብረት ሥራ ማህበር በዓመት 92 ኩንታል በቆሎ ቢያመርቱ እና ቢከፋፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት ስንት ኩንታል በቆሎ ይደርሳቸዋል?

4.6 በማባዛት እና በማካፈል መካከል ያለው ዝምድና

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል እና በሶስተኛ ክፍል ምዕራፍ 3 ስለማባዛት የተማራችሁትን ሀሳብ በማጠና ከር ማካፈል ከማባዛት ጋር ያለዉን ዝምድናምን እንደሚመስል በዚህ ንዑስ በስፋት ትማራላ ችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ማካፈል ከማባዛት ጋር ያለዉን ዝምድና ትገነዘባላችሁ።

ተግባር 4.6

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩባቸዉ።

   ሀ. የአንድ ኪሎ ግራም ሙዝ ዋጋ 9 ብር ነው። በ72 ብር ስንት ኪሎ ግራም ሙዝ መግዛት ይቻላል?

   ለ. 50 ሎሚ ለአምስት ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸዉ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

ሐ. በ “ለ” የተሰጠዉን ጥያቄ እንዴት ወደ ማባዛት ለዉጦ መጻፍ ይቻላል?

ማስታወሻ፦

ሀ. “ሀ” እና “ለ” ከዜሮ የተለዩ ሁለት ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ እና $ሀ \times ለ = ሐ$ ከሆነ $ሐ \div ለ = ሀ$ ወይም $ሐ \div ሀ = ለ$ ሁልጊዜ እውነት ነው።

ለ. “መ” እና “በ”ሙሉ ቁጥሮች ሆነው (በ ከዜሮ የሚለይ ቢሆን) $መ \div በ = ቀ$ እውነት ከሆነ $መ = ቀ \times በ$ ሁልጊዜ እውነት ነው።

ምሳሌ 4.6፦

የሚከተሉትን ስሌቶች ትክክል መሆናቸውን አረጋግጡ።

ሀ. $15 \times 7 = 84$ ለ. $23 \times 8 = 184$ ሐ. $69 \div 3 = 23$

መፍትሔ፦

ሀ. $15 \times 7 = 84$ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም $84 \div 7 \neq 15$

ለ. $23 \times 8 = 184$ ትክክል ነው። ምክንያቱም $184 \div 8 = 23$ ስለሆነ

ሐ. $69 \div 3 = 23$ ትክክል ነው። ምክንያቱም $69 = 23 \times 3$ እውነት ስለሆነ።

መልመጃ 4.6

1. የሚከተሉትን ስሌቶች ትክክል መሆናቸውንና አለመሆናቸውን አረጋግጡ።

   ሀ. $5 \times 20 = 100$ ሐ. $96 \div 6 = 16$

   ለ. $30 \times 4 = 130$ መ. $84 \div 4 = 12$

2. ለ10 ሴቶች ለእያንዳንዳቸው 50 ፍየሎች ተሰጣቸው። በጠቅላላ ለ10 ሴቶች ስንት ፍየሎች ተሰጣቸው? ውጤቱን በማካፈል አረጋግጡ።

3. 14 ከርሜላዎች 2 ልጆች እኩል ቢከፋፈሉ፤ ስንት ስንት ይደርስላቸዋል? ውጤቱን በማብዛት አረጋግጡ።



የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር "ሀ" ሀ÷ 1 = ሀ ነው።
- የ10 ብዜት ሙሉ ቁጥርን ለ10 ለማካፈል በአጭሩ የ10 ብዜቱን የ1 ቤት "0" ማጥፋት ነው።
- በማካፈል የሚገኘውን ውጤት በማብዛት ማረጋገጥ ይቻላል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን አካፍሉ።

   ሀ. 82÷2 ሐ. 88 ÷4 ሠ. 36÷6 ሰ. 72 ÷8

   ለ. 27÷3 መ. 80÷5 ረ. 42÷7 ሸ. 40÷10

2. አንድ ማሸጊያ ካርቶን ውስጥ 8 መጽሐፍትን ማሸግ ይቻላል። 72 መጽሐፍትን ለማሸግ ስንት ካርቶኖች ያስፈልጋሉ?

3. አንድ የጫማ አዳሽ በቀን 7 ጥንድ ጫማዎችን ያድሳል። ይህ አዳሹ 49 ጥንድ ጫማዎችን በስንት ቀን ያድሳቸዋል?



5. ክፍልፋዮች

መግቢያ

የዚህ ምዕራፍ ዓቢይ ትኩረት ስለ ክፍልፋዮች ያላችሁትን በበለጠ ግንዛቤ ማስላት ሲሆን ይህንኑ ከግብ ለማድረስ አራት ንዑስ ምዕራፎችን በዋናነት የሚሸፈኑ ይሆናሉ። በመጀመሪያ ቀደም ካለው ዕውቀታቸው በመነሳት የሶስት ክፍልፋዮች ክለሳ ይካሄዳል። በመቀጠል በሁለተኛው ንዑስ ምዕራፍ ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮችን መግለጽ እንዲችሉ የተለያዩ ምሳሌዎች በግልና በቡድን የሚሰሩ የተግባር ጥያቄዎች ይኖራሉ። በሶስተኛው ንዑስ ምዕራፍ፣ የሙሉ ቁጥሮች ግማሽና ሩብ በተለይ የ2 ብዜቶችን ግማሽና የ4 ብዜቶችን ሩብ እንዴት መፈለግ እንዲሚችሉ ትማራላችሁ። በመጨረሻም ንዑስ የክፍልፋዮችን ውክልና በመደመርና በመቀነስ እንዴት መግለጽ እንደትሚችሉ ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ክፍልፋይ የሙሉ አካል ወይም የስብስብ ክፍል መሆኑን ትረዳላችሁ።
- በነባራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ላይ ክፍልፋዮች በመጠቀም ትተገብራላችሁ።

5.1 ግማሽ፣ ሩብ እና ሲሶ

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል በሒሳብ ትምህርታችሁ ስለተወሰኑ ክፍልፋዮች ስያሜ ለምሳሌ፦ ስለግማሽ ፣ ስለሩብ እና ስለሲሶ (አጠራር) ተምራችኋል። በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ዳግም የግማሽ፣ የሩብ እና የሲሶ ምሳሌዎች በስዕል እና በአኃዝ እንዴት እንደሚገለጽ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ግማሽ፣ ሩብና ሲሶን ትለያላችሁ።

ተግባር 5.1

ከዚህ በታች የቀረቡትን ምስሎች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን መልሱ።



ካሬ



ሬክታንግል



ክብ

ሀ. ካሬ ለስንት እኩል ቦታ ተከፍሏል?

ለ. ሬክታንግል ለስንት እኩል ቦታ ተከፍሏል?

ሐ. ክብ ለስንት እኩል ቦታ ተከፍሏል?

መ. የተቀባው ክፍል የሬክታንግሉን ስንት ስንተኛ ነው?

ሠ. የተቀባው ክፍል የካሬውን ስንት ስንተኛ ነው?

ማስታወሻ፦

- ከላይ የተመለከትነው ምስል ካሬ ለሁለት እኩል ቦታ ተከፍሎ አንዱ ክፋይ ተቀብቷል። ይህ ክፋይ ከዋናው ካሬ ምስል አንድ-ሁለተኛ አካል ተብሎ ይጠራል። የተቀባው ቦታ ለካሬ $\frac{1}{2}$ ወይም **ግማሽ** ተብሎ ይጠራል።
- የተቀባው ክፋይ የሬክታንግሉ $\frac{1}{4}$ ወይም **ሩብ** ተብሎ ይጠራል።
- የተቀባው ቦታ የክብ ክፍል የክቡ $\frac{1}{3}$ ወይም **ሲሶ** ተብሎ ይጠራል።
- አንድ ሙሉ ነገር ለእኩል ክፍሎች ከተከፋፋለ እያንዳንዱ ክፍል **ክፍልፋይ** ይባላል።
- ክፍልፋይ "$\frac{1}{4}$" የአንድ-አራተኛ አኃዛዊ አጻጻፍ ሲሆን፥ ስያሜዎቹ እና ትርጉሞቹ እንደሚከተሉት ናቸው።
  "1" የክፍልፋዩ **ላዕል (ጠሪ)** ሲሆን ይህም የክፍልፋይ መጠንን ይገልፃል።
  "4" የክፍልፋዩ **ታህት (ቆጣሪ)** ሲሆን ይህም አንድ ሙሉ ነገር ከስንት እኩል ቦታ እንደተካፋፈሉ ይገልፃል።
- አግድም **ሰረዙ (-)** የክፍልፋይ **ሰረገ** ይባላል።

መልመጃ 5.1

1. የሚከተለው ምስል በአራት እኩል ቦታዎች የተከፈለ ነው። የተቀባውን የምስሉን ክፍል በአጋዝ (በክፍልፋይ) ግለጹ።



2. የሚከተሉትን ክፍልፋዮች ላዕል እና ታህት ለይታችሁ ፃፉ።

ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{1}{2}$ ሐ. $\frac{1}{4}$

5.2 ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች

መግቢያ

በ5.1 ንዑስ ርዕስ ምስሎችን በመጠቀም የተወሰኑ ክፍልፋዮች እንዴት እንደሚመሰረቱ ቀደም ሲል የተማራችሁትን አስታወሱ። አሁን ደግሞ ከ$\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች ላዕል እና ታህት ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮችን በቁጥር መስመር ላይ በማንበብ ትገልጻላችሁ።

ተግባር 5.2

1. ከዚህ በታች በቀረበው የመጀመሪያ ምሳሌ መሠረት ሌሎችን ጥያቄዎች ስሩ።

ሀ.  የክፋዮች ብዛት = _____

የተቀባው ክፍል ብዛት = _____

የተቀባው በክፍልፋይ ስገለጽ = _____

ለ.  የክፋዮች ብዛት = _____

የተቀባው ክፍል ብዛት = _____

የተቀባው በክፍልፋይ ስገለጽ = _____

ሐ.  የክፋዮች ብዛት = _____

የተቀባው ክፍል ብዛት = _____

የተቀባው በክፍልፋይ ስገለጽ = _____

ማስታወሻ፦

- ላዕላቸው 1 የሆኑ ክፍልፋዮች ሁሉ አሀዳዊ ክፍልፋዮች ይባላሉ።

  ለምሳሌ፦ $\frac{1}{2}$፣ $\frac{1}{3}$፣ $\frac{1}{4}$፣ $\frac{1}{5}$ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

- አንድ-ሁለተኛ በአኃዝ $\frac{1}{2}$ ተብሎ ይጻፋል።
- አንድ-አምስትኛ በአኃዝ $\frac{1}{5}$ ተብሎ ይጻፋል።
- የተወሰኑ አኃዳዊ ክፍልፋዮች የተለመደ አጠራር አላቸው። እነርሱም፦
- $\frac{1}{2}$ **ግማሽ** ተብሎ ይጠራል። $\frac{1}{3}$ **ሲሶ** ተብሎ ይጠራል።
- $\frac{1}{4}$ **ሩብ** ተብሎ ይጠራል። $\frac{1}{5}$ **አምሶ** ተብሎ ይጠራል።
- $\frac{1}{10}$ **አስራት** ተብሎ ይጠራል።
- የአሀዳዊ ክፍልፋዮች ታህታቸው እየጨመረ ሲሄድ የክፍልፋዮች ዋጋ እያነሰ ይሄዳል።

  ለምሳሌ፦ ከ $\frac{1}{2}$ ፤ $\frac{1}{3}$ ያነሰ ዋጋ አለው። ይኸውም፦ ስናወዳድራቸው $\frac{1}{3} < \frac{1}{2}$ ነው። ምክንያቱም የ $\frac{1}{3}$ ታህት "3" ከ $\frac{1}{2}$ ታህት "2" የሚበልጥ ስለሆነ ነው። ይኸውም

ስናወዳድራቸው 3 > 2 ነው።

- ስለዚህ ታህታቸው ከ2 እስከ 10 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የያዙ አሀዳዊ ክፍልፋዮች ከዚህ በታች ባለው የቁጥር መስመር ላይ በቅደም ተከተላቸውን ይዘው ተገልጸዋል።



መልመጃ 5.2

1. የጠቆረውን ክፍል በክፍልፋይ ፃፉ::

ሀ.  ለ.  ሐ. 

2. ከዚህ በታች በቃል የተገለጹ ክፍልፋዮች በተሰጠው ክፍት ቦታዎች በአኃዝ ፃፉ።

ሀ. አንድ-ሰባተኛ = _____ መ. አንድ-አስረኛ = _____

ለ. አንድ-ሶስተኛ = _____ ሐ. አንድ-ስምንተኛ =_____

3. ምስሎችን በማጦቀር ከአሀዳዊ ክፍልፋዮች ውስጥ $\frac{1}{4}$ ፣ $\frac{1}{6}$፣ $\frac{1}{7}$ እና $\frac{1}{9}$ አሳዩ።

4. ከዚህ በታች ያለውን የቁጥር መስመር ተጠቅማችሁ ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ክፍት ቦታዎችን አሟሉ።



ሀ. አንድ-አምስተኛ = ——

ለ. አንድ-ዘጠነኛ = ——

ሐ. አንድ-አራተኛ = ——

መ. አንድ-ስምንተኛ = ——

ሠ. አንድ-ሶስተኛ = ——

5.3 ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ ክፍልፋዮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተላቸው ማስቀመጥ

መግቢያ

ከዚህ በፊት ግማሽ፣ ሩብ እና ሲሶ በምስልና በአኃዝ እንዴት እንደሚገለጽና እንደሚጻፍ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የክፍልፋዮችን እንዴት ማወዳደር እና በቅደም ተከተላቸው እንደሚቀመጡ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የቁጥሮችን ግማሽ፣ ሩብና ሲሶን መለየትና ማወዳደር ነው።

ተግባር 5.3

1. ከዚህ በታች ያሉ ምስሎች እያንዳንዳቸው እኩል በሆኑ ክፍልፋዮች ተከፍለዋል። የተቀቡትን ክፍሎች ተመልከቱና የተሰጡትን አሀዳዊ ክፍልፋዮች፦ የ > ወይም < ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. $\frac{1}{6}$ ——— $\frac{1}{5}$



$\frac{1}{6}$

ለ. $\frac{1}{4}$ ——— $\frac{1}{6}$

$\frac{1}{4}$



ሐ. $\frac{1}{6}$ ——— $\frac{1}{10}$



$\frac{1}{6}$

ማስታወሻ፦

- አሀዳዊ ክፍልፋዮችን ለማወዳደር ታህታቸውን በማየት ትልቅ ታህት ያለው ክፍልፋይ ትንሹ ይሆናል። በተቀራኒ ትንሽ ታህት ያለው ክፍልፋይ ትልቁ ይሆናል።

ለምሳሌ 5.1፦

የሚከተሉትን አሀዳዊ ክፍልፋዮች የ> ወይም < ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. $\frac{1}{4}$ ——— $\frac{1}{7}$ **ለ.** $\frac{1}{3}$ ——— $\frac{1}{2}$

ሀ. $\frac{1}{4} > \frac{1}{7}$ **ምክንያቱም የ** $\frac{1}{4}$ **ታህት "4" ከ** $\frac{1}{7}$ **ታህት "7" ትንሽ ስለሆነ።**

ለ. $\frac{1}{3} < \frac{1}{2}$ **ምክንያቱም የ** $\frac{1}{3}$ **ታህት "3" ከ** $\frac{1}{2}$ **ታህት "2" ትልቅ ስለሆነ።**

መልመጃ 5.3

የሚከተሉትን አሀዳዊ ክፍልፋዮች የ> ወይም < ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. $\frac{1}{6}$ ——— $\frac{1}{7}$ **ለ.** $\frac{1}{9}$ ——— $\frac{1}{8}$ **ሐ.** $\frac{1}{8}$ ——— $\frac{1}{6}$ **መ.** $\frac{1}{7}$ ——— $\frac{1}{8}$ **ሠ.** $\frac{1}{10}$ ——— $\frac{1}{9}$

5.4 የሙሉ ቁጥሮች ግማሽ እና ሩብ

ከዚህ በፊት አሀዳዊ ክፍልፋዮች በፊደልና በአኃዝ እንዴት እንደሚገለጽና እንደሚጻፍ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የሙሉ ቁጥሮችን ግማሽና ሩብ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- **የቁጥሮችን ግማሽ፣ ሩብና ሲሶን መለየት እና ማወዳደር ነው።**

ተግባር 5.3

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ።
   ሀ. 12 ለ. 16 ሐ. 88
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ።
   ሀ. 20 ለ. 56 ሐ. 96

ማስታወሻ፦

- የ2 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ2 ማካፈል የሚገኘው ውጤት የሙሉ ቁጥሩ ግማሽ ነው።
- አንድ የ4 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ4 በማካፈል የሚገኝ ውጤት የሙሉ ቁጥሩ ሩብ ይባላል።

ምሳሌ 5.1፦



ጠቅላላ የሙዞች ብዛት = 8

እኩል ሙዞችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 2

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ሙዞች 4 ናቸው።

ስለዚህ 4 = 8÷2

ይህ ማለት የ8 ግማሽ 4 ማለት ነው።

2. ጠቅላላ የኳሶች ብዛት = 12

እኩል ኳሶችን የያዙ ክፍሎች ብዛት = 4

በአንዱ ክፍል ውስጥ ያሉ ኳሶች ብዛት 3 ናቸው።

ስለዚህ 3 = 12÷4

ይህ ማለት የ12 ሩብ 3 ማለት ነው።



ምሳሌ 5.2፦

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ።

   ሀ. 14 ለ. 82

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ።

   ሀ. 40 ለ. 60

መፍትሔ፦

1. ሀ. የ14 ግማሽ = 14÷2 = 7 ለ. የ82 ግማሽ = 82÷2 = 41

2. ሀ. የ40 ሩብ = 40÷4 = 10 ለ. የ60 ሩብ = 60÷4 = 15

መልመጃ 5.4

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ።

   ሀ. 18 ለ. 22 ሐ. 26 መ. 32

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ።

   ሀ. 48 ለ. 28 ሐ. 36 መ. 80

3. ትሕትና 4 ኪሎ ግራም ብርቱካን ገዛች። የአራቱ ኪሎ ግራም ብርቱካን ዋጋ 64 ብር ነው። በጠቅላላ 4 ኪሎ ግራም ብርቱካን ለመግዛት ካወጣችው ብር ውስጥ ግማሹ ስንት ነው?

4. አንድ መምህር 72 ደብተሮችን ለ8 ጎበዝ ተማሪዎች እኩል ቢያከፋፍል፥ የአንዱ ተማሪ ድርሻ ስንት ደብተሮች ይሆናል?

የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

- አንድ ሙሉ ነገር ለእኩል ክፍሎች ሲካፈል ክፍልፋይ ይባላል።
- አሀዳዊ ክፍልፋዮችን በፊደል ስንገልጽ፥ አንድ-ሁለተኛ፣ አንድ-ሶስተኛ ወዘተ ተብለው ይገለጻሉ።
- አግድም ሰረዙ "–" የክፍልፋይ ሰረዝ ይባላል።
- በተለምዷዊ አጠራር ግማሽ ማለት $\frac{1}{2}$፣ ሲሶ ማለት $\frac{1}{3}$፣ ሩብ ማለት $\frac{1}{4}$፣ አምሶ ማለት $\frac{1}{5}$ እና አስራት ማለት $\frac{1}{10}$ ናቸው።

- “ሀ” እና “ለ” ሙሉ ቁጥሮች እና ለ ዜሮ የተለየ ቁጥር ቢሆን ክፍልፋይ $\frac{ሀ}{ለ}$ ውስጥ “ሀ” ላዕል ስሆን የክፍልፋይ መጠን ይገልፃል። ደግሞ “ለ” ታህት ስሆን አንድ ሙሉ ነገር ለስንት እኩል ቦታ እንደተከፋፈለ ይገልጻል።
- የ2 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ2 ማካፈል (ሁለት እኩል ቦታ መክፈል) የሚገኘው ውጤት የሙሉ ቁጥር “ግማሽ” ይባላል።
- የ4 ብዜት የሆነን ሙሉ ቁጥር ለ4 ማካፈል (አራት እኩል ቦታ መክፈል) የሚገኘው ውጤት የሙሉ ቁጥር “ሩብ” ይባላል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. አንድ ነጭ ወረቀት ለሶስት እኩል ቦታ ክፈሉ። የላይኛውን ክፍል አረንጓዴ ቀለም ቀቡ፣ መካከለኛውን ክፍል ቢጫ ቀለም ቀቡ እና የታችኛውን ክፍል ቀይ ቀለም ቀቡ።

   ሀ. አረንጓዴ የተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲፃፍ = ——

   ለ. ቀይ የተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲፃፍ = ——

   ሐ. ቢጫ የተቀባው ክፍል በክፍልፋይ ሲፃፍ = ——



2. ከበቡሽ አስራ ሁለት እንቁላሎችን ገዝታ አንድ-

   ሶስተኛውን ለቁርስ ጠበሰችው የተጠበሰው የእንቁላሎች ብዛት ስንት ነው?

3. ለወጣት አሸኮ በልብስ መሸጫ ሱቅ 20 ሱሪዎች ነበሩ። በዓመት በዓል ሰሞን ሩብ ሱሪዎች ቢሸጡ ያልተሸጡ ሱሪዎች ስንት ናቸው?

4. 30 ብርቱካኖችን አምስት ልጆች እኩል ቢከፋፈሉ ለእያንዳንዳቸው ምን ያህል ብርቱካኖች ይደርሳል?

5. የሚከተሉትን የተለመዱ የአሀዳዊ ክፍልፋዮች በምሳሌው መሰረት ስያሜያቸውን ስጡ።

ክፍልፋይ	ስያሜ
$\frac{1}{2}$	ግማሽ
———	ሲሶ

$\frac{1}{4}$	————
$\frac{1}{5}$	————



6. ስርዓተ ጥለቶች (ፓቴርን)

መግቢያ

አብዛኛው በዓለማችን ውስጥ ያሉ ነገሮች፣ ሁኔታዎችና ክስተቶች በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ስርዓት ራሳቸውን የሚደጋገሙ ወይም በሚገመት ሁኔታ የሚከሰቱ ናቸው። ከእነዚህም መካከል፥ ቅርፆች፣ ቀለማት፣ የቁጥር ስብስቦች፣ ክስተቶች፣ ሁኔታዎች ወዘተ የመሳሰሉት ይገኛሉ። እነዚህ ሲከሰቱ ከሚከሰቱበት ባህሪያት አንዱ የስርዓተ ጥለት ጽንሰ-ሀሳብ ይገኛል። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ስርዓት የሚከሰቱ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን፣ ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን እና ተደጋጋሚና የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን ሀሳብ ማዳበርና የሩቅ አባላቶቻቸውን መገመትን ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የእድገት ስርዓተ ጥለትን ትረዳላችሁ።
- በነባራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ላይ ስርዓተ ጥለቶችን በመጠቀም ትተገብራላችሁ።

6.1 የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን መለየት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ የስርዓተ ጥለት ቀጣይ አባላትን እና የጎደሉ አባላትን ማግኘት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የእድገት ስርዓተ ጥለትን ትለያላችሁ።

ተግባር 6.1

ከዚህ በታች ያሉት ስርዓተ ጥለቶች የመጀመሪያ አባላቶቻቸውን በመመልከት የእነሱን ቀጣይ ሶስት አባላቶቻቸውን ፃፉ።

1. 1፣ 3፣ 5፣ ...

2. 

ማስታወሻ፦

- የእድገት ስርዓተ ጥለት ማለት የአንድ ነገር ቅደም ተከተል ሆኖ በተከታታይ ያሉ አባላት ስርዓት ባለው መልክ በመጨመር ወይም በመቀነስ የሚከሰት

ምሳሌ 6.1

ቀጥለው ያሉ ስርዓተ ጥለቶችን ተመልክታችሁ ቀጣዮቹን ሁለት አባላት በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ቁጥር በመጻፍም ሆነ ስዕል በመሳል መልሱ።

ሀ. 2፣ 4፣ 6፣ ☐ ☐ ለ.1፣ 4፣ 7፣ ☐፣ ☐

ሐ. ☐፣ ☐ ☐ ☐

6.2 ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን ማስቀጠል (ማስፋፋት)

መግቢያ

በንዑስ ምዕራፍ 6.1 ላይ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን እና አባሎቻቸውን እንዴት እንደሚነኙ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የእድገት ስርዓተ ጥለቶችን በስዕላዊ መንገድ ደግማችሁ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለትን ታስቀማጣላችሁ።

ተግባር 6.2

ጥንድ ጥንድ በመሆን ቀጥለው የሚመጡ የስርዓተ ጥለቱን አባላት በመሳል አሳዩ።

1. △□△△□□△△△□□□△△ _____ ____ _____

2.  _____ ____ _____

ማስታወሻ፦

- ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለቶች የራሳቸውን ቀጣይ አባል ስርዓት ባለው ሁኔታ እያባዙ የሚያድጉ በመሆናቸው ቀጣይ አባሎቻቸውን ለማወቅ የመጀመሪያዎቹ አባሎቻቸው እንዴት እያደጉ እንደመጡ በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል።

ምሳሌ 6.2፦

የሚከተሉትን ስርዓተ ጥለቶች ተመልክታችሁ ቀጣይ ሁለት አባላቶቹን በተሰጠው ክፍት ቦታ ሙሉ።

ሀ. ☆ ☆☆ ☆☆ ☆☆☆ ☆☆☆ ☆☆☆ _ _ _

ለ.  ___ ___ ___

መፍትሔ ሀ. ይህ ስርዓተ ጥለት አንድ ረድፍና አንድ ተርታ እየጨመረ የሚያደግ ነው። በመሆኑም

ሀ.  እና ይሆናሉ።

ለ. ይህ ስርዓተ ጥለት ከመነሻው ጀምሮ አንድ ተርታ እየጨመረና በእያንዳንዱ ተርታ ላይ አንድ ጭማረ ጠጠር እየጨመረ የሚያደግ ነው። በመሆኑም

 እና ይሆናሉ።

መልመጃ 6.2

ለሚከተሉት ስርዓተ ጥለቶች ቀጣይ ሁለት አባላቶቹን በተሰጠው ክፍት ቦታ በመሙላት መልሱ።

ሀ.  ___ ___ ___

ለ.  ___ ___ ___

ሐ.  ___ ___ ___

6.3 የተደጋጋሚ እና የእድገት ስርዓተ ጥለቶች የሩቅ አባላቶቻቸው መተንበይ

መግቢያ

በንዑስ ምዕራፍ 6.1 እና 6.2 ላይ ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለቶች ቀጣይ አባሎቻቸው እንዴት እንደምታገኙ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የተደጋገሙ የእድገት ስርዓተ ጥለትን ሩቅ አባላትን እንዴት እንደምናገኝ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሚደጋገሙ እና የእድገት ስርዓተ ጥለት ሩቅ አባላትን ትገምታላችሁ።

ተግባር 6.3

የሚከተለውን ቅደም ተከተል ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብባችሁ ከተረዳችሁ በኋላ ቀጣዩን ክፍት ቦታ ሙሉ።

1. ተማሪ ባንቴ ባናሻ እና ተማሪ ማኑቃ ማጋ ዘውትር ጧት ቁርስ፣ ቀን ምሳ እና ማታ እራት በጋራ ይመገባሉ። ተማሪ አለሙ በተጨማሪ ማምሻውን መክሰስ ይመገባል። ለዚህ የሚገባ ስርዓተ ጥለት በመጠቀም ቀጥለው የሚመጡትን በክፍት ቦታው በመፃፍ መልሱ።

   ሀ. ባንቴ፦ ምሳ እራት – – –

   ለ. አለሙ፦ ቁርስ ምሳ – – –

2. በአንድ ከተማ የሚኖሩ በቴ-እምነቶች ጎብረት በዓመቱ በመስከረም ወርና በሚያዝያ ወር በከተማቸው ያሉ አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት የተቋቋመ ፕሮጀክት አሏቸው። በዚህ መንገድ ይህ ጎብረት ባለፈው ዓመት በሚያዝያ ወር ላይ ከረዷቸው ቀጥሎ በምን ወር ይረዷቸዋል?

ማስታወሻ፦

- አንድ ስርዓተ ጥለት የራሱን የመጀመሪያዎቹን አባላት በተወሰነ ስርዓተ ዑደት እየደጋገመ የሚሄድ ከሆነ ተደጋጋሚ ስርዓተ ጥለት ይባላል። በተጨማሪም የተደጋገመ ስርዓተ ጥለት ስርዓት ባለው መልኩ እየጨመረ ከሄደ ተደጋጋሚ የእድገት ስርዓተ ጥለት ይባላል።

ምሳሌ 6.3፦

1. የሚከተሉትን ስርዓተ ጥለቶች ተመልክታችሁ ቀጥለው የሚመጡትን አባላቶችን ፃፉ።

ሀ. 0 ፣1 ፣00 ፣ 11፣ 000 ፣ 111፣ – ፣ – ፣ –

ለ. 1፣ 0 ፣ 11፣ 0 ፣ 111 ፣ 0 ፣1111 ፣0 ፣– ፣ – ፣ –

2. አንድ የቅቤ ነጋዴ ሰኞ 5 ብር፣ ማክሰኞ 10 ብር እና ረቡዕ 15 ብር አተረፈ። ይህ ነጋዴ በዚህ የማትረፍ ሂደት በቀጣይ ሶስት ቀናት የሚያተርፈውን በቅደም ተከተል ፃፉ።

መፍትሔ፦

1. ሀ. በእያንዳንዱ ዑደት ውስጥ የመጀመሪያቹ 0 እና 1 አባላቶች ላይ አንድ “0” እና አንድ “1” በመጨመር የሚመጣ ድግግሞሽ ነው።

ስለዚህ 0000 1111 00000 11111 ይሆናል።

ለ. በእያንዳንዱ ዑደት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አባላቶች ላይ ከ “0” በመቀጠል አንድ ላይ ተጨማሪ “1” በመጨመር የሚመጣ ድግግሞሽ ነው።

ስለዚህ 11111 0 111111 1111111 ይሆናል።

2. በዚህ የቃላት ፕሮብሌም ውስጥ ነጋዴው ያተረፈው፦

በመጀመሪያው ቀን = 5 ብር = 1×5 ነው።

በሁለተኛው ቀን = 10 ብር = 2×5 ነው።

በሶስተኛው ቀን = 15 ብር = 3×5 ነው። በዚህ ዓይነት ስሌት ስናሰላ በ4ተኛው ቀን = 4×5 = 20 ብር፣ በ5ተኛው ቀን 5×5 = 25 ብር እና በ6ተኛው ቀን 6×5 = 30 ብር ያተርፋል።

መልመጃ 6.3

1. የሚከተለውን ስርዓተ ጥለት ተመልክታችሁ ቀጥለው የሚመጡ አባላትን ፈልጉ።

   ሀ. 0 2 00 22 000 222 ——— እና ———

   ለ. 0 8 0 88 0 888 ——— እና ——— እና የዚህ ስርዓተ ጥለት 10ኛው አባል ——— ነው።

   ሐ. 

የዚህ ስርዓተ ጥለት 100ኛው አባል ——— ነው።

የ101ኛ አባል ——— ነው። የ1,000ኛ አባል ——— ነው።

3. ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ የቀረበውን ስርዓተ ጥለት ተመልክታችሁ ባዶ ቦታውን ሙሉ።

ሳጥኖች	የሳጥኖች ብዛት	ሳጥኖቹ የተሰሩባቸው የክብሪት እንጨቶች ብዛት
□	1	4
□ □	2	7
□ □ □	3	10
□ □ □ □	4	?

□□ □□□	5	?

4. ከዚህ በላይ በጥያቄ ቁጥር 2 ለቀረበው ስርዓተ ጥለት ሳጥኖቹ የሚሰሩባቸውን የክብሪት እንጨቶች ብዛት የሚያሳይ ውል ፈልጉ።
5. በጥያቄ ቁጥር 3 ባገኛችሁት ውል መሰረት 100 ሳጥኖችን ለመስራት ስንት የክብሪት እንጨቶች ያስፈልጋሉ?

የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

- የእድገት ስርዓተ ጥለት ማለት የአንድ ነገር ቅደም ተከተል ሆኖ ተከታታይ አባላቶቹ ስርዓት ባለው መልክ በመጨመር ወይም በመቀነስ የሚከሰት ነው።
- ስዕላዊ የእድገት ስርዓተ ጥለቶች የራሳቸውን ቀጣይ አባላቶች ስርዓት ባለው ሁኔታ እያባዙ የሚያድጉ በመሆናቸው ቀጣይ አባሎቻቸውን ለማወቅ የመጀመሪዎቹ አባሎቻቸው ምን ዓይነት ሁኔታ እያደጉ እንደመጡ በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል።
- አንድ ስርዓተ ጥለት የራሱን የመጀመሪዎቹን አባላት በተወሰነ ስርዓተ ዑደት እየደጋገመ የሚቀጥል ከሆነ የተደጋገመ ስርዓተ ጥለት ይባላል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ስርዓተ ጥለቶች ተመልክታችሁ ቀጣይ አባሎቻቸውን በክፍት ቦታዎች ፃፉ።

   ሀ. 5 ፣ 10 ፣ 15 ፣ 20 ፣ – ፣ – ፣ –

   ለ. 0 ፣ 1 ፣ 0 ፣ 1 ፣ – ፣ – ፣ –

   ሐ. △ ○ △ △ ○ △ △ △ ○ _ _ _

2. በሚከተለው ሰንጠረዥ ስርዓተ ጥለት የተቀመጡ ፊደሎች ተጽፈዋል። በመሐል የጎደሉትን ፊደላት በመሞፍ ሰንጠረዡን ሙሉ።

ሀ	ለ	መ	ሀ	ለ
መ			መ	ሀ

ለ	መ			መ
	ለ		ሀ	ለ
	ሀ	ለ	መ	

3. የሚከተሉትን ስርዓተ ጥለት ቀጣይ ሁለት አባላቶችን በተሰጠው ክፍት ቦታ በመሙላት መልሱ።።



4. ተማሪ ቡራ በቂላ ከ1ኛ ክፍል 1ኛ ስለወጣ 100 ብር፣ ከ2ኛ ክፍል 1ኛ ስለወጣ 150 ብር እና ከ3ኛ ክፍል 1ኛ ስለወጣ 200 ብር አባቱ ሸለመው። ተማሪው በቀጣይ ሶስት ክፍሎች ደረጃውን አስጠብቆ 1ኛ ከወጣ አባቱ በዚህ መንገድ የሚሸለመውን ብር መጠን በቅደም ተከተል ፃፉ።።
5. አንድ ነጋዴ ከሚያገኘው ትርፍ ውስጥ 20 ብር፣ 40 ብር እና 60 ብር በተከታታይ ሶስት ቀናት ቢቆጥብ፤ በቀጣይ ሁለት ቀናት በዚህ ዓይነት ሂደት የሚቆጥበው – እና – ብር ነው።።



7. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማብዛት እና ማካፈል

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ትምህርታችሁ እስከ 1,000 ያሉ ቁጥሮችን ማብዛት እና ማካፈልን ተምራችኋል። ከዚህ በመቀጠል በሶስተኛ ክፍል ደግሞ የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማብዛትን፣ የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማካፈል እና የማብዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ የሙሉ ቁጥሮች እና በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ብዜት ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ❖ እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን በባለ 1-ሆሄ ታባዛላችሁ።
- ❖ እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን በባለ 1-ሆሄ ታካፍላላችሁ።

7.1 የ1,000 ብዜት ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ማባዛት

በሁለተኛ ክፍል በሒሳብ ትምህርታችሁ የ100 ብዜት ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛትን ተምራችኋል። በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ የ1,000 ብዜት ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማብዛትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ባበለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ታባዛላችሁ።

ተግባር 7.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ሥሩ።

ሀ. $\begin{array}{r} 1{,}000 \\ \times\ 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 1{,}000 \\ \times\ 4 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 1{,}000 \\ \times\ 7 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 1{,}000 \\ \times\ 9 \\ \hline \end{array}$

2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ በመጻፍ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ። ደብተራችሁን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመቀያየር የሰራችሁትን መልስ በውይይት አረጋግጡ።

×	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
1,000										

3. የ1,000 ብዜቶች ሁሉ የ100 ብዜቶች ናቸውን? ካልሆኑ ለምን?

ማስታወሻ፦

1. ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት አንድን ቁጥር ደጋግሞ የመደመር አጭር መንገድ ነው።
2. ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ፤ ሀ × ለ = መ በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሀ እና ለ የ"መ" አብዥዎች ሲሆኑ፤ መ ደግሞ የሀ እና የለ ብዜት ነው።
3. የ1,000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በቀላሉ አባዝቶ ለማግኘት በሺህ ቤት የሚገኘውን ሆሄ በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር አባዝቶ ከሚገኘው ውጤት በስተቀኝ ሦስት ዜሮች መጻፍ ነው።

ምሳሌ 7.1፦

1. $20 + 20 + 20 + 20 + 20 = 100$ የሚለውን በአጭሩ $5 \times 20 = 100$ በማለት ውጤቱን ማግኘት ይቻላል።

ምሳሌ 7.2፦

የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $2 \times 1{,}000$ ለ. $3\times 2{,}000$ ሐ. $5 \times 1{,}000$

መፍትሔ፦

ሀ. $2 \times 1{,}000$ ለማባዛት በሺህ ቤት የሚገኘውን "1"ን በ "2" ማባዛት

$2 \times 1 = 2$ ከዚያም ከውጤቱ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መጻፍ፤

ስለሆነም 2,000 ይሆናል። ስለዚህ $2 \times 1{,}000 = 2{,}000$ ነው።

ለ. $3\times 2{,}000$ ለማባዛት በመጀመሪያ በሺህ ቤት የሚገኘውን "2"ን በ "3" ማባዛት

ይህም $2 \times 3 = 6$ ይሆናል። ከዚያም ከውጤቱ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መጻፍ፤

ስለሆነም 6,000 ይሆናል። ስለዚህ $3 \times 2,000 = 6,000$ ነው።

ሐ. $5 \times 1,000$ ለማባዛት በመጀመሪያ በሺህ ቤት የሚገኘውን "1"ን በ "5" ማባዛት

$5 \times 1 = 5$ ከዚያም ከውጤቱ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መጻፍ፤

ስለሆነም 5,000 ይሆናል። ስለዚህ $5 \times 1,000 = 5,000$ ነው።

ምሳሌ 7.3፦

ከሚከተሉት ቁጥሮች የ1,000 ብዜት የሆኑት የትኛዎቹ ናቸው?

ሀ. 600 ለ. 3,000 ሐ. 560

መፍትሔ፦

ሀ. 600 የ1,000 ብዜት አይደለም። ምክንያቱም የ600 የመጨረሻ ሦስት ሆሄያት ዜሮ አይደሉም።

ለ. 3,000 የ1,000 ብዜት ነው። ምክንያቱም የመጨረሻ ሦስት ሆሄያት ዜሮ በመሆናቸው።

ሐ. 560 የ1,000 ብዜት አይደለም። ምክንያቱም የ560 የመጨረሻ ሦስት ሆሄያት ዜሮ አይደሉም።

መልመጃ 7.1

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $2 \times 1,000$ ሐ. $2 \times 3,000$ ሠ. $2 \times 5,000$

ለ. $3 \times 2,000$ መ. $1 \times 7,000$

2. የሚከተለውን የአብዝቦ ሰንጠረዥ አሟሉ።

×	4	5	6	7	8
1,000					

3. የሚከተለውን የአብዥር ሰንጠረዦችን አሟሉ።

ሀ.

×	2
1,000	
2,000	
3,000	
4,000	
5,000	

ለ.

×	3
1,000	
2,000	
3,000	

4. ትንሹ የ1,000 ብዜት ቁጥር ስንት ነው?

7.2 የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማካፈል

መግቢያ

በምዕራፍ አራት እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮዎችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማካፈል ተምራችኋል። በተካፋይ፣ አካፋይ እና ድርሻ መካከል ያለውን ዝምድናም መማራችሁ ይታወሳል። አሁን ደግሞ የ10 እና የ100 ብዜት ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማካፈልን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ታካፍላላችሁ።

ተግባር 7.2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ሥሩ።

ሀ. 100 ጠጠሮችን በ2 እኩል ቦታ ብመደቡ በእያንዳንዱ ምድብ ስንት ጠጠሮች ይኖራሉ?

ለ. አንድ ትምህርት ቤት በሽልማት ወቅት 100 ደብተሮች ለ5 ጎበዝ ተማሪዎች እኩል ለእያንዳንዳቸው ብሸልሚቸው ስንት ስንት ደብተር ይደርሳቸዋል?

ሐ. የአንድ ጎብረት ሥራ ማህበር 400 እንቁላል የሚጥሉ ዶሮዎችን ገዝቶ ለ8 የማህበሩ አባላት እኩል አከፋፈሉ። ለእያንዳንዱ የማህበሩ አባል ስንት ዶሮዎች ይደርሳል?

2. የሚከተሉትን አካፍሉ።

ሀ. $10 \div 2 =$ _____ ሐ. $100 \div 5 =$ _____ ሠ. $800 \div 4 =$ _____

ለ. $40 \div 8 =$ _____ መ. $300 \div 3 =$ _____ ረ. $500 \div 5 =$ _____

ማስታወሻ፦

- የ10 ወይም የ100 ብዜቶች የሆነውን ማንኛውም በባለ 1 ሆዜ ቁጥር ለማካፈል፤ ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ሆነው ለ ≠ 0 ቢሆንና ሀ ÷ ለ = መ እውነት ከሆነ "ሀ" ተከፋይ፣ "ለ" አካፋይ እና "መ" ድርሻ ይባላሉ።
  ተካፋይ = (ድርሻ) × (አካፋይ) ይሆናል። ይህም ሀ = መ × ለ ይሆናል።

ምሳሌ 7.4፦

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ። መልሳችሁንም በማብዛት ስለት አረጋግጡ።

ሀ. $100 \div 2 =$ _____ ሐ. $200 \div 5 =$ _____

ለ. $40 \div 4 =$ ____ መ. $600 \div 6 =$ _____

መፍትሔ፦

ሀ. $10 \div 2 = 5$ ምክንያቱም $10 = 2 \times 5$ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ተካፋይ 10፣ አካፋይ 2 እና ድርሻ 5 ይሆናል።

ለ. $40 \div 4 = 10$ ምክንያቱም $40 = 4 \times 10$ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ተካፋይ 40፣ አካፋይ 4 እና ድርሻ 10 ይሆናል።

ሐ. $200 \div 5 = 40$ ምክንያቱም $200 = 5 \times 40$ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ተካፋይ 200፣ አካፋይ 5 እና ድርሻ 40 ይሆናል።

መ. $600 \div 6 = 100$ ምክንያቱም $600 = 6 \times 100$ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ተካፋይ 600፣ አካፋይ 6 እና ድርሻ 100 ይሆናል።

መልመጃ 7.2

1. የሚከተሉትን አስሉ። መልሶቻችሁን በማብዛት አረጋግጡ።

ሀ. $50 \div 5$ ሐ. $120 \div 6$ ሠ. $400 \div 8$

ለ. $80 \div 4$ መ. $180 \div 3$ ረ. $7{,}200 \div 9$

2. የሚከተሉትን አስሉ። ለእያንዳንዳቸው ተካፋዩን፣ አካፋዩን እና ድርሻውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ሀ. $90 \div 3$ ሐ. $210 \div 3$

ለ. $140 \div 2$ መ. $300 \div 5$

3. ወይዘሮ ሉባብ፣ አቶ አለማየሁ እና ወጣት ማቴዎስ ጎበዝ አርሶ አደሮች ናቸው። ሦስቱም በጋራ በመስኖ ያመረቱትን የበጋ ስንዴ ከሸጡት ብር

የቆጠቡትን 9,000 ብር እኩል ቢከፋፈሉ የአንዱ አርሶ አደር ድርሻ ስንት ብር ይሆናል?

7.3 የማብዛት ውጤታቸው ከ10,000 ያልበለጡ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል በሒሳብ ትምህርታችሁ ብዜታቸው ከ100 የማይበልጡ የሙሉ ቁጥሮች እና የባለ 1 ሆሄያት ማባዛትን ተምራችኋል። ቀጥሎም በሦስተኛ ክፍል በሒሳብ ትምህርታችሁ በንዑስ ምዕራፍ 3.1፣ 3.2 እና በንዑስ ምዕራፍ 7.1 ላይ የ10፣ የ100 እና የ1,000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ብዜታቸው ከ10,000 ያልበለጡ ሙሉ ቁጥሮች እና የባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ተግባር 7.3 ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ታባዛላችሁ።

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ሥሩ።

ሀ. $800 \times 2 =$ _____ ሐ. $314 \times 2 =$ _____ ሠ. $3,241 \times 2 =$ ____

ለ. $120 \times 3 =$ _____ መ. $3,142 \times 2 =$ ____ ረ. $1,654 \times 2 =$ ____

ማስታወሻ ፦

1. በባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ከባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ጋር **ያለ አለችታ ሲባዛ፦** የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በአንድ ቤት ማጻፍ። የ10 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤቱን በ10 ቤት መጻፍ። የ100 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤቱን በ100 ቤት መጻፍ። የ1,000 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤቱን በ1,000 ቤት መጻፍ።
2. በባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ከባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ጋር **በአለችታ ሲባዛ፦**

- የ1 ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘውን ውጤት የ1 ቤት ሆሄውን በ1 ቤት ጽፎ የ10 ቤት ሆሄውን አለችታ ብሎ ማቆየት

- የ10 ቤት ሆሄውን አባዝቶ ውጤቱን አለኝታ ከተባለው ጋር መደመር እና መልሱን በ10 ቤት ስር መፃፍ።
- ቀጥሎ የ100 ቤት ሆሄውን አባዝቶ ውጤቱን አለኝታ ከተባለው ጋር መደመር እና መልሱን በ100 ቤት ስር መፃፍ።
- በመጨረሻም የ1,000 ቤት ሆሄውን ማባዛት በአለኝታ የቆየ ካለ ከውጤቱ ጋር ደምሮ በ1,000 ቤት ወይም በ1,000 እና በ10,000 ቤት ስር መፃፍ።

ምሳሌ 7.5፦

1. የሚከተሉትን አባዙ::

ሀ. $\begin{array}{r} 3{,}401 \\ \times\ \ 2 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 4{,}013 \\ \times\ \ 2 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 2{,}351 \\ \times\ \ 3 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 4{,}627 \\ \times\ \ 2 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ፦

ሀ. $\begin{array}{r} 3{,}401 \\ \times\ \ 2 \\ \hline \end{array}$

- በቤት ቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታቸው ስር መፃፍ፤ በመሆኑም፦
- 2 × 1 = 2 2ን በ1 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 0 = 0 0ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 4 = 8 8ን በ100 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 3 = 6 6ን በ1,000 ቤት ስር መፃፍ፤

ስለዚህ $\begin{array}{r} 3,401 \\ \times\ \ 2 \\ \hline 6,802 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም ያለ አለኝታ የተባዛ ነው)::

ለ. $\begin{array}{r} 4,013 \\ \times\ \ 2 \\ \hline \end{array}$ በቤት ቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታቸው ስር መፃፍ፤በመሆኑም፦

- 2 × 3 = 6 6ን በ1 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 1 = 2 2ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 0 = 0 0ን በ100 ቤት ስር መፃፍ፤
- 2 × 4 = 8 8ን በ1,000 ቤት ስር መፃፍ፤

ስለዚህ $\begin{array}{r} 4,013 \\ \times\ \ 2 \\ \hline 8,026 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም ያለ አለኝታ የተባዛ ነው)::

ሐ. $\begin{array}{r} 2,351 \\ \times\ \ 3 \\ \hline \end{array}$ በቤት ቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታቸው ስር መፃፍ፤

- 3 ×1 = 3 3ን በ1 ቤት ስር ፅፎ “1”ን በአለኝታ ወይም በተሻጋሪነት ማቆየት፤
- 3 × 5 = 15 “15”ን አለኝ ካለነው ከ1 ጋር መደመር 15 +1 = 16 “6”ን በ10 ቤት ስር መፃፍ እና “1”ን በአለኝ ማቆየት፤
- 3 × 3 = 9 “9”ን በአለኝታ ካቆየነው ከ“1” ጋር በመደመር 9 + 1 = 10 ከዚያም “0”ን በ100 ቤት ፅፎ “1”ን በለኝታ ማቆየት፤
- 3 × 2 = 6 “6”ን በአለኝታ ካቆየነው ከ“1” ጋር በመደመር 6 + 1 = 7 ከዚያም “7”ን በ1,000 ቤት መጻፍ፤
- ስለዚህ $\begin{array}{r} 2,351 \\ \times\ \ 3 \\ \hline 7,053 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም በአለኝታ የተባዛ ነው)::

መ. $\begin{array}{r} 4,627 \\ \times \quad 2 \\ \hline \end{array}$ በቤት ቤታቸው አባዝቶ ውጤቱን በየቤታቸው ስር መፃፍ፤

- $2 \times 7 = 14$ “4”ን በ1 ቤት ስር ዕፎ “1”ን በአለኝታ ወይም በተሻጋሪነት ማቆየት፤
- $2 \times 2 = 4$ “4”ን አለኝ ካለነው ከ1 ጋር መደመር 4 +1 = 5 ከዚያም“5”ን በ10 ቤት ስር መፃፍ፤
- $2 \times 6 = 12$ “12”ን በአለኝታ ያቆየነው ቁጥር ስለለሌ “2”ን በ100 ቤት ዕፎ “1”ን በለኝታ ማቆየት፤
- $2 \times 4 = 8$ “8”ን በአለኝታ ካቆየነው ከ“1” ጋር በመደመር 8 + 1 = 9 ከዚያም “9”ን በ1,000 ቤት መጻፍ፤
- ስለዚህ $\begin{array}{r} 4,627 \\ \times \quad 2 \\ \hline 9,254 \end{array}$ ይሆናል (ብዜቱም በአለኝታ የተባዛ ነው)::

ማስታወሻ፦
ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ አባዝቶ ከማስቀመጥ በፊት የቁጥሩን በስተግራ በኩል ያለውን ሆሄ ብቻ ወስዶ በቀሪ ሆሄያት ቦታ ዜሮ በመፃፍ ከተሰጠው ባለ 1 ሆሄ ጋር በማባዛት ብዜቱን መገመት ይቻላል።

ምሳሌ 7.6፦

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች የብዜት ዋጋቸውን ገምቱ::

ሀ. 312×5 ለ. 209×6

መፍትሔ 7.6፦

ሀ. 312×5 ይህንን ብዜት ለመገመት በመጀመሪያ “300”ን በ5 ማባዛት፤

ይኸውም $300 \times 5 = 1{,}500$

ስለዚህ 312×5 ብዜቱ በግምት 1,500 አካባቢ ነው።

ለ. 209×6 ይህንን ብዜት ለመገመት በመጀመሪያ “200”ን በ6 ማባዛት፤

ይኸውም $200 \times 6 = 1{,}200$

ስለዚህ 209×6 ብዜቱ በግምት 1,200 አካባቢ ነው።

መልመጃ 7.3

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. $420 \times 3 =$ _____ ሐ. $3{,}568 \times 2 =$ ____ ሠ. $981 \times 7 =$ __

ለ. $4{,}008 \times 2 =$ _____ መ. $598 \times 4 =$ ____ ረ. $1{,}806 \times 5 =$ ____

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች የብዜት ዋጋቸውን ገምቱ።

ሀ. $609 \times 3 =$ _____ ለ. $452 \times 2 =$ _____ ሐ. $308 \times 7 =$ ____

3. አቶ ሳሙኤል ለአምስት ልጆቹ ለእያንዳንዳቸው በየወሩ 35 ብር በኡሞ ማይክሮ ፋይናንስ በኩል ይቆጥባል። በስምንት ወር በጠቅላላ ስንት ብር አቶ ሳሙኤል ለልጆቹ ይቆጥባል?

4. አንድ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች አርቢ በየቀኑ 825 እንቁላሎችን ያገኛል። ይህ አርቢ በስድስት ቀናት ውስጥ ስንት እንቁላሎችን ያገኛል?

7.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች እና በ10 ማካፈል

መግቢያ

ከዚህ በፊት በምዕራፍ አራት እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ2፣ ለ3፣ 4፣5፣ 6፣ 7፣8፣ 9 እና ለ10 ማካፈልን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች እና በ10 ማካፈልን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር እና ለ10 ታካፍላላችሁ።

ተግባር 7.4

1. የሚከተሉትን አስሉ፤ መልሶቻችሁንም በማብዛት አረጋግጡ።

   ሀ. 360 ÷ 10　　ሐ. 1,600 ÷ 2　　ሠ. 100 ÷ 10

   ለ. 300 ÷ 5　　መ. 600 ÷ 6　　ረ. 1,200 ÷ 3

2. አቶ ዮሐንስ 5 የቀን ሰራተኞችን ቀጥሮ አሰርተው በስተመጨረሻ ለአምስቱ ሰራተኞች 600 ብር ቢሰጡ ለእያንዳንዳቸው ስንት ብር ይደርሳቸዋል?
3. 50 ጠጠሮችን 10 እኩል ቦታ እንደሚከተለው ቢመደቡ። በእያንዳንዱ ምድብ የሚገኙ ጠጠሮች ስንት ናቸው?



4. 63 አፕሎችን ስድስት ልጆች እኩል ቢከፋፈሉ የእያንዳንዱ ልጅ ድርሻ ስንት አፕሎች ይሆናሉ? ቀሪ ስንት ይሆናል?



ማስታወሻ፦

- ቀሪ የሚያስከትሉ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲካፈሉ ድርሻውንና ቀሪውን በቀላሉ ለማወቅ፦
  ተካፋዩን በአካፋዩ ብዜት እና ከአካፋዩ በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለፅ፣ ከዚያም የማካፈሉን ስራ በመቀጠል ድርሻ እና ቀሪውን ማግኘት ነው።

ምሳሌ 7.7፦

1. የሚከተሉትን አካፍሉ::

   ሀ. $29 \div 4$ ለ. $34 \div 5$

መፍትሔ፦

ሀ. $29 \div 4 = (28 + 1) \div 4 \leftrightarrow$ "29"ን በ4 ብዜት እና ከ4 በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለጽ፤

$= (28 \div 4) + (1 \div 4)$

$= 7 + (1 \div 4)$ "1" ከ4 ስለሚያንስ "1"ን ለ4 ማካፈል ተግባራዊ አይሆንም፤

$= 7$ ቀሪ 1

ስለዚህ $29 \div 4 = 7$ ቀሪ 1 ይሆናል።

ለ. $34 \div 5 = (30 + 4) \div 5 \leftrightarrow$ "34"ን በ5 ብዜት እና ከ5 በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለጽ፤

$= (30 \div 5) + (4 \div 5)$

$= 6 + (4 \div 5)$ “4” ከ5 ስለሚያንስ “4”ን ለ5 ማካፈል ተግባራዊ አይሆንም፤

$= 6$ ቀሪ 4

ስለዚህ $34 \div 5 = 6$ ቀሪ 4 ይሆናል።

ማስታወሻ፦

- ማንኛውም ባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ለ10 ሲካፈል ድርሻው ዜሮ ሆኖ ቀሪው የተሰጠው ባለ 1 ሆሄ ቁጥር ይሆናል።
- ባለ 2 ሆሄ እና ከዚያም በላይ ሆሄያት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮዎች ለ10 ሲካፈሉ የ1 ቤት ሆሄው ቀሪ ስሆን የቀሩት ሆሄያት ድርሻ ይሆናሉ።
- የማካፈል ጽንሰ-ሀሳብ እኩል ድርሻ መካፈል ነው።
- በባለ ሦስት ሆሄ እና ባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥሮች ለማካፈል ረዥም የማካፈል ዘዴን መጠቀም የተሻለ ነው።

ምሳሌ 7.8፦

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ. $5 \div 10$ ሐ. $865 \div 10$ ሠ. $88 \div 4$ ሰ. $582 \div 5$

ለ. $28 \div 10$ መ. $27 \div 3$ ረ. $428 \div 2$

መፍትሔ፦

ሀ. $5 \div 10$ ድርሻው "0" ስሆን ደግሞ "5" ቀሪ ይሆናል።

ለ. $28 \div 10$ ድርሻው "2" ስሆን ደግሞ "8" ቀሪ ይሆናል።

ሐ. $865 \div 10$ ድርሻው "86" ስሆን ደግሞ "5" ቀሪ ይሆናል።

መ. $27 \div 3$ በመጀመሪያ ሦስቱን ተካፋዮችን ወደ ጎን ደርድሮ የእያንዳንዳቸውን ድርሻ ማደል፤ ይኸው

1 2 3 → ሦስቱ ተጋሪዎች
5 5 5 በመጀመሪያ እኩል አምስት አምስት ለእያንዳንዳቸው ማደል፤ ከዚያም 12 ይቀራል።
4 4 4 ቀጥሎም የቀረውን 12 እኩል አራት አራት ማደል ስሆን የእያንዳንዱ ተጋሪ ድርሻ $5 + 4 = 9$ ይሆናል።

ሠ. $88 \div 4$ በመጀመሪያ አራቱን እኩል ተጋሪዎችን ወደ ጎን ደርድሮ የእያንዳንዳቸውን ድርሻ ማደል፤ ይኸውም

1	2	3	4	→ አራቱ ተጋሪዎች
10	10	10	10	በመጀመሪያ እኩል አስር አስር ለእያንዳንዳቸው ማደል፤ ከዚያም 48 ይቀራል።
10	10	10	10	ቀጥሎም እኩል አስር አስር ለእያንዳንዳቸው ማደል፤ ከዚያም 8 ይቀራል።
2	2	2	2	በስተመጨረሻም የቀረውን 8 እኩል ሁለት ሁለት ማደል ስሆን የእያንዳንዱ ተጋሪ ድርሻ 10 + 10 + 2 = 22 ይሆናል።

234

ሰ 2 | 468

- 4 4 ለ2 ስካፈል ድርሻው 2 ነው። "2"ን ከምልክቱ ላይኛው ቦታ መጻፍ፤
6 ከዚያም "2"ን በ2 አባዝቶ ከ4 ግርጌ መጻፍና መቀነስ 4 — 4 = 0፤
- 6 ከቀነስን በኋላ "6"ን ቀጥታ ወደ ታች በቤቱ ከመስመሩ በታች አውርዶ
8 መጻፍ "6"ን ለ2 ማካፈልና ድርሻውን ከውጤት መጻፊያው ከ"2" በስተቀኝ
- 8 መጻፍ፤ "3"ን በ2 አባዝቶ ከ6 ላይ መቀነስ 6 —(3X2) = 6 - 6 = 0
0 ከተካፋዩ የቀረውን "8"ን ከመስመሩ በታች በቤቱ አውርዶ መጻፍ፤
"8"ን ለ2 ማካፈልና ድርሻውን ከውጤት መፃፊያ ቦታ ላይ ከ"23"
በስተቀኝ መጻፍ፤ 8 ÷ 2 = 4 "4"ን በ2 አባዝቶ ከ8 ላይ መቀነስ
8 — 8 = 0። ስለዚህ 468 ÷ 2 = 234 ይሆናል።

116

ረ 5 | 582

- 5 5 ለ5 ስካፈል ድርሻው 1 ነው። "1"ን ከምልክቱ ላይኛው ቦታ መጻፍ፤
8 ከዚያም "1"ን በ5 አባዝቶ ከ5 ግርጌ መጻፍና መቀነስ 5 — 5 = 0፤
- 5 ከቀነስን በኋላ "8"ን ቀጥታ ወደ ታች በቤቱ ከመስመሩ በታች አውርዶ
32 መጻፍ "8"ን ለ5 ማካፈልና ድርሻውን ከውጤት መጻፊያው ከ"1" በስተቀኝ
- 30 መጻፍ፤ "1"ን በ5 አባዝቶ ከ8 ላይ መቀነስ 8 —(5X1) = 8 - 5 = 3
2 ከተካፋዩ የቀረውን "2"ን ከ3 በስተቀኝ መጻፍ፤ "32"ን ለ5 ማካፈልና
ድርሻው "6" ከ"11" በስተቀኝ መጻፊያው ላይ መጻፍ፡ 6ን በ5 አብዝቶ
ከ32 ውጤቱን ቀንሶ 30 — 30 = 2 ከ5 ስለሚያንስ 2 ቀሪ ይሆናል።
ስለዚህ 582 ÷ 5 = 116 ቀሪ 2 ነው።

መልመጃ 7.4

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 18 ÷ 5 ሐ.9 ÷ 10 ሠ. 365 ÷ 10 ሰ. 825 ÷ 4 ቀ. 2,684 ÷ 2

ለ. 18 ÷ 6 መ. 26 ÷ 10 ረ. 268 ÷ 3 ሸ. 9,256 ÷ 10

2. አንድ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ለ7 ሲካፈል ድርሻው 6 ቀሪው ደግሞ 4 ቢሆን ቁጥሩ ስንት ነው?
3. 30 ብርቱካኖች ለ5 ልጆች እኩል ቢካፈሉ እያንዳንዳቸው ስንት ብርቱካኖች ይደርሳቸዋል?
4. ሁለት ደላሎች በጋራ ደልለው አንድ ቤት አሻሽጠው ያገኙትን 10,000 ብር እኩል ቢካፈሉ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

- ባለ 2 ሆሄ፣ ባለ 3 ሆሄ ወይም ባለ 4 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ጋር በአለኝታ እና ያለ አለኝታ ሲባዛ
  - ❖ ከ 1 ቤት ሆሄው በመጀመር በቤት ቤታቸው ማብዛት፤
  - ❖ የተገኘውን ውጤት በቤት በቤት አድርጎ መጻፍ፤ አለኝታ ያለው ከሆነ "አለኝታ" የተባለውን ሆሄ ከሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄ ብዜት ጋር መደመር ይሆናል።

- የ1,000 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በቀላሉ አባዝቶ ለማግኘት በሺህ ቤት የሚገኘውን ሆሄ በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር አባዝቶ ከሚገኘው ውጤት በስተቀኝ ሦስት ዜሮዎችን መጻፍ ነው።
- የ10 ወይም የ100 ብዜቶች የሆነውን ማንኛውም በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ለማካፈል፤ $ሀ$፣ $ለ$ እና $መ$ ሙሉ ቁጥሮች ሆነው $ለ \neq 0$ ቢሆንና $ሀ \div ለ = መ$ እውነት ከሆነ "$ሀ$" ተከፋይ፣ "$ለ$" አካፋይ እና "$መ$" ድርሻ ይባላሉ።

  ተካፋይ = (ድርሻ) × (አካፋይ) ይሆናል። ይህም $ሀ = መ \times ለ$ ይሆናል።
- በባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር **ያለአለኝታ ሲባዛ**፡ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በአንድ ቤት መጻፍ። የ10 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤቱን በ10 ቤት መጻፍ። የ100 ቤት ሆሄን አባዝቶ

የሚገኘውን ውጤቱን በ100 ቤት መጻፍ። የ1,000 ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤቱን በ1,000 ቤት መጻፍ።

- በባለ አራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በአለኝታ ሲባዛ የ1 ቤት ሆሄን አባዝቶ ከሚገኘውን ውጤት የ1 ቤት ሆሄውም በ1 ቤት ጽፎ የ10 ቤት ሆሄውን አለኝታ ብሎ ማቆየት ነው።
- ቀሪ የሚያስከትሉ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲካፈሉ ድርሻውንና ቀሪውን በቀላሉ ለማወቅ

  ተካፋዩን በአካፋዩ ብዜት እና ከአካፋዩ በሚያንስ ሙሉ ቁጥር ድምር መግለፅ፣ ከዚያም የማካፈሉን ስራ በመቀጠል ድርሻ እና ቀሪውን ማግኘት ነው።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።

   ሀ. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ10 ሲካፈል ድርሻው 368 ከሆነ ቁጥሩ 3,680 ነው።

   ለ. አንድ ሙሉ ቁጥር ለ2 ሲካፈል ድርሻው 13 ከሆነ እና ቀሪው 1 ከሆነ ቁጥሩ 27 ነው።

   ሐ. ማንኛው የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር በባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስባዛ ውጤቱ የ1,000 ብዜት ይሆናል።

2. የሚከተሉትን አስሉ።

   ሀ. $2,000 \times 3$ ሐ. $4,000 \times 2$ ሠ. $800 \div 4$ ሰ. $9,625 \div 2$

   ለ. $3,000 \times 3$ መ. $20 \div 3$ ረ. $2,680 \div 10$ ሸ. 284×5

3. አንድ አርሶ አደር ሁለት ኩንታል በቆሎ ገበያ አውጥቶ ሸጠ። የአንዱ ኩንታል ዋጋ 3,000 ብር ቢሆን ጠቅላላ በቆሎውን ሸጦ ያገኘው ብር ስንት ነው?

4. አንድ የቆዳ እና ለጦ ፋብርካ በቀን ውስጥ 850 ጥንድ ጫማዎችን ያመርታል። ይህ ፋብርካ በዘጠኝ ቀናት ውስጥ ስንት ጥንድ ጫማዎችን ያመርታል?

5. የሚከተሉትን የአብዥር ሰንጠረዥር አሚሉ።

×	8	7	6	4	5	1	2	9	10
1,000									

6. የሚከተሉትን የማካፈል ሰንጠረዥር አሚሉ።

÷	2	4	10
2,000			
3,680			

ምዕራፍ ስምንት

8. የመረጃ አያያዝ

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ትምህርታችሁ መረጃ መሰብሰብ እና መረጃን በምስሎች ግራፍ ማክፋፈልን መማራችሁ ይታወሳል። አሁን ደግሞ የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት መረጃ አያያዝን የሚመለከት ይሆናል። ምዕራፉ በዋናነት በሁለት ንዑስ ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን እነሱም የምስሎች ግራፍና የምስሎችን ግራፍ ማንበብና መግለጽ ናቸው። በምስሎች ግራፍ የሚካተቱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ግራፎችን መሳል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የምስሎች ግራፍ ማንበብና መግለጽን ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ስዕላዊ ግራፎችን እንዴት እንደሚንገለጽ ትረዳላችሁ።
- በነባራዊ የኑሮ ሁኔታዎች ላይ የምስል ግራፍን በመጠቀም ትተግብራላችሁ።

8.1 የምስል ግራፎች

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ መረጃ መሰብሰብና መረጃን በምስሎች ግራፍ ማክፋፈልን ተምራችኋል። አሁን ደግም በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የምስሎች ግራፍን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በወለል ላይ፣ በጠርጴዛ ላይ ወይም በሳጥኖች ውስጥ የፍራፍሬ ምስሎችን መጠቀምን የመሳሰሉ የስዕል ግራፎችን ትሰራላችሁ።

ተግባር 8.1

1. በቤታችሁ ውስጥ ስንት ኩባያ፣ ሲኒና መቀመጫ እንዳለ መዝግባችሁ ቁጥራችውን ግለጹ።
2. ቤተሰቦቻችሁ ለእናንተ የሚገዙትን የፍራፍሬ ዓይነቶችን ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።
3. ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንድ ብር ሳንቲም ዲናርን 24 ጊዜ ወደ ላይ በመወርወር የሚመጣውን ሚዛን ወይም አንበሳ ምስል መዝግባችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ
4. ከእናንተ ቤት ጎን አንድ ቤት ወስዳችሁ ስንት ወንዶችና ሴቶች እንዳሉ መዝግባችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር መረጃውን ተነጋገሩ።
5. ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ለሰበሰባችሁት መረጃ የምስል ግራፍ ሳሉ።

ማስታወሻ፦

- የምስል ግራፍን ለመሳል መጀመሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት ያስፈልጋል።
- ምስላዊ ግራፍ እውነታዎችን (ድርጊቶችን) በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል።
- በምስላዊ ግራፍ አንድ ምስል የተለያዩ መጠን ያላቸውን ነገሮች ሊወክል ይችላል።
- አንድ ምስል 1፣ 2፣ 4፣ 5፣ 8 ወይም ሌሎች መጠኖችን ሊወክል ይችላል።

ምሳሌ 8.1፦

በቤተሰቦቻችሁ የሚወዷቸውን የፍራፍሬ ዓይነቶች ጠይቃችሁ ስትመዘግቡ የሚከተለውን ውጤት አግኝታችሁ ይሆናል። ማንጎ የሚወዱ 5፣ አቮካዶ የሚወዱ 3፣ ብርቱካን የሚወዱ 2 እና ሎሚ የሚወዱ 1 ናቸው። ይህን መረጃ ይዘን ግራፍ በመጠቀም በሚከተለው መንገድ ሊገለጽ ይችላል።

የፍራፍሬ ዓይነት	ፍራፍሬን የሚወዱ ቤተሰቦች
ማንጎ	
አቮካዶ	
ብርቱካን	
ሎሚ	

መልመጃ 8.1

5. አንድ የሱቅ መደብር ነጋዴ 5 ደርዘን ሳሙና፣ 20 ደርዘን ማስቲካ፣ 15 ደርዘን ብዕር፣ 30 ደርዘን ኮሾሮ እና 40 ደርዘን ከረሜላ ሸጧል። መረጃን ተጠቅማችሁ የምስል ግራፍ ሳሉ። (አንድ ምስል 5 ደርዘን እንደሚወክል አድርጋችሁ ተጠቀሙ)።
6. ጥንድ ጥንድ በመሆን የአንድ ብር ሳንትም 30 ጊዜ ወደ ላይ በመወርወር የመዘገባችሁትን መረጃ በምስል ግራፍ በመሳል አሳዩ።
7. አንድ አርሶ አደር ችግኝ ለመተክል አሰበ። አርሶ አደሩ በሚያዝያ ወር 80 ችግኞች፣ በግንቦት ወር 60 ችግኞች፣ በሰኔ ወር 40 ችግኞች እና በሐምሌ ወር 100 ችግኞቹን ተክሏል። መረጃውን ተጠቅማችሁ የምስል ግራፍ ሳሉ። (አንድ ምስል 10 ችግኞች እንደሚወክል አድርጋችሁ ተጠቀሙ)።
8. በአንድ ወረዳ ውስጥ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ አካባቢዎች፦ አካባቢ አንድ 6 ሰዎች፣ አካባቢ ሁለት 8 ሰዎች፣ አካባቢ ሶስት 4 ሰዎች፣ አካባቢ አራት 12 ሰዎች እና

አካባቢ አምስት 6 ሰዎች አሉ። መረጃዎችን ተጠቅማችሁ የምስል ግራፍ ሳሉ። (አንድ ሰው ምስል 2 ሰዎችን ይወክላል)።

9. በአንድ ሕክምና ጣቢያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላላሽ ታካሚዎች ብዛት ከዚህ በታች በተሰጠው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

የበሽታው ዓይነት	የደም ግፊት	ኤች አይቪ ኤድስ	ቲቪ	የልብ ህመም
የታካሚ ብዛት	25	15	30	10

ሀ. በሰንጠረዥ ላይ የተሰጠውን መረጃ በምስል ግራፍ ግለጹ።

ለ. ከፍተኛ ቁጥር ተመላላሽ ታካሚ ያለበት የበሽታ ዓይነት የትኛው ነው?

ሐ. ዝቅተኛ ቁጥር ተመላላሽ ታካሚ ያለበት የበሽታ ዓይነት የትኛው ነው?

መ. በወሩ ውስጥ የሚኖረው ጠቅላላ ታካሚ ብዛት ስንት ነው?

8.2 የምስል ግራፎችን ማንበብና መግለጽ

መግቢያ

መረጃዎችን በምስል ግራፍ መሳል በንዑስ ርዕስ 8.1 ተምራችኋል። አሁን ደግም በዚህ ንዑስ ምዕራፍ መረጃዎችን ከምስሎች ግራፍ ማንበብና መግለጽ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የእያንዳንዱ መረጃ ምድብ ቁጥር በጣም ትልቅ፣ በጣም ትንሽ ብሎም በከፍተኛው እና በዝቅተኛው መካከል ያለው ምን ያህል ልዩነት እንደሆነ ትናገራላችሁ።

ተግባር 8.2

1. ከዚህ በታች ያለውን ምስላዊ ግራፍ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተመልከቱና ጥያቄዎችን መልሱ። ምስላዊ ግራፉ አንድ ሕንፃ መሣሪያዎች ባለበት የሽጡት የፓኬት ሚስማር መጠን ያሳያል። አንድ ምስል 10 ፓኬት ሚስማር ይወክላል።

ሰኞ	
ማክሰኞ	
ሐሙስ	
ዓርብ	
ቅዳሜ	

ሀ. ሰኞ ዕለት ስንት ሚስማሮች ተሸጠ?

ለ. ከዕለታት ውስጥ ብዙ ፓኬት ሚስማር የተሸጠበት በምን ቀን ነው? ብዛት ስንት ነው?

ሐ. እኩል ፓኬት ሚስማር የተሸጡበት እለታት በየትኞቹ ቀናት ነው? ስንት ፓኬት ተሸጠ?

መ. በአምስት ቀናት ውስጥ የተሸጡት የሚስማር ፓኬቶች ብዛት በጠቅላላ ስንት ናቸው?

ማስታወሻ፦

የምስላዊ ግራፍን ለመተርጎምና የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ፦

- በመጀመሪያ ምስላዊ ግራፍ በምን ጉዳይ ላይ እንደተዘጋጀ ደጋግሞ በማንበብ መረዳት ያስፈልጋል።
- አንድ ምስል የሚወክለውን መጠን ማወቅ።
- በመጨረሻ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

ምሳሌ 8.2፦

ከዚህ በታች ያለውን ምስላዊ ግራፍ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተመልክቱና ጥያቄዎች መልሱ። ምስላዊ ግራፍ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ3ኛ ሀ እስከ መ ክፍል ውስጥ ያሉ የጎበዝ ተማሪዎች ብዛትን ያመለክታል።

ሀ	
ለ	
ሐ	
መ	

መልመጃ 8.2

1. በአንድ ትምህርት ቤት ለ3ኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰጠ የመጽሐፍት ዓይነትና ብዛት ድልደላ ተመልከቱ። አንድ መጽሐፍ ምስል 4 መጽሐፍትን ይወክላል።

የመጽሐፍት ዓይነት	የመጽሐፍት ብዛት
አማርኛ	
እንግሊዘኛ	
ሒሳብ	
አከባቢ ሳይንስ	

ሀ. እያንዳንዱ መጽሐፍ ስንት መጽሐፍትን ይወክላል?

ለ. በብዛት ለተማሪ የተሰጠ መጽሐፍ ዓይነት የትኛው ነው?

ሐ. እኩል የተሰጠ የመጽሐፍ ዓይነት የትኛው ነው?

መ. አጠቃላይ የተሰጠ የመጽሐፍ ብዛት ስንት ነው?

2. ቀጥሎ የተሰጠው የስዕል ግራፍ ከሚያዝያ ወር እስከ ነሐሴ ወር ዕለታዊ የዝናብ ስርጭትን ያመለክታል። አንድ የዝናብ ቀን በምስል● ሁለት ቀን ይወክላል።

ወራት	ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት
ሚያዝያ	●● ● ●●●●● ●
ግንቦት	●● ● ●●●
ሰኔ	●●● ● ●●● ●●
ሐምሌ	●●● ● ●●● ● ●●●
ነሐሴ	●●● ● ●●●

ሀ. እያንዳንዱ ይህ ምልክት ስንት ቀን ይወክላል?

ለ. በእያንዳንዱ ወር ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ስንት ናቸው?

ሐ. ብዙ ቀናት ዝናብ የዘነበው በየትኛው ወር ላይ ነው?

መ. ለጥቂት ቀናት ዝናብ የዘነበው በየትኛው ወር ላይ ነው?

ሠ. ከሚያዝያ ወርና ከነሐሴ ወር ለብዙ ቀናት ዝናብ የዘነበበት ወር የትኛው ነው?

ረ. በአምስት ወራት ውስጥ በአጠቃላይ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ምን ያህል ይሆናሉ?

3. በአንድ ትምህርት ቤት በ3ኛ ክፍል የሚማሩ 6 ተማሪዎች ክብደታቸውን በኪሎ ግራም የተገለጸበት ከዚህ በታች የተሰጠው የምስል ግራፍ የሚያመለክተውን ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።



ሀ. ጠቅላላ የተማሪዎች ክብደታቸው ስንት ይሆናል?

ለ. ከሁሉም ተማሪዎች ውስጥ ከባድ ክብደት ያለው ተማሪ ስም ማን ነው?

ሐ. ከሁሉም ተማሪዎች ውስጥ ቀላል ክብደት ያለው ተማሪ ስም ማን ነው?

መ. ክብደታቸው ከ26 ኪሎ ግራም በላይ ያላቸው ተማሪ ብዛት ስንት ነው?

ሠ. ክብደታቸው ከ26 ኪሎ ግራም በታች ያላቸው ተማሪ ብዛት ስንት ነው?

የምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያ

- የምስል ግራፍ ተጠቅመን ድርጊቶችን (ክህስተቶችን) ለማሳየት መጀመሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት ያስፈልጋል።
- ምስላዊ ግራፍ እውነቶችን (ድርጊቶችን) በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል።
- በምስላዊ ግራፍ አንድ ምስል የተለያዩ መጠን ያላቸውን ነገሮች ሊወክል ይችላል።

የምስላዊ ግራፍን ለመተርጎምና የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ፦

- በመጀመሪያ ምስላዊ ግራፍ በምን ጉዳይ ላይ እንደተዘጋጀ ደጋግሞ በማንበብ መረዳት ያስፈልጋል።
- አንድ ምስል የሚወክለውን መጠን ማወቅ።
- በመጨረሻ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. በክፍል ውስጥ የሚገኙ ጓደኞችን በጣም የሚወዷቸው የፍራፍሬ ዓይነት (ብርቱካን፣ ማንጎ፣ ሎሚ እና አቮካዶ) ጠይቃችሁ መዝግቡ። ይህንን መረጃ በመጠቀም የምስል ግራፍ ሳሉ። በተጨማሪ በመረጃው መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።
   ሀ. ብዙ ተማሪዎች የሚወዱት የፍራፍሬ ዓይነት የትኛው ነው?
   ለ. ጥቂት ተማሪዎች የሚወዱት የፍራፍሬ ዓይነት የትኛው ነው?

ሐ. በእኩል ተማሪዎች የሚወዱት የፍራፍሬ ዓይነት የትኛው ነው?

መ. አቮካዶና ሎሚ የሚወዱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

ሠ. አቮካዶና ብርቱካን የሚወዱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

2. በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደረሽን ለ2022 አለም ዋንጫ ማጣሪያ በአሰልጣኝ አቶ ውበቱ አባተ አማካይነት 40 የዋሊያዎቹ ተጨዋቾች ስብስብ፣ 35 የቀይ ቀበሮች ተጨዋቾች ስብስብ፣ 25 የኦሎምፒክ ቡድን እና 32 ከ23 ዓመት በታች ታዳጊ ስብስባቸውን ጠርቷል። ይህንን መረጃ በምስል ግራፍ ተጠቅማችሁ ግለጹ። የምስል ግራፍን በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. የብዙ ተጨዋቾች ስብስብ ያለው ቡድን የትኛው ነው?

ለ. የትንሽ ተጨዋቾች ስብስብ ያለው ቡድን የትኛው ነው?

ሐ. አጠቃላይ የተጨዋቾች ስብስብ ስንት ነው?

3. በአንድ ትምህርት ቤት በ3ኛ ክፍል የሚማሩ 7 ተማሪዎች ቁመታቸውን በሳንቲ ሜትር የተገለጸበት ስለሆነ ከዚህ በታች የተሰጠው የምስል ግራፍ የሚያመለክተውን ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።



ሀ. ረዥም ቁመት ያለው ተማሪ ማን ነው?

ለ. እኩል ቁመት ያላቸው ተማሪዎች እነማን ናቸው?

ሐ. በቁመት ሁለተኛ ደረጃ የያዘው ተማሪ ማን ነው?

መ. በጠቅላላ ቁመታቸው ድምር ስንት ነው?

4. በሶስተኛ ክፍል በሒሳብ ትምህርት ለተማሪዎች ከ10% መምህሩ የሙከራ ፈተና (ቴስት) ውጤት እንደሚከተለው በምስል ግራፍ ገልጹዋል።



ሀ. በፈተና ውጤት 8 እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

ለ. በፈተና ውጤት 6 እና በታች ያመጡ ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

ሐ. ፈተናውን የተፈተኑት ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?



9. የጂኦሜትሪ ምስሎች

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን በመመልከት መከፋፈል፣ ቅርፆችን በጎናቸውና በነቁጦቻቸው መግለጽ ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸው ማወዳደር እና ባለ ሶስት አውታር ምስሎችን መለየት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የምጥጥን እና ያለ ምጥጥን የጂኦሜትሪ ምስሎች መካከል ያለውን ልዩነት ትረዳላችሁ።
- በጎኖች ብዛት የጂኦሜትሪ ምስሎችን ትሰይማላችሁ።
- የጂኦሜትሪ ምስሎች ባህሪያትን ትረዳላችሁ።

በዚህ ምዕፍራ የጂኦሜትሪ ምስሎች ነቁጥን ለመለየት የሚያግዙ ተግባራት፣ ምጥጥን እና ያለ ምጥጥን ቅርጾችን፣ በጎኖች ብዛት የጂኦሜትሪ ምስሎችን መለየት እና የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት እንደገና ማደራጀት እና መሰየም ናቸው።

9.1 መጋጠሚያዎችን (ነቁጦች) ለይቶ ለመረዳት ማንሸራተትን፣ መገልበጥን እና ማዞርን መጠቀም

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ በጎኖች ብዛት የጂኦሜትሪ ምስሎችን መሰየም ተምራችኋል። አሁን ደግሞ የተለያዩ የጂኦሜትሪ ምስሎችን በማንሸራተት፣ በመገልበጥ እና በማዞር የመጋጠሚያዎችን ቦታ መቀያየርን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ማንሸራተቻን፣ መገልበጫን እና ማዞሪያን በመጠቀም ነቁጦችን ትለያላችሁ።

ተግባር 9.1

1. ከዚህ በታች ያለውን ምስል ወደ ጎን በማንሸራተት የሚገኘውን ምስል ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።



2. ከዚህ በታች ያለውን ምስል በተሰጠው መስመር ላይ በመገልበጥ የሚገኘውን ምስል ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።



ማስታወሻ፦

ቅርፆችን ስናንሸራተት መጋጠሚያዎች ሁሉም በራሳቸው አቅጣጫ ይቀመጣሉ። ነገር ግን የተሰጠው ቅርፅ ወደ ፊለገበት አቅጣጫ ተገፍቶ ሄዶ ይቀመጣል።

ለምሳሌ 9.1፦



3. ቅርፆችን ስንገለብጥ መጋጠሚያዎች ተገልብጠው በተቀራኒ አቅጣጫ ይሆናሉ።

ለምሳሌ 9.2፦ 

4. ቅርፆችን ስናዞር አንዱን መጋጣሚያ (ነቁጥ) በቦታው አስረን የቀሩትን መጋጠሚያዎች በሰዓትዮሽ አቅጣጫ ወይም በኢሰዓትዮሽ አቅጣጫ እናዞራለን።

ለምሳሌ 9.3፦  ምስሉ በለይኛው መጋጠሚያን ታስሮ የዞረ

መልመጃ 9.1

1. ከዚህ በታች የቀረቡት ቅርፆች በምን መንገድ እንደተንቀሳቀሱ ግለጹ።

ሀ 

ለ 

ሐ 

መ. 

ሠ. 

ረ. 

9.2 የምጥጥን እና ያለ ምጥጥን ቅርፆች

መግቢያ

ከከዚህ በፊት በ9.1 ላይ ቅርፆችን መገልበጥ፣ ማንሸራተትና ማዞር ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እነዚህን ቅርፆች ምጥጥን ወይም ያለ ምጥጥን መሆናቸውን መለየት ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የምጥጥን እና የያለ ምጥጥን ቅርፆችን ትለያላችሁ።

ተግባር 9.2

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ከሚከተሉት መሀል ምጥጥን ቅርፆችን ለዩ።

ሀ 

ለ 

ሐ 

2. ከሚከተሉት መሀል ያለ ምጥጥን ቅርፆችን ለዩ።


ሀ


ለ


ሐ

ማስታወሻ

- ተስተካክሎ የተመዛዘነ እና የተመጣጠነ ቅርፅ ምጥጥን ቅርፅ ይባላል።
- አንድን ምጥጥን ሁለት እኩል አምሳያ ቅርጾች ማካፈል ይቻላል።

ለምሳሌ 9.4፦  የዚህ ቅርፅ ቀኝና ግራ ጎኖቹ በኩል እና ተመሳሳይ ናቸው። ስለዚህ ምጥጥን ቅርፅ ነው።

- ተስተካክሎ ያልተመዛዘነ እና ያልተመጣጠነ ቅርፅ ያለ ምጥጥን ቅርፅ ይባላል። ያለ ምጥጥን ቅርፅን ሁለት እኩል የተመሳሰሉ ቅርፆች ማካፈል አይቻልም።

ለምሳሌ 9.5፦  የዚህ ቅርፅ የላይኛው ክፍልና የታችኛው ክፍል እኩል የተመሳሰሉ አይደሉም። ስለዚህ ያለ ምጥጥን ቅርፅ ነው።

- አንድን ምጥጥን ቅርፅ ሁለት እኩልና ተመሳሳይ ቅርጾች የሚከፍል መስመር ማመጣጠኛ መስመር ይባላል።

ለምሳሌ 9.6፦



በነጠብጣብ የተሰመረው መስመር የማመጣጠኛ መስመር ነው።

መልመጃ 9.2

1. ከሚከተሉት መሀል ያለ ምጥጥን ቅርፅ የሆነው የቱ ነው።

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 

2. ከዚህ በታች ላሉት የማመጣጠኝ መስመር አስምሩ።

ሀ  ለ  ሐ  መ  ሠ. M

3. ለሚከተሉት ቅርፆች የማመጣጠኛ መስመሮችን ብዛት በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፉ።

ሀ  ለ  ሐ  መ 

9.3 የጂኦሜትሪ ምስሎችን በጎናቸው ብዛት መለየት እና መሰየም

መግቢያ

ከዚህ በፊት በንዑስ ምዕራፍ 9.2 ላይ ምጥጥንና ያለ ምጥጥን ቅርፆችን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ከእነዚህ ውስጥ የተለያዩ የጂኦሜትሪ ምስሎችን በጎናቸው ብዛት መለየትንና መሰየምን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የጂኦሜትሪ ምስሎችን በየስማቸው ትሰይማላችሁ።

ተግባር 9.3

1. ይህ ምስል ስንት ጎን አለው? ይህን ምስል የሚመስል ቅርፅ ያለው ነገር አይታችሁ ታውቃላችሁ?



ማስታወሻ

ጠለላዊ ምስሎች

1. ሶስት ጎኖችን የያዘ የጠለል ምስል ጎነ ሶስት (ትሪያንግል) ይባላል።

ምሳሌ 8.7፦



2. አራት ጎኖች ያለው ምስል ጎነ አራት ይባላል። የተወሰኑ የጎነ አራት ምስሎች ከዚህ በታች እንሚለከተው ናቸው።



3. ሁለቱ ጥንድ የጎነ አራት ተቃራኒ ጎኖች ትይዩ ከሆኑ ጎነ አራቱ ፓራሌሎግራም ይባላል።



4. የፓራሌሎግራም ሁለቱ ተቋራጭ ጎኖች ማዕዘናዊ (ቀጤ) ከሆነ ፓራሌሎግራሙ ሬክታንግል ተብሎ ይጠራል።



5. የሬክታንግል አራት ጎኖች ርዝመት እኩል ከሆነ ሬክታንግሉ ካሬ ተብሎ ይጠራል።



6. ምንም ጎን የሌለው ጠለላዊ ምስል ክብ ይባላል።



መልመጃ 9.3

የሚከተሉትን ስሞች ከምስሎቻቸው ጋር አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ካሬ	ሀ. 
2. ጎነ ሶስት	ለ.
3. ሬክታንግል	ሐ.
4. ክብ	መ.

9.4 የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት እንደገና ማደራጀት እና መሰየም

መግቢያ

ከዚህ በፊት በንዑስ ምዕራፍ 9.3 ላይ የጂኦሜትሪ ምስሎችን በጎናቸው ብዛት መለየትን እና መሰየምን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ከእነዚህ ውስጥ የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት እንደገና ማደራጀት እና መሰየምን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የጂኦሜትሪ ምስሎች ባህሪያትን ትረዳላችሁ።

ተግባር 9.4

1. የሬክታንግልና የካሬ ልዩነታቸው ምንድ ነው? አራቱም ጎኖች እኩል ርዝመት ያለው የትኛው ነው?
2. የመማሪያ ክፍላችሁ ወለል የየትኛው ምስል ምሳሌ ልሆን ይችላል?

ማስታወሻ

1. ጎነ ሶስት ምስሎች

- ጎነ ሶስት ምስሎች ሶስት ጎኖች እና ሶስት መጋጠሚያዎች (ነቁጦች) ያሏቸው ጠለላዊ ምስሎች ናቸው። ጎነ ሶስት ምስሎች ሶስት አንግሎች አሉት።
- የጎነ ሶስት ምስሎች ነጥቦቻቸውን በፊደላት በመወከል ይሰየማሉ።



ሀ፣ ለ እና መ ነቁጥ (መጋጠሚያ ነጥቦች) ናቸው።

$\overline{ሀለ}$ ፣ $\overline{ሀመ}$ እና $\overline{ለመ}$ የጎነ ሶስት ጎኖች ናቸው።

ጎነ ሶስት ሀለመ ወይም "Δሀለመ" ተብሎ ይጠራል።

"Δ" ይህ የጎነ ሶስት መገለጫ ምልክት ነው።

2. ጎነ አራት ምስሎች

- ጎነ አራት ምስሎች አራት ጎኖች እና አራት ነቁጥ ያሏቸው ጠለላዊ ምስሎች ናቸው። እያንዳንዱ ጎነ አራት ምስል አራት አንግሎች አሉት።
- ጎነ አራት ምስሎችን ነጥቦቻቸውን በፊደላት በመወከል ይሰየማሉ።

ሀ. ፓራሌሎግራም

ፓራሌሎግራም ጎነ አራት ምስል ሆኖ ሁለቱ ጥንድ ተቀራኒ ጎኖቹ ትይዩ ናቸው።



$\overline{ሀለ}$ ና $\overline{መሠ}$ እና $\overline{ሀሠ}$ ና $\overline{ለመ}$ ትይዩ ጎኖች ናቸው።

$\overline{ሀለ}$፣ $\overline{ሀመ}$፣ $\overline{ለመ}$ እና $\overline{መሠ}$ የጎነ አራቱ (የፓራሌሎግራሙ) ጎኖች ናቸው። ፓራሌሎግራም (ጎነ አራት) ሀለመሠ ወይም ለመሠሀ ወይም መሠሀለ ተብሎ ይጠራል።

ለ. ሬክታንግል

ሬክታንግል ፓራሌግራም ምስል ሆኖ አራቱም ውስጣዊ አንግሎቹ ማዕዘናዊ ናቸው።



ሠ፣ ረ፣ ቀ እና ሸ ነቁጦች ናቸው።

$\overline{ሠሸ}$ እና $\overline{ሸቀ}$ እንዲሁም $\overline{ረቀ}$ እና $\overline{ሠረ}$ ተጓዳኝ ጎኖች ናቸው።

$\overline{ሠሸ}$ እና $\overline{ረቀ}$ እንዲሁም $\overline{ሸቀ}$ እና $\overline{ሠረ}$ ትይዩ ጎኖች ናቸው።

ሬክታንግል ሠረቀሸ፣ ረቀሸሠ፣ ሸሠረቀ ወይም ቀሸሠረ ተብሎ ይጠራል።

ሐ. ካሬ

ካሬ ሬክታንግል ሆኖ የአራት ጎኖቹ ርዝመት እኩል የሆነ ምስል ነው።



በ፣ ከ፣ ተ እና ቸ ነቁጦች ናቸው።

$\overline{በቸ}$ እና $\overline{ቸተ}$ እንዲሁም $\overline{ቸተ}$ እና $\overline{ተከ}$ ተጓዳኝ ጎኖች ናቸው።

$\overline{በከ}$፣ $\overline{ከተ}$፣ $\overline{ተቸ}$ እና $\overline{ቸበ}$ እኩል ርዝመት አሏቸው።

ካሬ በከተቸ፣ ከተቸበ፣ ቸበከተ ወይም ተቸበከ ተብሎ ይጠራል።

መ. ሮምቦስ

ሮምቦስ አራቱም ጎኖቹ እኩል የሆነ ፓራሌሎግራም ምስል ነው።



በ፣ ከ፣ ተ እና ቸ መጋጠሚያ ነጥቦች ናቸው።

$\overline{ሀለ}$ እና $\overline{ሠመ}$ እንዲሁም $\overline{ሀሠ}$ እና $\overline{ለመ}$ ትይዩ ጎኖች ናቸው።

አንግል ሀለመ እና ሀሠመ እንዲሁም አንግል ለሀሠ እና ለመሠ እኩል ናቸው።

3. ክብ ምስል

ክብ በአንድ ነጥብ ዙርያ በእኩል ርቀት ላይ ባሉ ነጥቦች ስብስብ የሚፈጠር ጠለላዊ ምስል ሲሆን ነጥቡም የክቡ መሐል (እምብርት) ተብሎ ይጠራል።



ይህ ምስል ምንም ነቁጥ እና ጎን የለውም።

“ቀ” የክቡ መሀል (እምብርት) ነው።

- በክቡ ላይ የተመለከቱት ነጥቦች ወ፣ ዘ እና ረ ከመሀል ነጥብ ቀ እኩል ርቀት ላይ ይገኛሉ።
- ክብ የሚሰየመው በክቡ መሀል በሚገኘው ነጥብ ሲሆን ይኸውም ክብ ቀ ይባላል።
- ከመሀል ነጥብ ቀ እስከ ክቡ ያለው ርቀት ሬዲየስ ተብሎ ይጠራል። $\overline{ቀዘ}$፣ $\overline{ቀረ}$ እና $\overline{ቀወ}$ ሬዲየሶች ናቸው።

መልመጃ 9.4

1. ከሚከተሉት ውስጥ ፓራሌሎግራም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሬክታንግል ለ. ካሬ ሐ. ሮምቦስ መ. ክብ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ትሪያንግል የቱ ነው?

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ. 

3. የካሬና የሮምቦስ ልዩነትን ጻፉ።

4. የክፍላችሁ ሰሌዳ የትኛውን ጎነ አራት ምስል ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

የምዕራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ

- አንድን ምጥጥን ሁለት እኩል ተመሳሳይ ቅርፅ ማካፈል ይቻላል።
- ተስተካክሎ ያልተመዛዘነ እና ያልተመጣጠነ ቅርፅ ያለ ምጥጥን ቅርፅ ይባላል።
- ጎነ ሶስት ምስሎች ሶስት ጎኖች እና ሶስት አንግሎች አሏቸው።
- ካሬ፣ ሬክታንግል፣ ፓራሌሎግራም እና ሮምቦስ ጎነ አራት ምስሎች ናቸው።
- ክብ ምንም ጎን የሌለው ጠለላዊ ምስል ነው።
- ክብ ስያሜ የሚጠራው በክቡ መሀል በሚገኘው ነጥብ ፊደል ወይም ምልክት ነው።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. አዛመዱ።

“ሀ”	“ለ”
—— 1. ካሬ	ሀ. 
—— 2. ጎነ ሶስት	ለ. 
—— 3. ሮምቦስ	ሐ. 
—— 4. ክብ	መ. 
—— 5. ሬክታንግል	ሠ. 

2. ምስል ሀለመሠ ካሬ ነው። የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ።

ሀ. $\overline{ሀለ} = \overline{ለመ}$

ለ. ለመሠሀ ሬክታንግል ነው።

ሐ. ለመሠሀ ሮምቦስ ነው።

መ. $\overline{ሀለ}$ እና $\overline{ለመ}$ ተጓዳኝ ጎኖች ናቸው።

ሠ. <ሀሠመ ማዕዘናዊ ነው።





10. ልኬት፡ ርዝመት፣ ክብደት እና ይዘት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ የተለያዩ የርዝመት፣ የክብደት እና የይዘት መለኪያ ምድቦችን እንዲሁም ተመሳሳይ የልኬት ምድቦችን መደመር እና መቀነስ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት ተማሪዎች መሰረታዊ የልኬት መሳሪያዎችን ተረድተው በዕለት ኑሯቸው ውስጥ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማስቻል ሲሆን ይህንንም ከግብ ለማድረስ የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ንዑስ ምዕራፎች በዋናነት ርዝመትን በሚሊ ሜትር፣ ሳንቲ ሜትር፣ ዴስ ሜትር፣ሜትር እና በኪሎ ሜትር መለካት፤ ክብደትን በሚሊ ግራም፣ በግራም፣ በኪሎ ግራም እና በኩንታል መለካት እና ይዘትን በሚሊ ሊትር፣ በሊትርና በጋሎን መለካት ናቸው። በሶስቱ ንዑስ ምዕራፎች ስለ ተመሳሳይ የልኬት ምድቦች መደመር እና መቀነስም ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- እንደ ርዝመት፣ ክብደት እና ይዘት ያሉ ባህሪያትን ትለያላችሁ።
- እያንዳንዱን ባህርይ ለመለካት ተገቢውን ዓይነት ምድብ ትለያላችሁ።
- በመደበኛ ምድቦች የመለካት አስፈላጊነትን ተረድታችሁ እና ባህላዊና ዘመናዊ ስርዓቶች ውስጥ ከመደበኛ ምድቦች ጋር ትተዋወቃላችሁ።
- በተመሳሳይ የልክት ስርዓት ውስጥ ያሉትን ምድቦች ከአንድ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ (ከሳንቲ ሜትር ወደ ሜትር) የመሳሰሉት መቀያየርን ታካሂዳላችሁ።

10.1 ርዝመትን በሚሊ ሜትር(ሚ.ሜ)፣ በሳንቲ ሜትር(ሳ.ሜ)፣ በሜትር(ሜ) እና በኪሎ ሜትር(ኪ.ሜ) መለካት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ ርዝመትን በሳንቲ ሜትር እና በሜትር መለካትን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ርዝመትን በሚሊ ሜትር፣ በሳንቲ ሜትር፣ በሜትር እና በኪሎ ሜትር መለካትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የርዝመት መለኪያ ምድቦችን ትለያላችሁ።

ተግባር 10.1

ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ።

1. ማስመሪያ ተጠቅማችሁ የሒሳብ መጽሐፋችሁን ርዝመት ለኩ።
   _____ ሳንቲ ሜትር (ሳ.ሜ) እና _____ ሚሊ ሜትር (ሚ.ሜ) ነው።
2. በሜትር ወይም በማስመሪያ የሁለት ክንዳችሁን ርዝመት ያለውን ገመድ ለኩ።
   ሀ. የገመዱ ርዝመት በሳንቲ ሜትር ስንት ነው?
   ለ. የገመዱ ርዝመት በሚሊ ሜትር ስንት ነው?

ማስታወሻ፦

- ርዝመትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው መደበኛ ምድቦች: ሚሊ ሜትር (ሚ.ሜ)፣ ሳንቲ ሜትር (ሳ.ሜ)፣ ዴስ ሜትር (ዴ.ሜ)፣ ሜትር (ሜ) እና በኪሎ ሜትር (ኪ.ሜ) ናቸው።
- በጣም አጭር ርዝመት ያላቸው ቁሶችን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች ሚ.ሜ ሳ.ሜ እና ዴ.ሜ ናቸው።
- መካከለኛ ርዝመት ያላቸው ቁሶችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ሜትር ነው።
- በጣም ረዥም ርዝመት ያላቸው ቁሶችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ኪ.ሜ ነው።
-
-
- መካከለኛ ርዝመት ያላቸው ቁሶችን ለመለካት የሚንጠቀመው ምድብ ሜትር ነው።





የርዝመት መለኪያ መሣሪያዎች

ምሳሌ 10.1፦

1. የመማሪያ ክፍል ጠረጴዛን ርዝመት ለመለካት የምትጠቀሙት የርዝመት ምድብ የትኛው ነው?
2. የደብተራችሁን ርዝመት ለመለካት የምትጠቀሙት የርዝመት ምድብ የትኛው ነው?

መፍትሔ፦

1. የጠረጴዛን ርዝመት ለመለካት የሚያስፈልገን የርዝመት ምድብ ሳ.ሜ.፣ ዴ.ሜ ወይም ሜ. ነው።
2. የደብተራችሁ ርዝመት ለመለካት የሚያስፈልገን የርዝመት ምድቦች ሚ.ሜ. ሳ.ሜ. እና ዴ.ሜ ናቸው።

መልመጃ 10.1

1. የክፍል ሰሌዳችሁን ርዝመት ለመልካት የምንጠቀመው የትኛውን የርዝመት ምድብ ነው?
2. የእግር ኳስ ሜዳ ርዝመትን ለመለከት የምንጠቀመው የትኛውን የርዝመት ምድብ ነው?
3. ከቤታችሁ እስከ ትምህርት ቤታችሁ ድረስ ያለውን ርቀት ለመለካት የምንጠቀመው የትኛውን የርዝመት ምድብ ነው?
4. የመማሪያ ክፍላችሁን በር ርዝመት ለክታችሁ በሚ.ሜ.፣ በሳ.ሜ. እና በሜ. ግለጹ።

10.2 የርዝመት ምድቦችን ወደ ዝቅተኛ ምድቦች መቀየር

መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ንዑስ ርዕስ ከከፍተኛ የርዝሜት መለኪያ ምድቦች ወደ ዝቅተ የርዝሜት መለኪያ ምድቦች መቀየርን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

የተለያዩ የርዝመት መለኪያ ምድቦችን በመጠቀም የቁሶችን ርዝመት ትለካላችሁ።

ተግባር 10.2

ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ሀ. የርዝመት መለኪያ ምድቦች ዘርዝራችሁ ጻፉ።

ለ. የርዝመት መለኪያ ምድቦችን ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደምተከተላቸዉ ጻፉ።

ሐ. የርዝመት መለኪያ ምድቦችን ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደምተከተላቸዉ ጻፉ።

ማስታወሻ፦

በምድቦች መካከል ያለው ዝምድና፦ 10 ሚ.ሜ = 1 ሳ.ሜ

1,000 ሜ = 1 ኪ.ሜ

ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ ለመቀየር ከኪ.ሜ ወደ ሜ በ1,000 ማብዛት፣ ከሜ ወደ ሳ.ሜ ለመቀየር በ100 ማብዛት እና ከሳ.ሜ ወደ ሚ.ሜ ለመቀየር በ10 ማብዛት ነው።

ምሳሌ 10.2፦

1. **ኪሎ ሜትርን ወደ ሜትር ለመቀየር በ1,000 ማባዛት ነዉ።**

1 ኪ.ሜ= 1,000 ሜ

2 ኪ.ሜ= ?

$$\frac{2\ \text{ኪ.ሜ} \times 1{,}000\ \text{ሜ}}{1\ \text{ኪ.ሜ}} = \frac{2{,}000\ \text{ሜ}}{1\ \text{ኪ.ሜ}} = 2{,}000\ \text{ሜ}$$

2. ሜትርን ወደ ሳንቲ ሜትር ለመቀየር በ100 ማባዛት ነዉ።

1 ሜ.=100 ሳ.ሜ.

4 ሜ = ?

$$\frac{4\ \text{ሜ} \times 100\ \text{ሳ.ሜ}}{1\ \text{ሜ}} = \frac{400\ \text{ሳ.ሜ}}{1} = 400\ \text{ሳ. ሜ}$$

3. ሳንቲ ሜትርን ወደ ሚሊሜትር ለመቀየር በ10 ማባዛት ነዉ።

1 ሳ.ሜ. = 10 ሚ.ሜ.

8 ሳ.ሜ = ?

$$\frac{8\ \text{ሳ.ሜ} \times 10\ \text{ሚ.ሜ}}{1\text{ሳ.ሜ}} = \frac{80\ \text{ሚ.ሜ}}{1} = 80\ \text{ሚ. ሜ}$$

መልመጃ 10.2

1. የሚከተሉትን የርዝመት መለኪያ ምድቦች ወደ ተጠየቀው ዝቅተኛ ቀይሩ።

ሀ. 5 ኪ.ሜ = _____ሜ ሐ. 70 ሳ.ሜ= _____ሚ.ሜ

ለ. 40 ሜ = _____ ሳ.ሜ

10.2 ክብደትን በሚሊ ግራም (ሚ.ግ)፣ ግራም (ግ)፣ ኪሎ ግራም (ኪ.ግ) እና በኩንታል መለካት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ ክብደትን በግራም እና በኪሎ ግራም መለካትን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ ክብደትን በሚሊ ግራም፣ በግራም፣ በኪሎ ግራም እና በኩንታል መለካትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመጠነ ትንሽ ቁሶች ክብደትን ትለካላችሁ።

ተግባር 10.3

ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. ቀላል ዕቃዎችን ለምሳሌ፥ አንድ የገላ ሳሙና ወይም አንድ የጆሮ ጌጥ ክብደት ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ምን ሊሆን ይችላል?
2. ከባድ ዕቃዎችን ለምሳሌ፥ አንድ ከረጢት ስምንቶ ክብደት ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ምን ሊሆን ይችላል?

ማስታወሻ፦

- ክብደትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች ሚሊ ግራም (ሚ.ግ)፣ ግራም (ግ)፣ ኪሎ ግራም (ኪ.ግ) እና ኩንታል ናቸው።
- በጣም ትንሽ ክብደት ያላቸው ቁሶችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ሚ.ግ ነው።
- እጅግ በጣም ትልቅ ክብደት ያላቸው ነገሮችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ኪ.ግ ወይም ኩንታል ነው።



ምሳሌ 10.3፦

1. የአንድ ብርቱካን ክብደት ለመለካት የምንጠቀመው የክብደት ምድብ የቱ ነው?
2. የአንድ ከረጢት ጤፍ ክብደት ለመለካት የምንጠቀመው የክብደት ምድብ የቱ ነው?

መፍትሔ፦

1. የአንድ ብርቱካን ክብደት ለመለካት የሚያስፈልገን የክብደት ምድብ ሚ.ግ ወይም ግራም ሊሆን ይችላል።
2. የአንድ ከረጢት ጤፍ ክብደት ለመለካት የሚያስፈልገን የክብደት ምድብ ኪ.ግ ወይም ኩንታል ሊሆን ይችላል።

መልመጃ 10.3

1. የአንድ ከረሜላን ክብደት ለመለካት የምንጠቀመው የክብደት ምድብ የቱ ነው?
2. የሰዎችን ክብደት ለመግለፅ የምንጠቀመው የክብደት ምድብ የቱ ነው?

10.4 የክብደት መለኪያ ምድብን ወደ ዝቅተኛ መለኪያ ምድብ መቀየር

መግቢያ

በንዑስ ምዕራፍ 10.3 ላይ የተለያዩ የክብደት መለኪያ ምድቦችን የተለያዩ ክብደቶችን ለመለካት እንደ ምንጠቀም ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የክብደት መለኪያ ምድብን ወደ ዝቅተኛ መለኪያ ምድብ መቀየርን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የቁሶችን ክብደት መለካት ነው።

ተግባር 10.4

1. 50 ኩንታል በቆሎ ስንት ኪሎ ግራም ይሆናል?
2. የ10 ግራም ዳቦ በሚሊ ግራም ስንት ይሆናል?

ማስታወሻ፦

ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ ለመቀየር በዝምድናቸው ማብዛት ያስፈልጋል።

በምድቦች መካከል ያለው ዝምድና፦ 1,000 ሚ.ግ = 1 ግ

1,000 ግ = 1 ኪ.ግ

100 ኪ.ግ = 1 ኩንታል

ምሳሌ 10.4፦

1. የሚከተሉትን የክብደት መለኪያ ምድቦች ወደ ተጠየቀዉ ዝቅተኛ ምድብ ቀይሩ።

ሀ. 1 ኩንታል = _____ ኪ.ግ ለ. 1 ኪ. ግ = _____ግ

መፍትሔ 10.4፦

ሀ. 1 ኩንታል = 100 ኪ.ግ. ከሆነ

100 ኩንታል = ?

$$\frac{100\ \text{ኩንታል} \times 100\ \text{ኪ.ግ}}{1\ \text{ኩንታል}} = \frac{10{,}000\ \text{ኪ.ግ}}{1} = 10{,}000\ \text{ኪ. ግ}$$

ለ. 1 ኪ.ግ = 1,000 ግራም ከሆነ

5 ኪ.ግ = ?

$$\frac{5\ \text{ኪ.ግ} \times 1{,}000\ \text{ግራም}}{1\ \text{ኪ.ግ}} = \frac{5{,}000\ \text{ግራም}}{1} = 5{,}000\ \text{ግራም}$$

መልመጃ 10.4

1. የሚከተሉትን የክብደት መለኪያ ምድቦች ወደ ተጠየቀዉ ዝቅተኛ ምድብ ቀይሩ።

ሀ. 70 ኩንታል = _____ ኪ.ግ ሐ. 6 ግ = _____ ሚ.ግ

ለ. 8 ኪ. ግ = _____ግ

10.5 ይዘትን በሚሊ ሊትር (ሚ.ሊ) እና ሊትር (ሊ) መለካት

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ ይዘትን በሚሊ ሊትር እና ሊትር መለካትን ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ ይህንኑ አጠናክራችሁ ይዘትን በሚሊ ሊትር እና ሊትር መለካትን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- አሻዋን ወይም ውሃን ኩባያዎች በመጠቀም ይዘትን ትለካላችሁ።

ተግባር 10.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. በጣም ትንሽ መጠን ያለውን የፈሳሽ ይዘት ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ምን ይባላል?
2. ከፍተኛ መጠን ያለውን ይዘት የሚንለካበት ምድብ ምን ይባላል?

ማስታወሻ፦

- ይዘትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች ሚሊ ሊትር (ሚ.ሊ) እና ሊትር (ሊ) ናቸው።
- በጣም ትንሽ ይዘት ያላቸው ነገሮችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ሚ.ሊ ነው።
- ከፈተኛ መጠን ያላቸው ነገሮችን ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ሊትር ነው።



የይዘት መለኪያ መሣሪያዎች

ምሳሌ 10.5፦

1. በጣም ትንሽ መጠን ያለውን ይዘት ለመለካት ምን መሣሪያዎችን በመጠቀም በሚለ ሊትር ምድብ እንገልፃለን?
2. መጠነኛ እና ከፍተኛ መጠን ያለቸውን ይዘቶች ለመለካት ምን መሣሪያዎችን በመጠቀም በሊትር ወይም በጋሎን መለካት ይቻላል?

መፍትሔ፦

1. በሲሪንጅ፣ በሻይ ማንኪያ እና የመሳሰሉ መሣሪያዎችን እንጠቀማለን።
2. ጠርሙሶችን፣ ጀሪካኖችን፣ ሮቶዎችን፣ በርሜሎችን፣ ታንከሮችን እና የመሳሰሉ ዕቃዎችን በመጠቀም።

መልመጃ 10.5

1. የአንድ ስርንጅ ይዘትን ለመለካት የምንጠቀመው የይዘት ምድብ የቱ ነው?
2. የአንድ በርሜል ሙሉ ውኃ ይዘትን ለመለካት የምንጠቀመው የይዘት ምድብ የቱ ነው?

10.6 የይዘት መለኪያ ምድብ ወደ ዝቅተኛ መለኪያ ምድብ መቀየር (መለወጥ)

መግቢያ

በንዑስ ምዕራፍ 10.5 ላይ የተለያዩ የይዘት መለኪያ ምድቦችን የተለያዩ ይዘቶችን ለመለካት እንደምንጠቀም ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የይዘት መለኪያ ምድብ ወደ ዝቅተኛ መለኪያ ምድብ መቀየር (መለወጥ) ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- አሸዋን ወይም ውሃን ኩባያዎች በመጠቀም ይዘትን ትለካላችሁ ።

ተግባር 10.6

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ የሚከተሉት ጥያቄዎችን መልሱ።

   ሀ. የ3 ሊትር ዘይት ስንት ሚ.ሊ. ይሆናል?

   ለ. የ5 ሊትር ዘይት ስንት ሚ.ሊ. ይሆናል?

ማስታወሻ፦

ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ ለመቀየር በዝምድናቸው ማብዛት ያስፈልጋል።

በምድቦች መካከል ያለው ዝምድና፦ 1,000 ሚ.ሊ = 1 ሊ

ምሳሌ 10.6፦

1. 7ሊ ስንት ሚሊ ሊትር ነው?

መፍትሔ፦

1 ሊትር = 1,000 ሚሊ ሊትር ከሆነ

7 ሊትር = ?

$$\frac{7\text{ ሊትር}\times 1{,}000\text{ ሚሊ ሊትር}}{1\text{ ሊትር}} = \frac{7{,}000\text{ ሚሊ ሊትር}}{1} = 7{,}000\text{ ሚሊ ሊትር}$$

መልመጃ 10.6

1. የሚከተሉትን ምድቦታዎች ወደ ሚሊ ሊትር ቀይሩ።

ሀ. 2ሊ ለ. 5 ሊ ሐ. 9ሊ

የምዕራፍ አስር ማጠቃለያ

- ርዝመትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች: ሚሊ ሜትር (ሚ.ሜ)፣ ሳንቲ ሜትር (ሳ.ሜ)፣ ሜትር (ሜ) እና በኪሎ ሜትር (ኪ.ሜ) ናቸው።
- ክብደትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች: ሚሊ ግራም (ሚ.ግ)፣ ግራም (ግ)፣ ኪሎ ግራም (ኪ.ግ) እና ኩንታል ናቸው።
- ይዘትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው ምድቦች ሚሊሊትር (ሚ.ሊ) እና ሊትር (ሊ) ናቸው
- በይዘት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና፦ 1,000 ሚ.ሊ = 1 ሊ

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶቻቸውን አስቀምጡ።

   ሀ. 50 ሜ = —— ሳ.ሜ ነው።

   ለ. 8 ኪ.ሜ = —— ሜ. ነው።

   ሐ. 10 ኪ. ግ = —— ግ ነው።

   መ. 4 ሊ = —— ሊ ነው።

2. በሲርንጅ ውኃ እየቀዳቹ እና የውኃውን መጠን በሚ.ሊ ስንት እንደሆነ በማንበብ፣ በመመዝገብ እና ወደ ባለ 1 ሊትር ሃይላንድ ውኃ ዕቃ በመጨመር አንድ ላይ ደምሩ እና ስንት ሚ.ሊ ሃይላንድ እንደሞላ በደብተራችሁ ፃፉ።

3. ሁለት ሁለት ተማሪዎች በመሆን ሂዱና አንድ ላይ እና በተናጥል ሚዛን ላይ በመውጣት ኪሏችሁን በመለካት የተናጥል ድምር እና የአንድ ላይ ክብደት አወዳደሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ምዕራፍ አስራ አንድ

11. የኢትዮጵያ ምንዛሪ

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ የኢትዮጵያ ምንዛሬ መደመር፣ መቀነስ እና የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዴት መተግበር እንዳለበት ተምራችኋል። ከቤተሰቦቻችሁ ጋር የተለያዩ የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና የብር ሳንትሞች ተመልክታችሁ ይሆናል። አሁን ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ላይ የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር (መቀየር) እና ምንዛሪ ማወዳደርንትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የተለያዩ የኢትዮጵያ ገንዘብ ኖቶች መኖራቸውን ትረዳላችሁ።
- ከአንድ ገንዘብ ወደ ሌላ እንዴት እንደሚቀየር እና እንደሚመነዘር ትለያላችሁ።
- የኢትዮጵያን ገንዘብ በነባራዊ ኑሮ ሁኔታዎች ላይ ትተገብራላችሁ።

11.1 የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር (መቀየር)

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ የኢትዮጵያ ምንዛሬ ስለ መደመር እና ስለ መቀነስ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ የገንዘብ ኖቶችን መዘርዘር (መቀየር) ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሳንቲሞችን ትለያላችሁ።

ተግባር 11.1

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቡድን ስሩ።

1. የተለያዩ የኢትዮጵያን የብር ኖቶችን እና ሳንቲሞችን ዘርዝሩ።
2. የተለያዩ የኢትዮጵያን የብር ኖቶች እና የሳንቲሞች ዝምድና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሐሳባችሁን አጋሩ።
3. አንድ ባለ አስር ብር ኖት ስንት ባለ አንድ ብር ሳንቲም ይሆናል?
4. አንድ ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት ስንት ባለ አምስት ብር ኖት ይሆናል?

ከዚህ በታች የምትመለከቱት ምስሎች የኢትዮጵያ ብር ኖቶችንና የብር ሳንቲሞችን ለማስታወስ ይጠቅማችኋል።



ባለ 1 ብር ኖት



ባለ 50 ብር ኖት



ባለ 5 ብር ኖት



ባለ 100 ብር ኖት



ባለ 10 ብር ኖት



ባለ 200 ብር ኖት

የኢትዮጵያ ብር ኖት ምስሎች



1 ሳንቲም



5 ሳንቲም



10 ሳንቲም



25 ሳንቲም



50 ሳንቲም



1 ብር ሳንቲም

የኢትዮጵያ የሳንቲም ዲናሮች ምስል

ማስታወሻ፡

በብር ኖቶች እና ሳንቲም ዲናሮች መካከል ያለው ዝምድና እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

- 1 ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት = 2 ባለ አንድ መቶ ብር ኖት
  = 4 ባለ ሃምሳ ብር ኖት
  = 20 ባለ 10 ብር ኖት
  = 40 ባለ 5 ብር ኖት ይወክላል፡፡
- 1 ባለ አንድ መቶ ብር ኖት = 2 ባለ ሃምሳ ብር ኖት
  = 10 ባለ አስር ብር ኖት
  = 20 ባለ 5 ብር ኖት ይወክላል፡፡

- 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት = 5 ባለ አስር ብር ኖት = 10 ባለ 5 ብር ኖት = 50 ባለ 1 ብር ሳንቲም ይወክላል።
- 1 ባለ አስር ብር ኖት = 2 ባለ 5 ብር ኖት
  = 10 ባለ 1 ብር ሳንቲም
  = 20 ባለ 50 ሳንቲም
  = 40 ባለ 25 ሳንቲም ይወክላል።
- 1 ባለ አምስት ብር ኖት = 5 ባለ 1 ብር ሳንቲም
  = 10 ባለ 50 ሳንቲም
  = 20 ባለ 25 ሳንቲም ይወክላል።
- 1 ባለ 1 ብር ሳንቲም = 2 ባለ 50 ሳንቲም
  = 4 ባለ 25 ሳንቲምይወክላል።
- 1 ባለ 50 ሳንቲም = 2 ባለ 25 ሳንቲም ይወክላል።
- ከተገለጸው ዝምድና ውጪ ከትልቁ ብር ኖት ወደ ትንሹ ብር ኖት መቀየር (መዘርዘር) ይቻላል። እንዲሁም ከትልቁ ሳንቲም ዲናር ወደ ትንሹ ሳንቲም ዲናር መቀየር (መዘርዘር) ይቻላል።

ምሳሌ 11.1፦

አንድ ባለ ሁለት መቶ ኖት ወይም ሌላ የብር ኖቶችን ወደ ሳንቲም ዲናሮች መዘርዘር ይቻላል

1. አንድ ባለ 5 ብር ኖት በ5 አንድ ብር ሳንቲም ጋር መዘርዘር ይቻላል።
2. አንድ ባለ 50 ብር ኖት በ5 አስር ብር ኖት ጋር መዘርዘር ይቻላል።

መልመጃ 11.1

1. ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛው ዋጋ ሙሉ።

ሀ. 1 ባለ አምስት ብር ኖት = — ባለ 50 ሳንቲሞች ይሆናል።

ለ. 1 ባለ አስር ብር ኖት = — ባለ 5 ብር ኖኖቶች ይሆናል።።።

ሐ. 1 ባለ አስር ብር ኖት = — ባለ 25 ሳንቲሞች ይሆናል።

መ. 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት = — ባለ 1 ብር ሳንቲሞች ይሆናል።

ሠ. 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት = — ባለ 10 ብር ኖቶች ይሆናል።

ረ. 1 ባለ አንድ መቶ ብር ኖት = — ባለ 5 ብር ኖቶች ይሆናል።

ሰ. 1 ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት = — ባለ 10 ብር ኖቶች ይሆናል።

2. ክፍት ቦታውን ሙሉ።

ሀ. 1 ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት = 2 ባለ 50 ብር ኖት + — ባለ 10 ብር ኖት ነው።

ለ. 1 ባለ መቶ ብር ኖት = 1 ባለ 50 ብር ኖት + — ባለ 10 ብር ኖት ነው።

ሐ. 1 ባለ መቶ ብር ኖት = 10 ባለ 5 ብር ኖት + — ባለ 50 ብር ኖት ነው።

መ. 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት = 2 ባለ 10 ብር ኖት + — ባለ 1 ብር ሳንቲም ነው።

ሠ. 1 ባለ አስር ብር ኖት = 1 ባለ 5 ብር ኖት + — ባለ 50 ሳንቲም ነው።

ረ. 1 ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት = 1 ባለ መቶ ብር ኖት + — ባለ 50 ብር ኖት ነው።

11.2 ምንዛሪን ማወዳደር

መግቢያ

የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና የሳንቲም ዲናሮች መካከል ያለውን ዝምድና መጠቀም ተምራችኋል። አሁን ደግሞ እስካሁን የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ምንዛሪዎችን ማወዳደር ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

የገንዘብ ምንዛሪዎችን ታወዳድራላችሁ።

ተግባር 11.2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን “>”፣ “<” ወይም “=” ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. 1 ባለ መቶ ብር ___ 2 ባለ 50 ብሮች

ለ. 4 ብር _____ 4 ባለ 50 ሳንቲሞች

ሐ. 2 ብር _____ 2 ባለ 50 ሳንቲሞች

ማስታወሻ፦

ምንዛሪን ለማወዳደር በብር ኖቶች መሀል ያለውን ዝምድና እና በሳንቲም ዲናሮች መሀል ያለውን ዝምድና መጠቀም ያስፈልጋል።

ምሳሌ 11.2፦

1 መቶ ብር = 10 ባለ 10 ብሮች ነው።

1 መቶ ብር = 2 ባለ 50 ብሮች ነው።

1 ብር = 10 ባለ 10 ሳንቲሞች ነው።

መልመጃ 11.2

1. የሚከተሉትን የገንዘብ ምንዛሪዎችን በ >፣ < ወይም = ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ።

ሀ. 2 ባለ መቶ ብሮች _____ 10 ባለ 50 ብሮች

ለ. 2 ብር _____ 20 ባለ 10 ሳንቲሞች

ሐ. 2 ባለ 2 መቶ ብሮች _____ 3 ባለ 100 ብሮች

መ. 1 ባለ 50 ብር _____ 6 ባለ 10 ብሮች

ሠ. 4 ባለ 1 ብሮች _____ 8 ባለ 50 ሳንቲሞች

ረ. 600 ሳንቲሞች _____ 6 ብር

ሰ. 5 ብር _____ 25 ባለ 25 ሳንቲሞች

የምዕራፍ አስራ አንድ ማጠቃለያ

- 1 ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት 2 ባለ አንድ መቶ ብር ወይም 4 ባለ ሃምሳ ብር ወይም 20 ባለ 10 ብር ወይም 40 ባለ 5 ብር ኖቶችን ይወክላል።
- 1 ባለ አንድ መቶ ብር ኖት 2 ባለ ሃምሳ ብር ወይም 10 ባለ አስር ብር ወይም 20 ባለ 5 ብር ኖቶችን ይወክላል።
- 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት 5 ባለ አስር ብር ወይም 10 ባለ 5 ብር ኖቶችን ወይም 50 ባለ 1 ብር ሳንቲሞች ይወክላል።
- 1 ባለ አስር ብር ኖት 2 ባለ 5 ብር ኖቶችን ወይም 10 ባለ 1 ብር ሳንቲም ወይም 20 ባለ 50 ሳንቲም ወይም 40 ባለ 25 ሳንቲም ዲናሮችን ይወክላል።
- 1 ባለ አምስት ብር ኖት 5 ባለ 1 ብር ሳንቲም ወይም 10 ባለ 50 ሳንቲም ወይም 20 ባለ 25 ሳንቲም ዲናሮችን ይወክላል።
- 1 ባለ 1 ብር ሳንቲም 2 ባለ 50 ሳንቲም ወይም 4 ባለ 25 ሳንቲም ዲናሮችን ይወክላል።
- 1 ባለ 50 ሳንቲም 2 ባለ 25 ሳንቲም ዲናሮችን ይወክላል።
- ከአንድ ብር ኖቶች ወደ ሳንቲም ዲናሮች ለመቀየር የተሰጠውን ብር በ100 ማባዛት ሲሆን ደግሞ ከሳንቲም ወደ ብር ለመቀየር የተሰጠውን ሳንቲም በ100 ማካፈል ይሆናል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛው ዋጋ ሙሉ።
   ሀ. 85 ብር — ሳንቲሞች ይሆናል።
   ለ. በ15 ብር ውስጥ — ባለ 50 ሳንቲሞች አሉ?
   ሐ. በ300 ብር ውስጥ — ባለ 50 ብር ኖቶች አሉ?
   መ. 1 ባለ 50 ብር ኖት = — ባለ 10 ብር + አራት ባለ 5 ብር ኖት ነው።
   ሠ. 34 ብር ከ50 ሳንቲም — ባለ ሳንቲሞች ይሆናል።
   ረ. 1 ባለ ሃምሳ ብር ኖት = — ባለ 10 ብር ኖት + 6 ባለ 5 ብር ኖት ነው።
2. 1 ባለ መቶ ብር ስንት ባለ አምስት ብር ኖቶች ይሆናል?
3. 4 ባለ 50 ሳንቲም ስንት ባለ 25 ሳንቲሞች ይሆናል?
4. 1 ባለ 50 ብር ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች ይሆናል?
5. ከሁሉም የኢትዮጵያ ብር ኖቶች አንድ አንድ በተናጠል ወስደን ብንደምራቸው በጠቅላላው ስንት ብር ይሆናሉ?

6. አንድ ባለ መቶ ብር ኖት + አራት ባለ ሃምሳ ብር ኖት + አስር ባለ አስር ብር ኖት = — መቶ ብር ኖት ይሆናል።
7. ባለ 5 ብር፣ ባለ 10 ብር፣ ባለ 50 ብር፣ ባለ 100 ብር፣ ባለ 200 የብር ኖቶችን በምን በምን ይለያያሉ? አብራሩ።
8. የአቶ አስፋው የወር ደሞወዝ 5,400 ብር ነው። ደሞወዙን እንደተቀበለ 400 ብር ለእናቱ፣ 800 ብር ለአባቱ እና ለቀለብ ወጪ 2,500 ብር አወጣ። እንዲሁም ለቤት ኪራይና ለትራንስፖርት 1,000 ብር ከፈለ።
    ሀ. በጠቅላላው አቶ አስፋው ስንት ብር አወጣ?
    ለ. አቶ አስፋው ከወጪ ቀሪ ስንት ብር አለው?

ምዕራፍ አስራ ሁለት

12. የኢትዮጵያ ጊዜ

መግቢያ

በሁለተኛ ክፍል ሒሳብ ትምህርታችሁ በአናሎግ ወይም በድጂታል ሰዓት ላይ ጊዜን: በሰዓት፣ በግማሽ ሰዓት እና በሩብ ሰዓት መከፋፈልን፤ሰዓትን ወደ ደቂቃ ወይም ደቂቃ ወደ ሰዓት መቀያየር እና ጊዜ ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት ተምራችኋል። አሁን ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት የሰዓት ንባብ፣ ሰዓትና ደቂቃ፣ ቀን፣ ሳምንት፣ ወር እና ዓመት፤ ቀላል የኢትዮጵያን የቀን አቆጣጠር እና የኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር የያዘ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትማራላችሁ።

የምዕራፉ ዓላማዎች፦ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የኢትዮጵያን የሰዓት አቆጣጠር እንዴት እንደሚነበብ ትረዳላችሁ።
- ከአንድ የጊዜ መለኪያ ወደ ሌላ የጊዜ መለኪያ ምድብ እንዴት እንደሚቀየር እና እንደሚመነዘር ትለያላችሁ።
- የኢትዮጵያን የጊዜ አቆጣጠር በነባራዊ የኑሮ ሁኔታዎች ጋር የሚዛመዱ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትተገብራላችሁ።

12.1 የሰዓት አነባበብ

መግቢያ

ከዚህ በፊት በሁለተኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርታችሁ በአናሎግ ወይም በድጂታል ሰዓት ላይ ጊዜን: በሰዓት፣ ግማሽ በሰዓት እና በሩብ ሰዓት መከፋፈልን መማራችሁ

ይታወሳል። አሁን ደግሞ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ ሰዓትን እንዴት ማንበብ እንደምትችሉና እንደምትረዱ ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሰዓት እና የደቂቃ መጠቆምያዎችን ትለያላችሁ።

ተግባር 12.1

የሚከተሉትን ተመልክታችሁ ሰዓቱን አንብቡ።

ሀ 

11:45

ለ 

3:00

ሐ 

7:30

ማስታወሻ፦

ጊዜን ለመለካት የምንጠቀምበት መሳሪያ ሰዓት ነው። በአብዘኛው የጊዜ ልኬት በሰዓትና በደቂቃዎች ይገለፃል።

በታች ያለው የሰዓት ምስል ነው።



ከምሳሉ በማየት የሚከተሉትን አስተውሉ።

- በምስሉ አጠርና ወፈር ያለው አመልካች ሰዓት ቆጣሪ ይባላል።
- ከሰዓት ቆጣሪው በመጠኑ ረዘም ያለው አመልካች ደቂቃ ቆጣሪ ይባላል።

- እንደ ደቂቃ ቆጣሪው በመጠኑ ረዘም ቀጠን ያለው አመልካች ሰኮንድ ቆጣሪ ይባላል።
- የሰዓት አቆጣጠር አቅጣጫ ከ12 በመጀመር ወደ ቀኝ በመዞር ይሆናል።
- ደቂቃ ቆጣሪው ከ12 ተነስቶ ተመልሶ 12 ሲደርስ (አንድ ሙሉ ዙር) 1 ሰዓት ይባላል።
- ደቂቃ ቆጣሪው ከ12 ተነስቶ ተመልሶ 1 ላይ ሲያመለክት 5 ደቂቃ፣ 2 ላይ ሲያመለክት 10 ደቂቃ፣ 3 ላይ ሲያመለክት 15 ደቂቃ፣ 6 ላይ ሲያመለክት 30 ደቂቃ፣ 9 ላይ ሲያመለክት 45 ደቂቃ ይባላል።

ምሳሌ 12.1፦ የሚከተሉትን ተመልክታችሁ ሰዓቱን አንብቡ።

ሀ 

3:30

ለ 

10:10

ሐ 

11:35

መ 

1:45

ሠ 

5:50

መፍትሔ 12.1፦

ሀ. 3 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ተብሎ ይነበባል። ይህም 3:30 ተደርጎ ይፃፋል።

ለ. 10 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ተብሎ ይነበባል። ይህም 10:10 ተደርጎ ይፃፋል።

ሐ. 9 ሰዓት ከ25 ደቂቃ ተብሎ ይነበባል። ይህም 9:25 ተደርጎ ይፃፋል።

መ. 1 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ተብሎ ይነበባል። ይህም 1:45 ተደርጎ ይፃፋል።

ሠ. 5 ሰዓት ከ50 ደቂቃ ተብሎ ይነበባል። ይህም 5:50 ተደርጎ ይፃፋል።

ተግባር 12.2

የሚከተሉትን በቡድን ስሩ።

1. ካርቶን እና ማርከር ተጠቅማችሁ የሰዓት ሞዴል ሰርታችሁ የተለያዩ ሰዓቶችን በማመልከት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

መልመጃ 12.1

የሚከተለትን ጥያቄዎች ስሩ።

1. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሰዓት በሁለት መንገድ በ"ሀ" መሰረት ግለጹ።
   ሀ. 3:45 3 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ወይም ለ4 ሰዓት ሩብ ጉዳይ
   ለ. 6:50 — ሰዓት ከ — ደቂቃ ወይም ለ— ሰዓት — ጉዳይ

   ሐ. 7:55 — ሰዓት ከ — ደቂቃ ወይም ለ— ሰዓት — ጉዳይ

   መ. 3:40 — ሰዓት ከ — ደቂቃ ወይም ለ— ሰዓት — ጉዳይ

   ሠ. 12:35 — ሰዓት ከ — ደቂቃ ወይም ለ— ሰዓት — ጉዳይ
2. ቀጥሎ ያሉትን ጊዚያት የሚያሳዩ የአናሎግ ሰዓት ሞዴሎችን ሳሉ።
   ሀ. 2:45 ለ. 4:20 ሐ. 12:55 መ. 9:05
3. ምስሎችን ተመልክታችሁ ሰዓቱ የሚያሳየውን ጊዜ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

ሀ  ለ  ሐ  መ  ሠ 

12.2 ሰዓት እና ደቂቃ

መግቢያ

ቀደም ሲል የሰዓቶችን አቆጣጠርና ሰዓቶችን ማንበብ ተምራችኋል። አሁን ደግሞ ሰዓትና ደቂቃ ያላቸውን ዝምድና ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሰዓታትን ወደ ደቂቃዎች ትቀይራላችሁ።

ተግባር 12.3

የሚከተለትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. በ5 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
2. 240 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነው?
3. በሰዓትና ደቂቃ መካከል ያለውን ዝምድና አሳዩ ።
4. በ130 ደቂቃዎች ውስጥ ስንት ሰዓትና ደቂቃዎች አሉ?

ማስታወሻ፦

1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

ሀ. ሰዓትን ወደ ደቂቃ ለመቀየር የተሰጠውን ሰዓት በ60 ማብዛት

ለ. ደቂቃዎችን ወደ ሰዓት ለመቀየር በ60፣ በ60 መድቦ ምደቦችን መቁጠር ይሆናል።

ምሳሌ12.2፦

2 ሰዓት = 2 × 60 ደቂቃዎች = 120 ደቂቃዎች

3 ሰዓት = 3 × 60 ደቂቃዎች = 180 ደቂቃዎች

4 ሰዓት = 4 × 60 ደቂቃዎች = 240 ደቂቃዎች

6 ሰዓት = 6 × 60 ደቂቃዎች = 360 ደቂቃዎች

60 ደቂቃዎች = አንድ 60 ደቂቃዎች = 1 ሰዓት

120 ደቂቃዎች = 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ = ሁለት 60 ደቂቃዎች = 2 ሰዓት

240 ደቂቃዎች = 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ

= አራት 60 ደቂቃዎች = 4 ሰዓት

መልመጃ 12.2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ገልብጡና መልሳቸውን ፃፉ።

1. በ5 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
2. በ7 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
3. 180 ደቂቃዎች ስንት ሰዓት ነው?
4. 300 ደቂቃዎች ስንት ሰዓት ነው?
5. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

ሰዓት	ደቂቃ
3	
	120
6	
	300
7	

12.3 ቀን፣ ሳምንት፣ ወር እና ዓመት

መግቢያ

ከዚህ በፊት ሰዓትና ደቂቃ ያላቸውን ዝምድና ተምራችኋል። አሁን በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ላይ ቀን፣ ሳምንት፣ ወር እና ዓመትን መለዋወጥ ወይም መቀያየርን ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ዓመታትን ወደ ወራት፣ ሳምታት እና ቀናት ትቀይራላችሁ።

ተግባር 12.4

የሚከተሉትን በቡድን ስሩ።

1. በአንድ ቀን ስንት ሰዓታት አሉ?
2. በአንድ ሳምንት ስንት ቀናቶች አሉ?
3. በአንድ ወር ስንት ቀናቶች አሉ?
4. በአንድ ዓመት ስንት ወራቶች አሉ?
5. በአንድ ዓመት ስንት ቀናቶች አሉ?

ማስታወሻ፦

1 ሰዓት = 60 ደቂቃዎች 1 ሳምንት = 7 ቀናት

1 ቀን = 24 ሰዓታት 1 ወር = 30 ቀናት

1 ዓመት = 13 ወራት ሆኖ 13ኛው ወር **ጳጉሜ** በኢትዮጵያ ብቻ የምቆጠር ነው። የቀናትም ብዛት 5 ወይም 6 በአራት ዓመት ይሆናል።

ምሳሌ12.3፦

1. በ2 ቀን ውስጥ ስንት ሰዓታት አሉ?
2. በግማሽ ዓመት ውስጥ ስንት ወራት አሉ?

መፍትሔ፦

ሀ. በአንድ ቀን ውስጥ 24 ሰዓታት አሉ። ስለዚህ ሁለት ቀናት ውስጥ $2 \times 24 = 48$ ሰዓታት ይኖራሉ።

ለ. በአንድ ዓመት ውስጥ 12 ወራት አሉ (የጳጉሜ ወር ሳይካተት)። ስለዚህ ግማሽ ዓመት ውስጥ $12 \div 2 = 6$ ወራት ይኖራሉ።

መልመጃ 12.3

1. የሚከተለትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ።

ሀ. 5 ሳምንት = — ቀናት

ለ. ሩብ ዓመት = — ወራት

ሐ. 27 ቀናት = — ሳምንታት

መ. 6 ወር = — ቀናት

ሠ. 7 ዓመት = — ወራት

ረ. 2 ወራት = — ቀናት

ሰ. 2 ዓመት = — ቀናት

ሸ. 2 ወራት = — ሳምንታት

2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ።

ዓመት	ወር	ሳምንት	ቀን
3			
	48		
		288	
			672

3. የካሳሁን ዕድሜ 12 ዓመት ከ6 ወር ነው። የካሳሁን ዕድሜን ወደ ወር ስንቀይር ስንት ወር ይሆናል?
4. ሁለት ወጣቶች ተከታታይ የእጅ ኪስ ዳኝነት ሰልጠና ሰልጥነዋል። የመጀመሪያውን ስልጠና በ5 ሳምንት፣ ሁለተኛውን ስልጠና ደግሞ በሶስት ወር አጠናቀቁ። ሁለቱ ወጣቶች ለማጠናቀቅ ስንት ሳምንታት ፈጀባቸው?

12.4 ቀላል የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር

መግቢያ

ከዚህ በፊት ቀን፣ ሳምንት፣ ወር እና ዓመትን እንዴት መቀየር እንደሚቻል ተምራችኋል። አሁን በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ቀላል የኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ትማራላችሁ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ዓመታትን ወደ ወራት፣ ሳምታት እና ቀናት ትቀይራላችሁ።

ተግባር 12.4

1. አንድ የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ምን ምን እንደሚያካትት ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።
2. በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ካሉ በዓላት ውስጥ ሁለቱን ፃፉ።

ማስታወሻ፦

የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር (ካላንደር) የሚይዟቸው ዓመት ምሕረት፣ ወራቶች፣ ሳምንቶችና ቀናቶች ናቸው። እንዲሁም የተለያዩ በዓላትና ቀናትን ያመልክታል። የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር በዓመት ውስጥ የሚገኙ ወራት እና ቀናት ያላቸውን ዝምድና በቅደም ተከተል የሚያሳይ የመርጃ ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል። የኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር በዓመት ውስጥ የሚከበሩ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ በዓላት አካትተው ይይዛል። እንዲሁም በዓመት ውስጥ ያሉ ወራት መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴና ጳጉሜ ናቸው።

ምሳሌ12.4፦

የሚከተለው ካላንደር የ2013 ዓ/ም የነሐሴ ወር እና የ2014 ዓ/ም የመስከረም ወር ተመልክታችሁ ጥያቄዎችን መልሱ።

ነሐሴ ወር 2013 ዓ/ም						
እ	ሰ	ማክ	ረቡ	ሐ	ዓር	ቅ
						1
2	3	4	5	6	7	8
9	10	11	12	13	14	15
16	17	18	19	20	21	22
23	24	25	26	27	28	29
30						

መስከረም ወር 2014 ዓ/ም						
እ	ሰኞ	ማ	ረ	ሐ	ዓ	ቅ
						1
2	3	4	5	6	7	8
9	10	11	12	13	14	15
16	17	18	19	20	21	22
23	24	25	26	27	28	29
30						

ሀ. በ2013 ዓ/ም የነሀሴ ወር 2ኛው ቅዳሜ ቀኑ ስንት ነበር?

ለ. በ2014 ዓ/ም የመስከረም ወር 3ኛው ማክሰኞ ቀኑ ስንት ነበር?

ሐ. የ2014 ዓ/ም የእንቁጣጣሽ ወይም የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መለወጫ በምን ቀን ነበር ያለፈው?

መ. የመስከረም የመጀመሪያው ረቡዕ ቀን ስንት ነበር?

መፍትሔ፦

ሀ. የነሀሴ ወር 2ኛው ቅዳሜ ቀኑ 8 ነበር። ስለዚህ ይህ መልስ ከካላንደር ነው።

ለ. የመስከረም ወር 3ኛው ማክሰኞ ቀኑ 18 ነበር። ስለዚህ ይህ መልስ ከካላንደር ነው።

ሐ. የ2014 ዓ/ም የእንቁጣጣሽ ወይም የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መለወጫ መስከረም 1 ቅዳሜ ቀን ነበር የዋለው።

መ. የነሀሴ ወር የመጀመሪያው ረቡዕ ቀን 5 ነበር።

ምሳሌ12.5፦

ከዚህ በላይ የተሰጡ ካላንደሮች የ2013 ዓ/ም የነሐሴ ወር እና የ2014 ዓ/ም የመስከረም ወር ናቸው። በዚህ መሠረት:

1ኛ) ነሀሴ 7 የሚውለው ዓርብ ዕለት ነው። ይህ ቀን ሲገለጽ፦

- ዓርብ ነሀሴ 7፣ 2013 ዓ/ም ወይም 7/12/2013 ዓ/ም ተብሎ ነው።

7 / 12/ 2013 ዓ/ም

ሰባተኛው ቀን አስራ ሁለተኛ ወር 2013 ዓመት ምሕረት

2ኛ) መስከረም 18 የሚውለው ማክሰኞ ዕለት ነው። ይህ ቀን ሲገለጽ፦

- ማክሰኞ መስከረም 18 ቀን 2014 ዓ/ም ወይም 18/01/2014 ዓ/ም ተብሎ ነው።

3ኛ) ነሀሴ 5 ቀን 2013 ዓ/ም የሚውለው በአጭሩ 5/12/2013 ዓ/ም ብለን መግለጽ

እንችላለን።

4ኛ) የነሀሴ 22 ቀን 2013 ዓ/ም የሚለውን በአጭሩ 22/12/2013 ዓ/ም ተብሎ ይፃፋል።

መልመጃ 12.4

የሚከተለትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ስሩ።

1. ከዚህ በታች ያለውን የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ጥቅምት ወር 2014 ዓ/ም						
እ	ሰ	ማክ	ረቡ	ሐ	ዓር	ቅ
	1	2	3	4	5	6
7	8	9	10	11	12	13
14	15	16	17	18	19	20
21	22	23	24	25	26	27
28	29	30				

ሀ. ጥቅምት 10 በምን ቀን ይውላል?

ለ. ጥቅምት ወር 2ኛው እሁድ ቀኑ ስንት ነው?

ሐ. ጥቅምት 30 በምን ቀን ይውላል?

መ. ጥቅምት ወር 4ኛው ሰኞ ቀኑ ስንት ነው?

2. ህዳር ስንተኛው ወር ነው?
3. ሐምሌ ስንተኛው ወር ነው?
4. የሚከተሉትን ቀኖች በአጭሩ ፃፉ።
   ሀ. መስከረም 19 ቀን 2009 ዓመት ምሕረት
   ለ. ታህሳስ 28 ቀን 2010 ዓመት ምሕረት
   ሐ. ሚያዝያ 4 ቀን 2010 ዓመት ምሕረት
5. በክፍላችሁ ውስጥ ያለውን የቀን መቁጠሪያ ተጠቅማችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።
   ሀ. የዚህ ዓመት ህዳር 4 በምን ዕለት ዋለ?

ለ. የዚህ ዓመት ጥር 11 በምን ዕለት ዋለ?

ሐ. የዚህ ዓመት ግንቦት 20 በምን ዕለት ዋለ?

መ. የዚህ ዓመት ሰኔ 30 በምን ዕለት ይውላል?

የምዕራፍ አስራ ሁለት ማጠቃለያ

- ጊዜን ለመለካት የሚንጠቀምበት መሳሪያ ሰዓት ነው።
- በሰዓትና በደቂቃ መካከል ያለው ግንኙነት 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ
- ሰዓትን ወደ ደቂቃ ለመቀየር የተሰጠውን ሰዓት በ60 ማባዛት ሲሆን፥ ደቂቃዎችን ወደ ሰዓት ለመቀየር በ60 መድቦ ምደቦችን መቁጠር ይሆናል።
- የቀን፣ የሳምንት፣ የወር እና የዓመት ዝምድና ሲገለጽ፦

1 ቀን = 24 ሰዓታት፣ 1 ሳምንት = 7 ቀናት፣ 1 ወር = 30 ቀናት ወይም 4 ሳምንት ከ2 ቀን ማለት ነው።

1 ዓመት = 12 ወራት ጳጉሜ 5 ወይም 6 ቀናት ነው።

- የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር (ካላንደር) የሚይዟቸው ዓመት ምሕረት፣ ወራቶች፣ ሳምንቶችና ቀናቶች ናቸው። እንዲሁም ብሔራዊና ዓለም አቀፍ የበዓላት ቀናትን ያመልክታል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ሰዓቶች የሚያሳዩ የአናሎግ የሰዓት ሞዴሎችን በደብተራችሁ ላይ ሳሉ።
   ሀ. 2:15 ለ. 7:00 ሐ. 9:45
2. በ9 ሰዓት ውስጥ ስንት ደቂቃዎች አሉ?
3. በ540 ደቂቃዎች ውስጥ ስንት ሰዓታት አሉ?
4. ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም የጣጂቱ ዕድሜ 8 ዓመት ከ4 ወር ነበር። ጣጂቱ የ12 ዓመት ልደቷን መቼ ታከብራለች?
5. ለአንድ ፈተና የተመደበው ጊዜ ሁለት ሰዓት ነው። ፈተናው ከጧት 2:30 ቢጀመር በስንት ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል?
6. የሚከተሉትን በሰዓት የጊዜ መሰፈሪያ ምድብ ግለጹ።
   ሀ. 4 ቀናት ለ. 7 ቀናት ሐ. 2 ሳምንታት መ. 3 ሳምንታት
7. የሚከተሉትን ወደ ደቂቃ ለውጡ።

ሀ. 3 ቀናት ለ. 5:15 ሐ. 10 ሰዓታት መ. 3 ሳምንታት

8. የሚከተሉትን ወደ ሰዓት ለውጡ።

ሀ. 5 ሳምንታት ሐ. 3 ወራት

ለ. 3 ቀናት መ. 2 ቀን ከ180 ደቂቃ

9. ተማሪ ትዝታ በቅዳሜ ቀን ቤተመጽሐፍት ቤት ገብታ 3:00 እስከ 5:00 ሰዓት ድረስ አነበበች። ትዝታ ቤተመጽሐፍት ቤት ገብታ ያነበበችው ስንት ደቂቃ ነው?